Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

መቅድም ።

« ሮሜዎና ፡ ዠልዬት» ፡የተባለውን ፡ በዓለም ፡ ላይ፡ በጣም ፡ የታወቀውን ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ደራሲያን ፡ ኮጽፎ ፡ የተገኘውን ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ ቢሚርኛ ፡ ጽፌ ፡ በቴትር ፡ መልክ ፡ አድርጌ ፡ ሳቀርብ ፡ መግለጫ ፡ የሆነውን ፡ ኩተታ ፡ ጨምሬ ፡ ላንባቢዎች ፡ ማስረዳት ፡ አስፈላጊ ፡ ያኖ ፡ ታየኝ ።« የሮሜዎና ፡ ዠልዬት ፡ »ዜና ፡ በታሪክ ፡ ኮጽፎ ፡ የተገኘ ፡ በኢጣሊያን ፡ አገር ፡ በቬሮና ፡ ከተማ ፡ ተዳረገ ፡ ነገር ፡ ነው ። ሲኒማውም ፡ በየጊዜው ፡ አዲስ ፡ ባ ፡ ታይቷል ። በደራሲያን ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ ሳደሩ ፡ የተነሣ ፡ አርተር ፡ ብሩክ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ግሊዝ ፡ ባለቅኔ ፡ መዠመሪያ ፡ በግጥም ፡ ጻፈው ። ኮ ፡ ሼክስፒር ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመ ል ፡ ቴአትር ፡ አድርጎ ፡ አቀረበው ። ይኸውም ፡ በዓ ፡ ላይ ፡ ከተመሠረቱት ፡ ዋና ፡ ዋኖቹ ፡ የድርስት ፡ ራዎች ፡ እንደ ፡ እንዱ ፡ ሆኖ ፡ ተቈዋሯል ።

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ ስጽፈው ፡ ላገራችን ፡ አንባቢ ዎች ፡ መንፈስ ፡ እንደሚስማማ ፡ ለኔም፡ለራሴ ፡ ባማርኛ ፡ ለመግለጥ ፡ እንደሚመቸኝ ፡ አድርጌ ፡ አቅርቤዋለሁ ። ሌሎች ፡ ደራሲያን፡የጸፉትን ፡ ድርሰት ፡ ሰው ፡ ላገሩ፡ሰዎች ፡ በራሱ ፡ ቋንቋ ፡ ሊያሰማ ፡ ሲፈልግ ፡ ወይም ፡ ይተረጕመ



ከዘደ ሚካኤ
ትዮጵያ ሥነ
ውስጥ ግናና
ደራሲያን አንዱ
ጥቅምት 23፣
የተወለዱት ባለቅ
ክህነትን ትምህር
ባደጉ በኋላ በ
ፍራንሲዝና በ
ሚስዮን ዘመናዊ
ትን ተክታትለዋ
ሪክ፣ የሮማውያን
ግሊዝ፣ የፈ ንሳ
ርመን፣ የሩስያና
ያንን በርካታ ወ
ከመ ረመሩም በ
ስድስት መ
ለወገኖቻ ፕሙ
ተ ል።

የአዲ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዚሁ አስተዋዕኦዋው
ያከተርንት ዲፕ 1990 በስጠበት ወቅትም፣ «በድርሰተ
ሙስና የሚታዩ ፣ ሳእኒህ ታላት ደራሲ የሃሳብ ንግስ
ታላ ዘይቤዎች ሌሎች የአማፍ ስልት ገዕታዎች ይኒህ
ደራ ሥች ያደረገ ኑ አስተዋዕኦ ቀላል አይደ ስም።
ዘረፍ ዘዴ ፣ ኑ ኑስ በርካታ ደራሲያኑ የሳቸውን
ዘዘጡ፣ ባሳቸው ሥነዕሁፍን አውቀውና ሕ
ደራሲ ሊሆኑ በቅተዋል ሊል።

ሚ ተ ሚ ሥ ኑም የኒህን ሊቅ ሥራዎች ለ
ማጥናና ለመፍናት ተ ውል ሚ የሚኖራቸውን ፋይዳም
የሚከተሉትን መፅሐፎቻቸውን ለአንባቢያን አቅርቧል።

1. ታሪክና ምሳሌ (ፅኛ መፅሐፍ)
2. ታሪክና ምሳሌ (፪ኛ መፅሐፍ)
3. የቅኔ ርዕት
4. ሮሜዎና ዠልዬት
5. የፈጣቱት ነልጭታ
6. ጃፓን እንደምን ሰለጠነች?
7. ኃ ሳላቅ ፈምቾ

ሚኒ አሳታሚ ድርጅት

ብርሃን ለሚ ማተሚያ ድርጅት

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ዋል ፤ አለዚያም ፡ ደግሞ ፡ (ይልቁንም ፡ በግጥም ፡ ሊ
ራው ፡ ሲፈልግ) አስመስሎ ፡ ሠርቶ ፡ ያቀርበዋል ። ትር
ጉም ፡ ማለት ፡ ሳይለወጥ ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ ቃል ፡
በቃል ፡ መተርጐም ፡ ነዉ ። አስመስሎ ፡ መሥራት ፡
ግን ፡ የዋናውን ፡ ታሪክ ፡ መንገድ ፡ ሳይለቁ ፡ የተሻለ ፡
መስሎ ፡ በታየው ፡ አኳኋን ፡ ቃሉንና ፡ አካሄዱን ፡ እየ
ለወጡና ፡ እያዘዋወሩ ፡ ሠርቶ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። ወይም ፡
ደግሞ ፡ ታሪኩን ፡ ብቻ ፡ በመከተል ፡ ከቃሉ ፡ ግን ፡ የሚ
ስማማውን ፡ ወስዶ ፡ የማይስማማውን ፡ ትቶ ፡ ከራሱ ፡
ጨምሮ ፡ መጻፍ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በፈረንጆች ፡ (አዳ
ፕታሲዮን ፡ ወይም ፡ ኢሚታሲዮን ፡ ይባላል) ።

ይህን ፡ በመሰለው ፡ ጉዳይ ፡ ደራስያን ፡ ያለባቸውን ፡
የተግባር ፡ ሐተታ ፡ ጥቂት ፡ ብናስተውል ፡ አይከፋም ።
በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈውን ፡ ድርሰት ፡ ሰው ፡ ላገሩ ፡
ሰዎች ፡ ጽፎ ፡ ለማሰማት ፡ ሲፈልግ ፡ በደንበኛው ፡ ትር
ጉም ፡ ወይም ፡ (ብአዳፕታሲዮን ፡ በኢሚታሲዮን) ፡
ሙያው ፡ በሚፈቅድለት ፡ መንገድ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለማቅ
ረብ ፡ ነጻነት ፡ አለው ።

በውስጣቸው ፡ የሚገኘው ፡ ትምህርትና ፡ አብነት ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ በጠቅላላውም ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡
ምሳሌነቱ ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ ከታሪክ ፡ የተወሰዱ ፡
አንዳንድ ፡ አርእስቶች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋና ፡ በልዩ ፡

ልዩ ፡ ደራስያን ፡ ሲጻፉ ፡ ይኖራሉ ። ለዚሁም ፡ የፎስት ፡
ታሪክ ፡ ምሳሌ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የጥንቶቹ ፡ የግሪክ ፡ ደራስያን ፡
እነኤሺል ፡ እርፒድ ፡ የጻፏቸው ፡ «ኤዲፐ» ፡«አንቲጎን» ፡
«ኢፊጌኒ» ፡ የተባሉ ፡ ቴአትሮች ፡ አሉ ። በኋላም ፡ እነዚ
ሀኑ ፡ አርእስቶች ፡ ባዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ የተነሡት ፡
ደራስያን ፡ እነኮርኔይ ፡ ራሲን ፡ ቮልቴር ፡ ጎት ፡ በየቋንቋ
ቸው ፡ አዲስ ፡ ቅርጽና ፡ አዲስ ፡ አካሄድ ፡ እየሰጧቸው ፡
የታሪኩን ፡ ምንጭ ፡ ሳይለቁ ፡ በኢሚታሲዮን ፡ ጽፈዋቸ
ዋል ። «የሮሜዎና ፡ ዠልዬት» ፡ ታሪክም ፤ እንደዚሁ ፡
በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደራስያን ፡
ተጽፏል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ስናስተውለው ፡ አንዱን ፡
የድርሰት ፡ አርእስት ፡ ያንድ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡
ብዙ ፡ ደራስያን ፡ ሊሠሩት ፡ ይችላሉ ። ምክንያቱም ፡
« የትም ፡ ፍጪው ፡ ዱቄቱን ፡ አምጪው» ፡ እንደሚ
ባለው ፡ ተረት ፡ ከሠራተኛ ፡ የሚፈለገው ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡
ሠብ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ እንዲያቀርብ ፡ በመሆኑ ፡
ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ደራስያን ፡ ባገራቸው ፡
ቋንቋ ፡ ሌሎች ፡ ደራስያን ፡ አስቀድሞ ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡
መልሰው ፡ ለዘመኑ ፡ በሚስማማ ፡ ቅርጽ ፡ አሻሽለው ፡
ሲያቀርቡት ፡ ይታያሉ ። ምሕረት ፡ የሌለው ፡ ነውር ፡

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ ሌላ ፡ ደራሲ ፡ የጻፈውን ፡ ቃል ፡ ወስዶ ፡ የራስ ፡ ሲያደርጉ ፡ መገኘት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ቄራርጦና ፡ ለዋውጠ ፡ ለማሻሻል ፡ ሲፈ ለግ ፡ ትልቅ ፡ ባለሙያ ፡ መሆን ፡ ያሻል ። ይህንኑም ፡ ያግ ራችን ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ስለ ፡ ፈደል ፡ ሐተታ ፡ መዝገበ ፡ ፊደል ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፤

«የፊደልን ፡ ገላ ፡ ደፍሮ ፡ ለመቊረጥ ፡

ሐኪም ፡ መሆን ፡ ያሻል ፡ በአፍአ ፡ በውስጥ» ፡ ሲሉ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ ለዚህ ፡ አሳብ ፡ ደጋፊ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፤ ስለ ፡ ፎስት ፡ ታሪክ ፡ ከጥንት ፡ ተያ ይዞ ፡ የመጣው ፡ ዜና ፡ ሊቁ ፡ ፎስት ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱ ፡ ተኰነነች ፡ ይላል ። ብዙዎችም ፡ ደራስያን ፡ በድርሰታቸው ፡ ይህንኑ ፡ አጽድቀውታል ። ገት ፡ ግን ፡ ለፍልስፍናውም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለራሱ ፡ ምኞት ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ የፎስት ፡ መኰነን ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘው ፡ የታሪኩን ፡ አካሄድ ፡ አፍርሶ ፡ በድርሰቱ ፡ ውስጥ ፡ ፎስት ፡ በማርገሪት ፡ አማላጅነት ፡ እንዲጸድቅ ፡ አደረገው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የገ ትን ፡ ባለሙያነት ፡ ማንኛውም ፡ ደራሲ ፡ ሊያገኘው ፡ አይችልም ።

በፈጠራ ፡ የተገኘውን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ የሆነ ፡ ታሪክ ፡ ለመለወጥ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ መሠረቱ ፡ ከውነተኛ ፡ የታሪክ ፡ ምንጭ ፡ ለተቀዳው ፡ ዜና ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ እውነተኛውን ፡ መንገድ ፡ መከተል ፡ የተሻለ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለምሳሌ ፡ አንዳንድ ፡ የፈረንሳይ ፡ ባለቅኔዎች ፡ ዱሲስን ፡ የመሰሉ ፡ ኪሼክስፒር ፡ በኋላ ፡ ይህ ንኑ ፡ « የሮሜዎንና ፡ ጁልዬትን » ፡ ታሪክ ፡ በፈረንሳይ ፡ ቋንቋ ፡ ጽፈው ፡ በቴአትር ፡ ሲያቀርቡት ፡ እናሻሽላለን ፡ በማለት ፡ ከሼክስፒር ፡ አካሄድ ፡ በጣም ፡ ርቀው ፡ እየሄዱ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ በመለወጣቸው ፡ ሥራቸው ፡ ተበላሽቶባቸ ዋል ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ሼክስፒር ፡ ቴአት ሩን ፡ የጻፈው ፡ ከዋናው ፡ የታሪክ ፡ ምንጭ ፡ ቀድቶ ፡ ከሆነ ፡ እሱን ፡ መከተል ፡ እንደሚገባ ፡ የሱን ፡ መንገድ ፡ ለውጠ ፡ ለመሥራት ፡ ማሰብ ፡ ግን ፡ ከእውነተኛው ፡ ነገር ፡ መራ ቅን ፡ እውነተኛ ፡ የሆነውንም ፡ ነገር ፡ ሠርዞ ፡ ፈጠራ ፡ ማግባት ፡ የሚያምረውን ፡ ነገር ፡ ይበልጥ ፡ አሳምራለሁ ፡ በማለት ፡ እንዲበላሽ ፡ ማድረግን ፡ እንደሚያስከትል ፡ ባለማስተዋላቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይኸንኑ ፡ በመመ ልከትና ፡ ይህን ፡ ከመሰለውም ፡ ጉዳት ፡ ለመዳን ፡ ስል ፡ በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ የሼክስፒርን ፡ አካሄድ ፡ ለመከተል ፡ ሞክሬያለሁ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለዋናው ፡ ታሪክ ፡ ምንም ፡ ሊያጐድል ፡ የማይችለውን ፡ እንደ ፡ ጓርፍ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረውን ፡ በመተው ፡ ወይም ፡ ቃሉን ፡ በመለወጥ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማሳጠር ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ያልሆነውንም ፡ በመሰረዝ ፡ ያሻሻልኩት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አለ ። ባጭሩ ፡ የሼክ ስፒርን ፡ መንገድ ፡ ተከትዬ ፡ በራሴ ፡ ንግግርና ፡ አካሄድ ፡

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

በአዳፕታሲዮን መርኛ ፡ አቀረብኩት ፡ እንጂ ፤ የሼክስ
ርን ፡ ቴአትር ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አልተረጐምኩትም ፡
ይህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ ዋናው ፡ አሳቤ ፡ « የሮሜዎንና ፡ ጥ
ዩትን » ፡ ታሪክ ፡ በራሴ ፡ ንግግር ፡ ለማሰማት ፡ ከመፈለግ
ይልቅ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆነውን ፡ የሼክስፒርን ፡ ሥራ ፡ ለ
ሳወቅ ፡ ፈልጌ ፡ ወዙንና ፡ ለዛውን ፡ ለመከተል ፡ የተጣ
ርኩበት ፡ መሆኔን ፡ አንባቢዎች ፡ ቢረዱልኝ ፡ እወዳለሁ ፡

ሼክስፒር ፡ ማለት ፡ ማነው ? ሼክስፒር ፡ ማለት ፡
የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ በደራሲነቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ኩብር ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ነው ። የእንግሊዝን ፡ ቋንቋ ፡ የተከ
በረ ፡ ያደረገው ፡ ሼክስፒር ፡ ነው ፡ ብንል ፡ ስለ ፡ ደራሲው ፡
ከሚገባው ፡ ግምት ፡ በላይ ፡ መናገር ፡ አይሆንብንም ፡
ለዚሁ ፡ አሳብ ፡ ደጋፊ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ አንዳንድ ፡
ጥቅስ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እናመጣለን ።

አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ደራሲ ፡ (ይልቁንም ፡
በግጥም ፡ ሲጽፍ ፡) የሥራው ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንዲ
ገመት ፡ ታሪኩን ፡ ራሱ ፡ ከልቡ ፡ አንቅቶ ፡ የፈጠረው ፡
እንዲሆን ፡ የሚያስፈልግ ፡ ይመስላቸዋል ። ይህ ፡ የሊቴራ
ቱርን ፡ ታሪክ ፡ ጠንቅቆ ፡ አለማወቅን ፡ የሚያሳይ ፡
ስሕተት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ሼክስፒር ፡ የጻፋቸውን ፡ ቴአ
ትሮች ፡ ሁሉ ፡ የቀዳው ፡ ከሱ ፡ በፊት ፡ ሌሎች ፡ ደራስ
ያን ፡ ከጻፉት ፡ ላይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ውብ ፡ በሆነ ፡

ንግግር ፡ አሳምሮ ፡ ለማቅረብ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ስጦታ ፡
ያገኘ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ አርእስቱን ፡ ከሌሎች ፡
ደራሲያን ፡ ላይ ፡ መውሰዱ ፡ የሥራውን ፡ ዋጋ ፡ ጥቂት ፡
እንኳ ፡ አልቀነሰበትም ። ይህንንም ፡ ስንል ፡ ሼክስፒር ፡
በደራሲያን ፡ ወይም ፡ በባለቅኔዎች ፡ ደረጃ ፡ ሲቀመጥ ፡
ከነሆሜር ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የመዝ
መሪያውን ፡ ማዕርግ ፡ ይዞ ፡ የሚኖር ፡ መሆኑን ፡ ማስገን
ዘብ ፡ እንወዳለን ።

ሼክስፒር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በዓለም ፡ የታ
ወቀ ፡ የተከበረና ፡ የተመሰገነ ፡ ባለቅኔ ፡ መሆኑን ፡ ለመ
ረዳት ፡ ብንፈልግ ፡ ባጭሩ ፡ አሌክሳንድር ፡ ዱማስ ፡ « ከእ
ግዚአብሔር ፡ ቀጥሎ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የፈጠረ ፡ ሼክስ
ፒር ፡ ነው » ፡ ሲል ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ መጥቀስ ፡
ይበቃ ፡ ይመስለኛል ።

ይህ ፡ አንድ ፡ የፈረንሳይ ፡ ደራሲ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡
ሲሆን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በእንግሊዞች ፡ ዘንድ ፡ ለሼክስ
ፒር ፡ የተደረገለትን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ እናስተውል ።

በጣም ፡ የታወቀውና ፡ በደራሲቱ ፡ የተመሰገነው ፡
ቶማስ ፡ ካርላይል ፡ የተባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ (ሌኮስ) ፡
አገር ፡ ደራሲ ፡ ስለ ፡ ሼክስፒር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡
ቃል ፡ ጽፍል ። « እናንተ ፡ እንግሊዞች ፡ የሀንድ ፡ መን
ግሥታችሁን ፡ ብታጡ ፡ ይሻላችኋልን ፡ ወይስ ፡ ደግሞ ፡

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

የናንተን ፣ ሼክስፒር ፣ ብታጡ ፣ ይሻላችኋል ? የሀንድን ፣ መንግሥት ፣ ጨርሳችሁ ፣ ያላገኛችሁት ፣ ሆናችሁ ፣ ብት ቀሩ ፣ ትወዳላችሁን ፣ ወይስ ፣ ደግሞ ፣ የናንተ፣የሆነውን ፣ ሼክስፒርን ፣ ፈጽሞ ፣ ያላገኛችሁት ፣ ብትሆኑ ፣ ትወዳላ ችሁ »? ተብለን ፣ ብንጠየቅ ፣ ኖሮ ፣ ምን ፣ እንመልስ ፣ ኖሯል ። በእውነቱ ፣ ይህ ፣ ጥያቄ ፣ ከባድ ፣ ሆኖ ፣ በተ ገኘ ፣ ነበር ። የመንግሥት ፣ ሰዎች ፣ የሆኑት ፣ አፈሲየል ፣ በሆነ ፣ ንግግር ፣ የሚመልሱ ፣ መሆናቸው ፣ አይጠረጠ ርም ። እኛ ፣ የእንግሊዝ ፣ ሕዝቦች ፣ ግን ፣ በበኩላችን ፣ የሀንድ ፣ መንግሥት ፣ ቢኖረን ፣ ወይም ፣ ባይኖረን ፣ ለኛ ፣ የሚበልጥብን ፣ ሼክስፒር ፣ ነው ፣ ብለን ፣ መመለስ ፣ ግድ ፣ ይሆንብናል ። በዚያም ፣ ሆነ ፣ በዚህ ፣ የሀንድ ፣ መንግ ሥት ፣ ውሎ ፣ አድሮ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ከእጃችን ፣ መው ጣቱ ፣ የማይቀር ፣ ነገር ፣ ነው ። ሼክስፒር ፣ ግን ፣ ሁል ፣ ጊዜ ፣ ከኛ ፣ ጋራ ፣ ይኖራል ። እኛም ፣ ደግሞ ፣ የኛ ፣ ሼክ ስፒር ፣ ከሆነው ፣ ጋራ ፣ ሳንለያይ ፣ አብረን ፣ እንኖራለን ።

ቶማስ ፣ ካርላይል ፣ ይህን ፣ ቃል ፣ የጻፈው ፣ እንደ ፣ አውሮፓ ፣ አቈጣጠር ፣ ካፒቷያቯቷ ፣ ዓ ፣ ም ፣ በፊት ፣ ነው ። የተናገረው ፣ ትንቢት ፣ እንሆ ፣ ከመቶ ፣ ዓመ ታት ፣ በኋላ ፣ ደረሰ ።

ዛሬ ፣ ሀንድ ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ በፈቃዷ ፣ በከመንዌልስ፣ አገሮች ፣ ጎብረት ፣ ውስጥ ፣ ብትሆን ፣ ከእንግሊዝ ፣ እጅ፣

ወጥታ ፣ ሙሉ ፣ ነጻነቷን ፣ አግኝታለች ። ሼክስፒር ፣ ግን፣ ከእንግሊዝ ፣ ሕዝብ ፣ ጋራ ፣ ሳይለያይ ፣ ዘለዓለም ፣ ይኖ ራል ።

ይህ ፣ ትልቅ ፣ ደራሲ ፣ ቶማስ ፣ካርላይል፣የተናገረው፣ ቃል ፣ የሕዝብ ፣ ትልቅነት ፣ የሚመሠረተው ፣ በግዛቱ ፣ ስፋትና ፣ በሀብቱ ፣ ብዛት ፣ ላይ ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ ይልቁ ንም ፣ የመንፈስ ፣ ሀብት ፣ በሆነው ፣ በሊቴራቱር ፣ ላይ ፣ ሆኖ ፣ በሠለጠኑት ፣ ሕዝቦች ፣ ዘንድ ፣ እንደሚገመት ፣ ይገ ልጥልናል ። ወደ ፣ ሠላሳ ፣ ስምንት ፣ በሚጠጉት ፣ ቴአት ሮቹ ፣ ውስጥ ፣ ሼክስፒር ፣ ሰዎችን ፣ እንደ ፣ ጠባይ፣እንደ፣ ጠባያቸው ፣ አድርጎ፣ሲያናግራቸውና፣ሲሠላቸው ፣መንፈስ፣ በሚገርክ፣ንግግሩ፣ጠባያቸውን፣ሲገልጠው ፣ ያለፉት ፣ የሞ ቱት፣የተረሱት፣ታሪክ፣ብቻ፣የሚያስታውሳቸው፣ሰዎች፣በሱ፣ ቴአትር ፣ ውስጥ ፣ ሕይወት ፣ አግኝተው ፣ እንዲንቀሳቀ ሱና ፣ ዘለዓለም ፣ እንዲኖሩ ፣ አድርጓቸዋል ። በደራሲነ ቱም ፣ እንደ ፣ ዋና ፣ ሞያ ፣ ሆኖ ፣ የሚቈጠርለት ፣ ጠባይ፣ በቴአትሩ ፣ ውስጥ ፣ የሚገኙትን ፣ ሰዎች ፣ ሁሉ ፣ ሕያዋን ፣ ሆነው ፣ እንዲኖሩ ፣ ሲያደርጋቸው ፣ ከጭካኔ ፣ ወደ ፣ ርኅ ራኄ ፤ ከቀልድ ፣ ወደ ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ካሸባሪነት ፣ ወደ፣ ርጋታ ፣ ከመንፈስ ፣ ግለት ፣ ወደ ፣ ደመ ፣ በራድነት ፣ ከጥል ቅነት ፣ ወደ ፣ ገርነት ፣ ለመዘዋወርና ፣ ለመለዋወጥ ፣ አስ ደናቂ ፣ ቅልጥፍና ፣ ያለው ፣ በመሆኑ ፣ ነው ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ምንም ፡ እንኳ ፡ የጸፈው ፡ አንዳንድ ፡ ኮሚዲ ፡ ቢኖር
ሼክስፒርን፡ ከቀሩት ፡ ደራስያን ፡ የተለየ ፡ የሚያደርገው
አንዱም ፡ የግል ፡ ጠባዩ ፡ የሱ ፡ ቴአትር ፡ ሁል ፡ ጊዜ
የሚፈጸመው ፡ በደም ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። « ማክቤት »
« ሐምሌት » ፡ « ንጉሥ ፡ ሊር » ፡ « አቴሎ » ፡ « ሮሚ
ዎና ፡ ዠልዬት » ፡ « አንቷንና ፡ ክሌዎፓትር » ፡ ሌሎ
ችም ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉት ፡ የሼክስፒር ፡ ቴአትሮች
በውስጣቸው ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ በክፋታቸው ፡ ቂመኞችና
በቀለኞች ፡ በመሆናቸው ፡ በምቀኝነታቸው ፡ የመንግሥ
ትን ፡ ሥልጣን ፡ በመፈለጋቸው ፡ በሰይፍ ፡ ይተራረዳሉ
በመርዝና ፡ በጩቤ ፡ ይጋደላሉ ፤ ይተላለቃሉ ። ስለዚህ
የሼክስፒር፡ሰዎች፡ሁል ፡ ጊዜ ፡ በደም ፡ሲዋኙ፡እናያቸዋለን።

የ« ሮሜዎና ፡ ዠልዬት » ፡ ታሪክ ፡ በሁለት ፡ ቤት
ሰቦች ፡ መካከል ፡ የተፈጠረ ፡ ቂምና ፡ በቀል ፡ ያስከተለ
ውን ፡ መዘዝ ፡ የሚገልጥ ፡ ነው ።

የሰዎችን ፡ ሕይወት ፡ ሼክስፒር ፡ እንደ ፡ ታላላቆቹ
የግሪክ ፡ የትራጄዲ ፡ ደራስያን ፡ የሚተረጉመው ፡ ባደጋ
ነው ። ናፖሌዎን ፡ ሲናገር ፡ ባደጋና ፡ በሞት ፡ « በትራ
ጄዲ » ፡ የማያልቅ ፡ ቴአትር ፡ ቴአትር ፡ አይደለም
ብሏል ።

ደስታና ፡ ተድላ ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ ዝቅ ፡ ሲያደር
ጉት ፡ አደጋና ፡ ሐዘን ፡ ግን ፡ ሰውን ፡ በጠባዩና ፡ በአእ
ምሮው ፡ ከፍ ፡ ያደርጉታል ።

አሪስቶትል ፡ (አርስጣጣሊስ) ፡ ሲናገር ፡ ትራ
ጄዲ » ፡ የማመለክተው ፡ ዐላማ ፡ የሽብርንና ፡ የርኅራ
ሄን ፡ ስሜት ፡ በመቀስቀስ ፡ የሰውን ፡ ፍትወቶች ፡ የጠሩ
የነጠሩ ፡ ለማድረግ ፡ ነው » ፡ ይላል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሼክስፒር ፡ ትራጄዲን ፡ ሲጽፍ ፡
ከሌሎቹ ፡ ደራስያን ፡ የተለየ ፡ ስጠታና ፡ ሙያ ፡ ያለው ፡
ሆኖ ፡ ይገኛል ። አንድ ፡ ደራሲ ፡ ሲናገር ፡ « ሆሜርና ፡
ሼክስፒር ፡ በእጃቸው ፡ የሚነኩትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ወርቅ ፡
ያደርጉታል » ፡ ብሏል ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

በቴአትሩ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ሰዎች ፦

- ኤስካሉስ ፡ ✓ — የቬሮና ፡ ከተማ ፡ መስፍን ፡
- ፓሪስ ፡ ✓ — የመስፍኑ፡ዘመድ፡የሆነ፡ወጣት፡መኳንን፡
- ሞንታግ ፡ ✓ — (ጠላቶች ፡ የሆኑ ፡
- ካፑሌ ፡ ✓ —) ሁለት ፡ ባላባቶች ፡
- ሮሜዎ ፡ ✓ — የሞንታግ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡
- ሜርኩቲዎ ፡ ✓ — የመስፍኑ ፡ ዘመድ፡ የሮሜዎ ፡ ወዳጅ፡
- ቤንቮሊዎ ፡ ✓ — የሞንታግ ፡ ዘመድ፡የሮሜዎ ፡ ወዳጅ፡
- ቲባልት ፡ ✓ — የካፑሌ ፡ ሚስት ፡ ዘመድ ፡
- አባ ፡ ሎራ ፡ ✓ — ካህን ፡
- አባ ፡ ዮሐንስ ✓ — ካህን ፡
- ቤልሻዋር ፡ ✓ — የሮሜዎ ፡ አሽከር ፡
- ሶምሶን ፡ ✓ — (የካፑሌ ፡
- ጎርጎርዮስ ፡ ✓ —) አሽከሮች ፡
- አብርሃም፡ ✓ — የሞንታግ ፡ አሽከር ፡
- አንድ ፡ መድኀኒት ፡ ሸያጭ ፡ ✓
- የፓሪስ ፡ እልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ✓
- አንድ ፡ የወታደር ፡ አለቃ ፡ ✓
- የሞንታግ ፡ ሚስት ፡ ✓
- የካፑሌ ፡ ሚስት ፡ ✓
- ጁልዬት ፡ ✓ — የካፑሌ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
- የጁልዬት ፡ ሞግዚት ፡ ✓
- ዘበኞች ፡ 3 ✓

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ካፑሌና ፡ ሞንታግ ፡ ሁለት ፡ ባላባቶች ፡
ሆነው ፡ የሚኖሩ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶች ፡
የእነሱም ፡ ወገኖች ፡ ባገረ ፡ ቬሮና ፡
ድንገት ፡ ሲገናኙ ፡ ሲያልፉ ፡ በጐዳና ፡
ጠብ ፡ እያበቀሉ ፡ በተንኰል ፡ በዘዴ ፡
ይተላለቃሉ ፡ በሰይፍ ፡ በጐራዴ ።
ሮሚዎና፡ ዡልዬት ፡ ሁለት ፡ ልጆቻቸው ፡
በጣም ፡ ተዋደዱ ፡ ፍቅር ፡ አድሮባቸው ፡
ግን ፡ አባቶቻቸው ፡ በነሱ ፡ መካከል ፡
ብርቱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የነበረው ፡ በቀል ፡
ዕርቅን ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ ከቂም ፡ ስላልወጡ ፡
በእነሱ ፡ ጎጢአት ፡ ልጆቹ ፡ ተቀጡ ።
ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ባገረ ፡ ቬሮና ፡
እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ የሚያስለቅስ ፡ ዜና ፡
እንባቢ ፡ ተመልከት ፡ እንግዲህ፡ እስተውለው፤
የምናቀርብልህ ፡ ታሪኩ ፡ ይኸ ፡ ነው ።

ሮሚዎና ፡ ዡልዬት ።

አንደኛ ፡ አክት ።

ትይንት ፡ ፩ ።

(በቤርና ፡ ከተማ ፡ አውራ ፡ መንገድ ፡ ላይ) ፡

ሶምሶንና ፡ ጎርጎርዮስ ፡

ሶምሶን ።

ዛሬ ፡ ሣር ፡ ቅጠሉ ፡ ዐፈርና ፡ ሙጃ ፡
ደም ፡ ደም ፡ ይሸተኛል ፡ ምክንያቱን ፡ እንጃ ።

ጎርጎርዮስ ።

የሞንታግ ፡ ወገኖች ፡ ሽተውህ ፡ ይሆናል ፤

ሶምሶን ።

የነሱማ ፡ ጠረን ፡ በሩቅ ፡ ይቀረናል ።

ጎርጎርዮስ ።

ምን ፡ ታዶርግ ፡ ኖሯል ፡ አሁን ፡ ብቅ ፡ ቢሉ ?

ሶምሶን ።

አይዘህ ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ አይነካም ፡ ጥሉ ፡
ግን ፡ እኔ ፡ በሰላም ፡ ብሄድም ፡ ዐርፌ ፡
ሳይጣላ ፡ አይቀርም ፡ ዐመለኛው ፡ ሰይፌ ።

ጎርጎርዮስ ።

አይጠረጠርም ፤ መቼም ፡ ካየናቸው ፤
እነሱም ፡ አይለቁን ፡ እኛም ፡ አንተዋቸው ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ሶምሶን ፦
እኔማ ፡ እንኳንስ ፡ እነሱን ፡ አይቼ ፡
ውሻቸውን ፡ ሰየው ፡ በድንገት ፡ አግኝቼ ፡
ያንቀጠቅጠኛል ፡ ደሜ ፡ እየተቄጣ ፦
ጎርጎርዮስ ፦
ከሞንታግ ፡ አሽከሮች ፡ ያው ፡ አንደኛው ፡ መጣ
አንዱም ፡ ተከተለ ፡ ብቅ ፡ አሉ ፡ ሁለቱ ፦
ሶምሶን ፦
ይንቀሳቀስ ፡ ጀመር ፡ የሰይፌ ፡ ስለቱ ፦
ጎርጎርዮስ ፦
እንግዲህ ፡ ተጠንቀቅ ፡ ሶምሶን ፡ ተሰናዳ ፤
ሶምሶን ፦
ብቻ ፡ እንዳያገኝን ፡ የዳኝነት ፡ ዕዳ ፡
አንድ ፡ ዘዴ ፡ እናምጣ ፡ ጠቡን ፡ እንዲያነሡ ፡
እዚህ ፡ ከኛ ፡ አጠገብ ፡ ጠብቄ ፡ ሲደርሱ ፡
ፊቴን ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡ እንዲያዩኝ ፡ መልሼ ፡
አስቄጣቸዋለሁ ፡ ከንፈሬን ፡ ነክሼ ፦
(አብርሃምና ፡ ቤልቫር ፡ መጡ) ፦
አብርሃም ፦
አንተ ፡ በኛ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ ከንፈር ፡ የምትነክሰው ፤
ሶምሶን ፦
እኔን ፡ አይጠይቅም ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ሰው ፦

አብርሃም ፦
በኛ ፡ ላይ ፡ እንደሆን ፡ ንገረኝ ፡ በፍጥነት ፡
ሶምሶን ፦
መጠየቅ ፡ አያሻም ፡ ከኖረህ ፡ ወንድነት ፦
አብርሃም ፦
ሁሉም ፡ በጃቸው ፡ ነው ፡ ሻምላ ፡ ሆነ ፡ ሰይፉም ፤
የሞንታግ ፡ ወገኖች ፡ ተሰድበው ፡ አያልፉም ፦
ሶምሶን ፦
የት ፡ አይተሻል ፡ ቀርተው ፡ መዋጋት ፡ ሳያውቁ ፤
የካፑሌ ፡ አሽከሮች ፡ በናንተ ፡ ሲጠቁ ?
አብርሃም ፦
ሊታይ ፡ ነው ፡ እኮ ፡ የናንተ ፡ ጉብዝና ፤
ሶምሶን ፦
መች ፡ አጣህ ፡ መሆኑን ፡ የኛ ፡ ወገን ፡ ጀግና ፦
(ወጊያ ፡ ይጀምራሉ) ፦
ቤንቮሊዎ ፦ (ይመጣል) ፦
ያላንድ ፡ ምክንያት ፡ በከንቱ ፡ ሳይቸገር ፡
አሁን ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ የናንተ ፡ ግርግር ፦
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ ስታልፉ ፡ በመንገድ ፡
ልማድ ፡ ሆነባችሁ ፡ ደርሶ ፡ ማንገራበድ ፦
ለማምጣት ፡ ነው ፡ እኮ ፡ በናንት ፡ የተነሣ ፡
በጌቶቻችሁ ፡ ላይ ፡ የዳኛ ፡ ወቀሣ ፦

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ቲባልት ፣ (ሻምላውን ፣ መዞ ፣ እያወዛወዘ ፣ መጣ) ።

እየው ፣ ቤንቮሊዎ ፣ ጥላውን ፣ ዘርግቶ ፤
ሞት ፣ የያዘ ፣ ሻምላ ፣ በራስህ ፣ ላይ ፣ መጥቶ ፣
ተመልከት ፣ ሲያንጥብብ ፣ እንደ ፣ ጀፌ ፣ አሞራ

ቤንቮሊዎ ።
መንፋትህ ፣ ይቅርና ፣ የማይረባ ፣ ጉራ ፣
እንገላግላቸው ፣ ይልቅ ፣ ተረዳድተን ።

ቲባልት ።
ልገጥምህ ፣ ነውና ፣ የመጣሁት ፣ አንተን ፣
ይልቅ ፣ ተሰናዳ ፣ ሻምላህን ፣ ምዘዘው ፤
ሳትዋጋ ፣ እንዳትሞት ፣ ቶሎ ፣ በጅህ ፣ ያዘው ።
ቲባልት ፣ ሻምላ ፣ መዞ ፣ እጁን ፣ ከዘረጋ ፣
ሊመለስ ፣ አይችልም ፣ ጠላቱን ፣ ሳይወጋ ፣
ወይም ፣ ደግሞ ፣ ራሱ ፣ ቀድሞ ፣ ካልወደቀ ።

ቤንቮሊዎ ።
ፉከራህ ፣ ከንቱ ፣ ነው ፣ በጣም ፣ የተናቀ ።
(ውጊያ ፣ ይገጥማሉ) ።
ሞንታግ ፣ (መጣ) ።
ወገኖቼ ፣ ሁሉ ፣ ድረሱ ፣ በፍጥነት ፤
እነሆ ፣ ሰዎቼን ፣ ፈጁዋቸው ፣ በድንገት ።

ለይፈን ፣ አቀብሉኝ ፣ በቶሎ ፣ ፍጠኑ ።
የሞንታግ ፣ ሚስት ፣ (ተከትላ ፣ መጣች) ።
እስቲ ፣ ባዶ ፣ እጅዎን ፣ አሁን ፣ ምን ፣ ሊሆኑ ?
ካፑሌ ፣ (መጣ) ።
ለይፈን ፣ አቀብለኝ ፣ ማነህ ፣ ቶሎ ፣ ድረስ ።
የካፑሌ ፣ ሚስት ፣ (ተከትላ ፣ መጣች) ።
ሽማግሌው ፣ አብዷል ፣ ድረሱልኝ ፣ በነፍስ ።
ወታደር ።
ይርጋ ፣ በየቦታው ፣ ሁሉም ፣ ጠቡን ፣ ትቶ
ልዑልነታቸው ፣ መጣ ፣ ተቆጥቶ ።
መስፍኑ ፣ (አገረ ገዥ) ።
መልካም ፣ ነው ፣ አየነው ፤ ይብቃ ፣ አሁን ፣ እርጉ ፤
ውጊያውን ፣ ትታችሁ ፣ ወደ ፣ እኔ ፣ ተጠጉ ፣
ካፑሌና ፣ ሞንታግ ፣ ልንገራችሁ ፣ ስሙ ፣
የናንተ ፣ አምባጓሮ ፣ በመደጋገሙ ፣
አልነቀል ፣ ብሎ ፣ የቂማችሁ ፣ መርዙ ፣
ሥር ፣ ስለ ፣ ሰደደ ፣ ጠንቃችሁ ፣ መዘዙ ፣
ደከመኝ ፣ ሰለቸኝ ፤ ታከተኝ ፣ በብዙ ።
ምንድንነው ፣ በውነቱ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ነገር ፤
ሰላም ፣ እያወኩ ፣ ዘለዓለም ፣ ማስቸገር ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ግርግር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጫጫታ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ አምባጓሮ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ቁቁታ ።
በናንተ ፡ ምክንያት ፡ ስንት ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ፤
ስንት ፡ ጊዜ ፡ አገሩ ፡ ጸጥታው ፡ ፈረሰ ፡
ስንት ፡ ጊዜ ፡ በጠብ ፡ ከተማው ፡ ታመሰ ?
አገሬ ፡ በናንተ ፡ — ንገሩኝ ፡ በሉ ፡ እኮ ፡
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይኖራል ፡ ታውኮ ?
እስቲ ፡ በማን ፡ አገር ፡ እስቲ ፡ በማን ፡ ዕድሜ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጥጋብ ፡ የሌለው ፡ ፍጻሜ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይታወቃል ፡ ታይቶ ፤
ማንም ፡ ሰው ፡ ይፍረደው ፡ ይህን ፡ ተመልክቶ ።
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቤ ፡ በሰይፍ ፡ ያልቃል ?
ትሰሙኝ ፡ እንደሆን ፡ እንግዴህ ፡ ይበቃል ።
በእውነቱ ፤ ዕወቁት ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡
በናንተ ፡ መካከል ፡ ቢሆን ፡ አምባጓሮ ፡
አዝኛለሁ ፡ አጥፊው ፡ በሞት ፡ እንዲቀጣ ፡
አለዚያም ፡ ጨርሶ ፡ ካገር ፡ እንዲወጣ ።
እንግዴህ ፡ ልባችሁ ፡ የኔን ፡ ፍቅር ፡ ቢሻ ፡
የዛሬው ፡ ጠባችሁ ፡ ይሁን ፡ መጨረሻ ፡
ስታዝኑ ፡ እንዳልሰማ ፡ በኋላ ፡ በፈራጅ ፡
ይህን ፡ ያሁን ፡ ቃሌን ፡ ቅጠሩት ፡ እንዳዋጅ ።

ትይንት ፡ ፪ ።

ካፑሌ ፡ ፓሪስ ፡ አንድ ፡ አሽከር ።

ካፑሌ ።

የመስፍኑ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ብርቱ ፡
ሞንታግና ፡ እኔ ፡ ሳስበው ፡ በውነቱ ፡
እንግዲህ ፡ ጠባችን ፡ እየቀዘቀዘ ፡
ይሄድ ፡ ይመስለኛል ፡ ባዋጅ ፡ ከተያዘ ።

ፓሪስ ።

ስማችሁ ፡ ዝናችሁ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡
እንዲሁም ፡ ክብራችሁ ፡ ከሁሉም ፡ የላቀ ፡
ሆኖ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ጊዜ ፡ ትጣልታችሁ ፡
በጣም ፡ ያሳዝናል ፡ በጠብ ፡ መኖራችሁ ፤
እረ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ደግሞስ ፡ የኔ ፡ ነገር ?
ልጅዎን ፡ ለማግባት ፡ ጠይቄዎት ፡ ነበር ።

ካፑሌ ።

ችላ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ታግሥ ፤
ጡልዬት ፡ ከፍ ፡ ትበል ፤ ለመታጨት ፡ ትድረስ ፡
አሁን ፡ አእምሮዋ ፡ ዕውቀቷም ፡ አልጠና ፤
ከልጅነት ፡ ዕድሜ ፡ አልወጣችም ፡ ገና ፡
እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ተላመዳት ፤
ትወቅህ ፡ ዕወቃት ፡ ትውደድህ ፡ ውደዳት ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡
ትልቅ ፡ ግብጣ ፡ አድርጌ ፡ በቤቴ ፡ ጨዋታ ፡
ደስታም ፡ ይሆናል ፡ አንተም ፡ እንዳትቀር ፤
ናና ፡ ከሷ ፡ ጋራ ፡ ቀርበህ ፡ ተነጋገር ።
በጣም ፡ ተዋወቁ ፤ ና ፡ እባክህ ፡ አንተ ፡ አሽከር ፡
በዚህ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ ስማቸው ፡
የሚነበበውን ፡ ቶሎ ፡ ፈልጋቸው ፤
ውጣ ፡ ከከተማ ፡ ዙር ፡ በየመንገዱ ፤
ታገኛቸዋለህ ፡ በድንገት ፡ ሲሄዱ ።
አደራ ፡ በላቸው ፡ ማታ ፡ እንዲመጡ ፤
ከግብጣዬ ፡ ቀርበው ፡ በልተው ፡ እንዲጠጡ ፡
እንዲጫወቱልኝ ፡ ፈቃዴ ፡ መሆኑን ፡
ፈጥነህ ፡ ንገራቸው ፤ ቶሎ ፡ ሂድ ፡ አሁኑን ።

አሽከር ፡ (ወረቀት ፡ ተቀብሎ ፡ ሄደ) ።

(ሮሜዎና ፡ ቤንቮሊዎ) ።

ሮሜዎ ።

የነካፑሌ ፡ አሽከር ፡ አንድ ፡ ወረቀት ፡ ይዞ ፡
መንገድ ፡ አገኘሁት ፡ ሲመለከት ፡ ፈዞ ፡
እሱስ ፡ ለካ ፡ ማንበብ ፡ የማያውቅ ፡ ኖሮ ፡
የሚያነብለት ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ተቸግሮ ፡
እኔን ፡ ቢለምነኝ ፡ እኔም ፡ የነሱ ፡ አሽከር ፡
ሳላውቅ ፡ መሆኑን ፡ ባለመጠራጠር ፡
ምንም ፡ ሳልተረጉም ፡ በደግም ፡ በመጥፎ ፡

የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ አየሁኝ ፡ ተጽፎ ።
አንብቤ ፡ ስጨርስ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡
በወረቀቱ ፡ ላይ ፡ ስማቸው ፡ የሞላ ፡
ምንድናቸው ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ብጠይቀው ፡
ዛሬ ፡ ካፑሌ ፡ ቤት ፡ ማታ ፡ ራት ፡ ተጋብዘው ፡
የሚመጡ ፡ ናቸው ፡ አለና ፡ ነገረኝ ።

ቤንቮሊዎ ።

እኔም ፡ ሰምቻለሁ ፡ እንኳን ፡ አስታወስከኝ ፡
እርግጥ ፡ በነሱ ፡ ቤት ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡
ትልቅ ፡ ግብጣ ፡ ሆኖ ፡ የዳንስም ፡ ጨዋታ ፡
ብዙ ፡ ሰው ፡ ተጠርቷል ፤ ሰውም ፡ የሚሄደው ፡
ፊቱን ፡ በመሰውር ፡ እየሸፈነ ፡ ነው ።
ስለዚህ ፡ አያውቅም ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ለይቶ ፤
አንተና ፡ እኔ ፡ ብንሄድ ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ ከቶ ፡
አያውቀንምና ፡ እንሂድ ፡ ሳንፈራ ፤
እዚያም ፡ ከሮዛሊን ፡ ከንተ ፡ እጮኛ ፡ ጋራ ፡
እንገናኛለን ፡ ተጠርታለችና ።

ሮሜዎ ።

እውነት ፡ ቤንቮሊዎ ፡ አስቢሃል ፡ ደኅና ፡
በል ፡ እንግዲህ ፡ ፍጠን ፡ ቶሎ ፡ እንሰናዳ ፤
እውነትም ፡ ባስበው ፡ የኔን ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡
ካየኋት ፡ ቁይታል ፡ ወር ፡ ሆኖኛል ፡ ይኸው ፤
በጣም ፡ ጥሩ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ያመጣኸው ።

ትይንት ፡ ፫ ።

(ሮሜዎና ፡ ሜርኩቲዎ) ።

ሜርኩቲዎ ።

ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ እንዲህ ፡ በጨለማ ?

ሮሜዎ ።

ዐይንህ ፡ እንዳላየ ፡ ጉሮህ ፡ እንዳልሰማ ፡
ሆነህ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ እለፍ ፡ በጐዳና ፤
ማንም ፡ ሰው ፡ እንዲያውቀኝ ፡ አልፈልግምና ።

ሜርኩቲዎ ።

ባሁን ፡ ሰዓት ፡ ስትሄድ ፡ ብቻህን ፡ አይቼ ፡
ለመቅረት ፡ አልችልም ፡ ካንተ ፡ ተለይቼ ።

ሮሜዎ ።

ልብህ ፡ እንዳይሠጋ ፡ ሆድህ ፡ እንዳይፈራ ፡
ምስጢሬን ፡ ልንገርህ ፡ የኔ ፡ ባልንጀራ ፤
ዛሬ ፡ ካፑሌ ፡ ቤት ፡ ትልቅ ፡ ግብጥ ፡ ሆኖ ፡
ሰዉ ፡ በመሰውር ፡ ፊቱን ፡ ተሸፍኖ ፡
ዳንስ ፡ ይጫወት ፡ ነበር ፡ ከቤንቮሊዎ ፡ ጋራ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያየን ፡ ገባን ፡ ሳንፈራ ፡
የቀድሞ ፡ እጮኛዬን ፡ ሮዛሊንን ፡ ልሻ ፡
ሂጂልህ ፡ ነበረ ፤ ኋላም ፡ መጨረሻ ፡
በጣም ፡ ያስገርማል ፡ ይደንቃል ፡ ወዳጄ ፤

የነካፑሌን ፡ ልጅ ፡ ጉቦልዬትን ፡ አይቼ ፡
በውበቷ ፡ ብርሃን ፡ መጣሁ ፡ ተረትቼ ፡
ግብጥው ፡ ስላለቀ ፡ ሰዉ ፡ ተበትኖ ፡
ብቅ ፡ ብትልልኝ ፡ ምናልባት ፡ ልቧ ፡ አዝኖ ፡
ይኸው ፡ መሄዴ ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ተመልሼ ፤
እመጣለሁ ፡ አሁን ፡ በፍጥነት ፡ ደርሼ ።

ሜርኩቲዎ ።

እንዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ ደፍረህ ፡ ከነሱ ፡ ቤት ?
አንድ ፡ ሰው ፡ ከነሱ ፡ ቢያገኝህ ፡ በድንገት ፡
ዕወቅ ፡ ይገድልሃል ፡ አብደሃል ፡ ፈጽሞ ፤
በራቸው ፡ ይዘጋል ፡ ለመግባትስ ፡ ደግሞ ፡
እንዴት ፡ ትችላለህ ? ይቅርብህ ፡ ተመለስ ።

ሮሜዎ ።

ማ ፡ ሊያየው ፡ ይችላል ፡ ሰው ፡ ጨለማ ፡ ሲለብስ ?
አጥሩ ፡ ቢረዝም ፡ በሩ ፡ ቢጠነክር ፡
ጠላትም ፡ አድፍጦ ፡ ሊገድለው ፡ ቢሞክር ፡
ሰው ፡ መውደድ ፡ አድሮበት ፡ ፍቅር ፡ ካሰከረው ፡
ምንም ፡ አያግደው ፤ ምንም ፡ አይበግረው ።
ባገኛት ፡ ቢቀናኝ ፡ ቶሎ ፡ ልምጣ ፡ ሂጂ ፤
ሜርኩቲዎ ፡ ደኅና ፡ እደር ፡ አትሥጋ ፡ ወዳጄ ።

ሜርኩቲዎ ።

ሮሚዎ ።

የወጣ ፡ ቃል ፡ የለም ፡ አፋችን ፡ ተናግሮ ፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ ተያይተን ፡ ባይን ፡ ስንገናኝ ፡
ለኔ ፡ መፈጠሯ ፡ ለልቤ ፡ ተሰማኝ ።
እሷም ፡ እንደዚሁ ፡ በውስጣዊ ፡ ልቧ ፡
አይጠረጠርም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ማሰቧ ።
እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ለብልኀ ፡ አስተዋይ ፡
እነሆ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ፍቅር ፡ ጠባይ ፡
እፍ ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ታስሮ ፡ በዝምታ ፡
ልብ ፡ ከልብ ፡ ጋራ ፡ ያደርጋል ፡ ጨዋታ ፡
ተወኝ ፡ ልሂድበት ፡ እንግዲህ ፡ ደኅና ፡ እደር ፤
እኔን ፡ አየሁ ፡ ብለህ ፡ ለሰው ፡ አትናገር ።

(ሮሜዎ ፡ ሄደ) ።

ሁለተኛ ፡ አክት ።

ትይንት ፡ ፩ ።

ሮሚዎ ፡ (ከጉቦልዬት ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ማታ ፡ በጨረቃ ፡ ከውጭ ፡ ሆኖ) ።

የሚያፈቅራትን ፡ ልጅ ፡ የሚጠብቅ ፡ ወጣት ፡
ረዝሞ ፡ ይታየዋል ፡ ደቂቃ ፡ እንደ ፡ ሰዓት ፤
ሰዓቱም ፡ እንደ ፡ ቀን ፡ ቀኑም ፡ እንደ ፡ ዘመን ፡
እኔስ ፡ መሞቴ ፡ ነው ፡ በፍቅሯ ፡ ስመመን ።

(ጉቦልዬት ፡ መስኮት ፡ ከፍታ ፡ ብቅ ፡ አለች) ።

አሳቤ ፡ ተነሣ ፡ ተከፈቱ ፡ ዐይኖቼ ፤

ደሜ ፡ ተንቀሳቀስ ፡ ተፍታቱ ፡ ሥሮቼ ።
ልቤ ፡ ተስፋ ፡ ሲቈርጥ ፡ የማትወጣ ፡ መስሎት ፡
ያቻት ፡ የኔ ፡ ጮራ ፡ ብቅ ፡ አለች ፡ በመስኮት ።
ልቤ ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ መንፈሴ ፡ ተሸበር ፤
የጉቦልዬትን ፡ ውበት ፡ እንግዴህ ፡ ልናገር ፤
መስኮቷ ፡ ምሥራቅ ፡ ነው ፡ ፊቷ ፡ የጧት ፡ ጀንበር ፡
ብርሃኗ ፡ የለውም ፡ የሚያግደው ፡ ድንበር ።
ሰላም ፡ ላንቺ ፡ ይሁን ፡ ትልሻለች ፡ ነፍሴ ፤
ጮራሽ ፡ አለበሰኝ ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሴ ፡
እኔ ፡ እንደምወድሽ ፡ አታውቂውም ፡ ፍቅሬ ፤
አላጫወትኩሽም ፡ ባፌ ፡ ተናግሬ ፡
ካየሁሽ ፡ ይበቃል ፡ ቆሜ ፡ ከሩቅ ፡ ቦታ ፤
ያጠግበኛልና ፡ ያይኖችሽ ፡ ጨዋታ ፡
ዐይንሽ ፡ የሚመስለው ፡ የርግብ ፡ የሚዳቋ ፡
እኔ ፡ የማልጠግበው ፡ አለው ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡
ዐይኔ ፡ እንደ ፡ ቀለበት ፡ ጣትሽ ፡ ላይ ፡ ተሰካ ፤
እዩት ፡ በቀኝ ፡ እጅዋ ፡ ጉንጮቿን ፡ ስትነካ ፡
የእጅ ፡ ሹራብ ፡ ሆኜ ፡ ገላሽን ፡ ባለብሰው ፡
ፊትሽን ፡ ጉንጭሽን ፡ ዠልዬት ፡ ብዳብሰው ፡
ደስታ ፡ ሕይወቴን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ባደሰው !

ዠልዬት ።

ሮሚዎ ፡ ሮሚዎ ፡ የልቤ ፡ ወለላ ፡

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

እባክህ ፣ ለውጠው ፣ ስምህን ፣ በሌላ ፣
ፍቅራችንን ፣ ገደል ፣ ሆኖ ፣ የሚያግደው ፣
ቂም ፣ በቀል ፣ ስላለ ፣ ጎጢአት ፣ የወለደው ፣
እኔም ፣ ዘሬን ፣ ልካድ ፤ አንተም ፣ ዘርህን ፣ ካደው ።
የኔ ፣ አባት ፣ ላንተ ፣ አባት ፤ የናንተ ፣ ዘር ፣ ለኛ ፣
መሆኑን ፣ አትርሳ ፣ ባላንጣ ፣ ደመኛ ።

ሮሜዎ ።

ይህን ፣ አልዘነጋም ፣ ገ፱ልዬት ፣ ይሰማኛል ፤
ነገር ፣ ግን ፣ ምን ፣ በቀል ፣ ምንስ ፣ ቂም ፣ ይገኛል ፣
ምንስ ፣ ጠላትነት ፣ ከታስቢው ፣ በሰው ፣
የፍቅር ፣ ማዕበል ፣ የማይደመሰሰው ፣
የኔ ፣ አባት ፣ ላንች ፣ አባት ፣ ቢሆንም ፣ ባላንጣ ፣
እኔ ፣ እወድሻለሁ ፣ ነፍሴ ፣ እስክትወጣ ።

ገ፱ልዬት ።

ሮሜዎ ፣ እውነት ፣ ነው ፣ ዕድሜ ፣ ለሰው ፣ ክፋት ፤
በፍቅር ፣ መካከል ፣ አለ ፣ ብዙ ፣ ዕንቅፋት ፣
የጌታ ፣ ልጅ ፣ ድኻን ፣ አይውደድ ፣ ይላሉ ፤
ብዙዎች ፣ ልጃቸውን ፣ በዚህ ፣ ይክዳሉ ፣
ዳሩ ፣ ግን ፣ የሰው ፣ ልብ ፣ በሰው ፣ አይመራም ፤
የፍቅራችን ፣ መብራት ፣ በትእዛዝ ፣ አይበራም ፣
ልጅ ፣ ካባት ፣ አጣልቶ ፣ ብዙ ፣ ሰው ፣ የጐዳ ፣
ይህን ፣ የመሰለ ፣ አለብን ፣ ብዙ ፣ ዕዳ ።

ቂም ፣ በቀል ፣ የሚሉት ፣ መከረኛ ፣ ጣጣ ፣
ካያት ፣ ካባት ፣ ከናት ፣ ከዘር ፣ የሚመጣ ፣
እኛ ፣ እንዳንፋቀር ፣ ማንንም ፣ ሳንፈራ ፣
ሆኖብን ፣ ታግኝ ፣ የፍቅር ፣ ደንቃራ ፤
ዳሩ ፣ ግን ፣ ይህ ፣ እክል ፣ ለሰው ፣ የማይራራ ፣
እጅ ፣ እግር ፣ የሌለው ፣ እኛ ፣ የማናውቀው ፣
አይችልም ፣ ልብህን ፣ ከልቤ ፣ ሊያርቀው ፣
ሞንታግስ ፣ ምንድነው ፣ ሬደል ፣ አይደለም ፣ ወይ ?
እኛን ፣ ሊለያየን ፣ አይችልም ፣ ፍቅሬ ፣ ሆይ ፣
ስሚን ፣ ብንለውጠው ፣ እስቲ ፣ ጽጌ ፣ ረዳ ፣
ይችላል ፣ ወይ ፣ መልኳ ፣ ሊለወጥ ፣ ሊጐዳ ፣
አይችልም ፣ ውሸት ፣ ነው ፣ በማዛ ፣ በውበት ፤
ጽጌ ፣ ረዳ ፣ ያው ፣ ነች ፣ አይነካትም ፣ ጉድለት ፣
ሮሜዎም ፣ እንዲሁ ፣ ስሙን ፣ ቢለውጠው ፣
ባሕርዩን ፣ አይችልም ፣ ከቶ ፣ ሊያናውጠው ፣
ተወዳጅነቱ ፣ እስከ ፣ ዘላለሙ ፣
በጠባይ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ አይደለም ፣ በስሙ ።
ያንተ ፣ ስም ፣ ቢለወጥ ፣ ዋጋህን ፣ አትርሳ ፣
እኔን ፣ ማግኘትህ ፣ ነው ፣ ያንተ ፣ ትልቅ ፣ ካሳ ።

ሮሜዎ ።

በመካከላችን ፣ የተገኘው ፣ እክል ፣
ስሜ ፣ ከሆነማ ፣ የኛ ፣ መሰናክል ፣

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

አጭር ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡ ዠልዴት ፡ የኔ ፡ ሹና
አንቺን ፡ ደስ ፡ እንዲልሽ ፡ ሰፍቅሬ ፡ ዋስትና ፡
ላደርገው ፡ የማልፈቅድ ፡ ነገር ፡ የለምና ፤
ቢያስፈልግ ፡ ልነግ ፡ ዳግም ፡ ከርስትና ፡
ሲሰማ ፡ እንዳይቀፈው ፡ ስሜን ፡ ያንቺ ፡ ገሮ ፡
ሮሜዎ ፡ አይደለሁም ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፤
ፍቅርሽና ፡ ፍቅሬ ፡ በዘር ፡ ቂም ፡ አይፈርስም ፤
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ይለወጥ ፡ የኔ ፡ ስም ።

ዠልዴት ።

ማነህ ፡ አንተ ፡ ከዚህ ፡ የቆምከው ፡ ከደጇ ?
ባይኔ ፡ የማላይህ ፡ የማልነካህ ፡ በእጇ ፡
ጨለማ ፡ የለበሰክ ፡ የፍቅር ፡ ማዕበል ፡
የልቤ ፡ ነበልባል ፡ ስምህን ፡ ማ ፡ ልበል?

ሮሜዎ ።

ባንቺ ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ የሚኖር ፡ ከርታታ ፡
የቀን ፡ ብርሃን ፡ ሸሽቶ ፡ የመጣ ፡ በማታ ፡
አንቺን ፡ በመውደዱ ፡ ከራሱ ፡ አብልጠ ፡
ያለ ፡ ስም ፡ የቀረ ፡ ስሙንም ፡ ለውጠ ።

ዠልዴት ።

ያጥራችን ፡ ግንቡ ፡ ትልቅ ፡ አይበገር ፤
እንዴት ፡ ነው ፡ የገባህ ፡ እንተ ፡ ሳትቸገር ?

መች ፡ አጥር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ትልቁን ፡ ጉድ ፡ ትቼ ፡
ደግሞም ፡ ይገድሉሃል ፡ ቢያዩህ ፡ ዘመዶቼ ።

ሮሜዎ ።

ፍቅር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ጉልበቴና ፡ ክንፌ ፡
ግንቡ ፡ ሳያግደኝ ፡ መጣሁኝ ፡ አልፌ ፡
ጨለማም ፡ አጥርም ፡ ሳያሰናክለኝ ፡
እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የሚከለክለኝ ?

ዠልዴት ።

ታዲያ ፡ እዚህ ፡ ቢያገኙህ፡ይገድሉህ ፡ የለም ፡ ወይ?

ሮሜዎ ።

ለኔ ፡ ምንም ፡ አይዶል ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፍቅሬ ፡ ሆይ ፡
አጥር ፡ እጥሳለሁ ፡ ጦርም ፡ አያግደኝ ፤
ብርሃን ፡ የሞላበት ፡ እኔን ፡ ያሳበደኝ ፡
ጦሩስ ፡ ያንቺ ፡ ዐይን ፡ ነው ፡ የኔን ፡ ልብ ፡ የወጋ ፡
በፍቅር ፡ አይተሸኝ ፡ መንፈሴ ፡ ቢረጋ ፤
ምንም ፡ ባላሠጋኝ ፡ የቀረው ፡ አደጋ ።

ዠልዴት ።

ሳይህ ፡ በኛ ፡ ግቢ ፡ ይሰማኛል ፡ ሥጋት ፤
በሻምላ ፡ ወይ ፡ በጦር ፡ ልብህን ፡ ለመውጋት ፡
ስለማይመለስ ፡ ወገኔ ፡ አንተን ፡ አይቶ ፡
ቢያዩህ ፡ አልፈልግም ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ከቶ ።

ሮሚዎ ።

ዡልዬት ፣ አታስቢ ፣ አትሥጊ ፣ ለነፍሴ ፤
ወዳንቺ ፣ ስመጣ ፣ ጨለማ ፣ ነው ፣ ልብሴ ፣
ትወጂኝ ፣ አትወጂኝ ፣ ባለመለየቴ ፣
ይህ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ ለኔ ፣ ሕመሜና ፣ ሞቴ ፤
ስለዚህ ፣ ንገሪኝ ፣ ምንም ፣ አትደብቂ ፤
ሌላውን ፣ አደጋ ፣ ግድ ፣ የለሽም ፣ ናቂ ።
አትወጂኝ ፣ እንደሆን ፣ ሰፊ ፣ ነው ፣ ሐዘኔ ፤
በዚህ ፣ ሕመም ፣ ብቻ ፣ እሞታለሁ ፣ እኔ ።

ዡልዬት ።

እፍረት ፣ እንዳይዘኝ ፣ ጨለማ ፣ ለብሼ ፣
እንግዲያው ፣ ልንገርህ ፣ አሳቤን ፣ ጨርሼ ፣
እፍረት ፣ ደኅና፣ሰንብት፣መግደርደር ፣ ደኅና ፣ ሁን ፤
ሮሚዎ ፣ አንድ ፣ ነገር ፣ ልጠይቅህ ፣ አሁን ፣
ከፊቴ ፣ የቆምከው ፣ ወዳጄ ፣ ፍቅሬ ፣ ሆይ ፣
ካንጀትህ ፣ ከልብህ ፣ ትወደኛለህ ፣ ወይ ?
ማንንም ፣ አልወድም ፣ ብለህ ፣ ካንቺ ፣ ሌላ ፣
ትናገራለህ ፣ ወይ ፣ አሁን ፣ በመሐላ ?
እኔ ፣ ባንቱ ፣ ፍቅር ፣ በጣም ፣ ተጨንቄ ፣
ስለዓ"ወድህ ፣ ነው ፣ ይህን ፣ መጠየቄ ፣
እኔስ ፣ የት ፣ ዐውቃለሁ ፣ ትወደኝ ፣ አትወደኝ ፤
ይህንን ፣ ከድፍረት ፣ ቈጥረህ ፣ አትፍረደኝ ።

ካፌ ፣ በመውጣቱ ፣ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ቃል ፣
እንዳትገምተው ፣ ጠባዬን ፣ በቀላል ፣
ከልብህ ፣ እንደሆን ፣ መንፈሴ ፣ ይረጋል ፤
መሠረት ፣ ከሌለው ፣ ፍቅር ፣ ምን ፣ ያደርጋል ።

ሮሚዎ ።

እንደ ፣ አልማዝ ፣ እንደ ፣ ዕንቊ ፣ ውበታ ፣ በጠራ፣
በመስክ ፣ በሸለቆ ፣ በዱር ፣ በተራራ ፣
ብርሃን ፣ በዘረጋች ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ ፈንጥቃ ፣
እምልልሻለሁ ፣ በዚች ፣ በጨረቃ ።

ዡልዬት ።

ተው ፣ አስብ ፣ ተመልከት ፣ አንድ ፣ ነገር ፣ ፍራ ፤
ፍቅርህ ፣ ተለዋዋጭ ፣ እንዳይሆን ፣ አደራ ፣
በጨረቃ ፣ አትማል ፣ በዚች ፣ ወረተኛ ፤
ሁሉ ፣ ቀን ፣ አትገኝ ፣ ዘወትር ፣ መንገደኛ ፣
ወር ፣ አይሞላምና ፣ ይህ ፣ የሷ ፣ ግሥግሳ ፤
ምን ፣ ጊዜም ፣ ያስታውሰው ፣ ልቡናህ ፣ አይርሳ ፣
አለች ፣ ስንል ፣ ኰርተን ፣ በብርሃን ፣ ሞገሷ ፣
ለጨለማ ፣ ትታን ፣ ትጠፋለች ፣ እሷ ።

ሮሚዎ ።

በምን ፣ ልማልልሽ ፣ ንገሪኝ ፣ ዡልዬት ፤

ገቦልዬት ።

ይቅርብኝ ፡ አትማል ፡በውነትም ፡ በውሸት ፡
ደግሞም ፡ ልማል ፡ ብለህ ፡ አሳብህ ፡ ከጸና ፡
ምን ፡ ጊዜም ፡ ጣዖቱ ፡ ፍቅሬ ፡ አንተ ፡ ነህና ፤
በራስህ ፡ ማልልኝ ፡ የኔ ፡ ሀለንተና ።

ሮሜዎ ።

እንግዲያውስ ፡ ስሚ ፡ እኔ ፡ አንቺን ፡ መውደዴ ፡

ገቦልዬት ፤

ይቅር ፡ በታ ፡ አትማል ፤ ተናወጠ ፡ ሆዴ ፡
ፈጥነህ ፡ ብትምልልኝ ፡ አሁን ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡
ምንም ፡ አይሰማኝ ፡ ለልቤ ፡ ደስታ ፡
እንደዚህ ፡ በድንገት ፡ እንዲህ ፡ በችኰላ ፡
እንደዚህ ፡ በቶሎ ፡ የሆነ ፡ መሐላ ፡
መሠረት ፡ የለውም ፡ ይጠፋል ፡ ባንዳፍታ ፤
አላፊ ፡ ነፋስ ፡ ነው ፡ የሰማይ ፡ ብልጭታ ።
የፍቅሩ ፡ ቡቃያ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡
ለምልሞ ፡ ይጠንክር ፡ በልባችን ፡ አድሮ ፡
እኛም ፡ እዚያ ፡ ድረስ ፡ ሆነን ፡ ትዕግሥተኛ ፡
ወደየቤታችን ፡ ገብተን ፡ እንተኛ ።

ሮሚዎ ።

ልትሄጂ ፡ ነወይ ፡ ትተሽኝ ፡ በከንቱ ?

ገቦልዬት ።

ይበቃል ፡ ለዛሬ ፡ መሸብን ፡ ሰዓቱ ።

ሮሜዎ ።

ስጭኝ ፡ የሚያጠግብ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ የበቃ ፤

ገቦልዬት ።

አንተ ፡ ሳትጠይቅ ፡ በፊት ፡ ገቦልዬት ፡ ዐውቃ ፡
ሰጥታህ ፡ ወስደኸዋል ፡ የፍቅሯን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፤
የተረፈው ፡ ይደር ፡ ለነገ ፡ እንዲረዳን ።

ሮሚዎ ።

መልሰሽ ፡ ወስደሺው ፡ መልካሙን ፡ ስጦታ ፡

ገቦልዬት ።

ቃሌን ፡ እሰጣለሁ ፡ ላንተ ፡ በችሮታ
የልቤ ፡ ደግነት ፡ ባሕር ፡ ነው ፡ ስፋቱ ፤
ፍቅሬም ፡ እንደዚሁ ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፡ ርቅቱ ፡
መልካም ፡ ጠባዮቼ ፡ እነዚህ ፡ ሀለቱ ፡
ሰፊ ፡ ሀብት ፡ ናቸው ፡ ከሁሉም ፡ የላቁ ፤
ብሰጥህ ፡ ብሰጥህ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አያልቁ ።

(ሞግዚቷ ፡ ጠራቻት) ።

ጠሩኝ ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ፡ በል ፡ ሄድኩኝ ፡ ደጎና ፡ እደር ።
ሞግዚቴ ፡ እሺ ፡ መጣሁ ፤ ሮሚዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡
አለ ፡ የምነግርህ ፡ አትሂድ ፡ ጠብቀኝ ፤ (ወደ ፡ ቤትነባች) ።

ሮሚዎ ፡ (ብቻውን) ።

የዛሬው ፡ ደስታ ፡ ምንኛ ፡ ደነቀኝ ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ሕልም ፡ ነው ፡ ራእይ ፡ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ቅዠት ፤
አልችልም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ልደርስበት ፤
ፀሓዬ ፡ ጠለቀች ፡ ገባች ፡ ወደ ፡ ቤታ ።
አሁን ፡ ተመልሳ ፡ ዳግም ፡ በመስኮቷ ፡
ብቅ ፡ እስክትል ፡ ድረስ ፡ ሆነብኝ ፡ ጨለማ ፡
ይሸው ፡ ተመለሰ ፡ የብርሃኗ ፡ ግርማ ።

ዡልዬት ፡ (ተመልሳ ፡ መጣች) ።

ሮሚዎ ፡ ልንገርህ ፡ የመጨረሻ ፡ ቃል ፤
እንደምታፈቅረኝ ፡ ዐወቅሁት ፡ ይበቃል ፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ ፍቅራችን ፡ መሠረት ፡ አግኝቶ ፡
በተከሊል ፡ ጋብቻ ፡ እንዲፈጸም ፡ ጸንቶ ፡
ትፈቅድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እልካለሁና ፡
ነገ ፡ ሰው ፡ ወዳንተ ፡ ጕዳዩን ፡ ካጠና ፡
ካሰበ ፡ በኋላ ፡ መንፈስህ ፡ መርምሮ ፡
የተከሊሉ ፡ ሰዓት ፡ ይሁን ፡ በቀጠሮ ።
ወስነህ ፡ ላክብኝ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡
ማመንታት ፡ ሳይኖረው ፡ ልቤ ፡ ሳይገነግን ፡
ችግር ፡ ሳያግደኝ ፡ አደጋና ፡ ሞትም ፡
አንተን ፡ ተከትዬ ፡ እሄዳለሁ ፡ የትም ።
ነገር ፡ ግን ፡ ያንተ ፡ አሳብ ፡ ከሌለው ፡ ንጽሕና ፡
የማይሄድ ፡ ከሆነ ፡ እንደኔ ፡ ኅሊና ፡
አትምጣ፡ ወደኔ ፡ አትድከም ፡ በከንቱ ፤

እንግዴህ ፡ ደኅና ፡ ሁን ፡ አለፈ ፡ ሰዓቱ ፡
ግባ ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ ፍጠን ፡ አታመንታ ፤
ሊነጋ ፡ ነውና ፡ ይታያል ፡ ወገግታ ፡
ጨለማ ፡ ለቀቀ ፡ ብርሃን ፡ ተከፈተ ፡
ስንት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ሰው ፡ ልላክ ፡ ወዳንተ ?

ሮሚዎ ።

ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ መልክተኛሽ ፡ ይምጣ ፡

ዡልዬት ።

እንግዴህ ፡ ደኅና ፡ ሁን ፡ ፀሓይ ፡ ሳትወጣ ፡
እንግባ ፡ ቤታችን ። (ሄደች) ።

ሮሚዎ ።

ዡልዬት ፡ ደኅና ፡ ሁኚ ፤
ልቤ ፡ ካንቺ ፡ ጋራ ፡ መቅረቱን ፡ እመኚ ። (ሄደ) ።

ትይንት ፡ ፪ ።

ሮሚዎና ፡ አባ ፡ ሎራ ፡ (ባባ ፡ ሎራ ፡ ቤት) ።

ሮሚዎ ።

እንደምን ፡ አድረዋል ፡ አባቴ ፡ አባ ፡ ሎራ ?

አባ ፡ ሎራ ።

ከምሥራቅ ፡ ሳይቷይ ፡ የፀሓይዋ ፡ ጮራ ፡
ማነህ ፡ በማለዳ ፡ የመጣህ ፡ ከቤቴ ?
በጣፋጩ ፡ ድምፅህ ፡ የምትል ፡ አባቴ ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ኧረግ ! አንተ ፡ ነህ ፡ ወይ ፡ ሮሜዎ ፡ ጐበዙ ፤
ዐይኔ ፡ ደከመና ፡ አላየም ፡ በብዙ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ አድረሃል ፡ የምወድህ ፡ ልጄ ፤
ዐይንህ ፡ በጣም ፡ ቀልቷል ፡ ምን ፡ ነካህ ፡ ወዳጀ
አንድ ፡ ሰው ፡ እንደዚህ ፡ በጧት ፡ የሚነሣ ፡
ነገር ፡ ሰ የገኘው ፡ ነው ፡ እንቅልፍ ፡ የሚነሳ ፡
አሳብ ፡ የምንለው ፡ የሰላም ፡ መጋኛ ፡
መንፈሱን ፡ ሰፍሮበት ፡ እንቅልፍ ፡ የማይተኛ ፡
ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ወጣት ፡ ግን ፡ በውኑ ፡
ከእንግዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነጻ ፡ በመሆኑ ፡
ተኝቶ ፡ ያነጋል ፡ እንቅልፉን ፡ በሰላም ፤
ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ዐይንህ ፡ በደኅናው ፡ አልቀላም ፡
ሮሜዎ ፡ ምን ፡ ሆኖ ፡ ሳይተኛ ፡ አደረ ?
አለመተኛቱን ፡ ዐይኑ ፡ መሰከረ ።

ሮሜዎ ።

እውነት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አርፌያለሁ ፡ በጣም

አባ ፡ ሎራ ።

ብታርፍማ ፡ ኖሮ ፡ በሌሊት ፡ አትመጣም ፡
ንገረኝ ፡ አትደብቅ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያደርከው ?

ሮሜዎ ።

ድል ፡ አድራጊው ፡ ፍቅሯ ፡ መንፈሴን ፡ ማረከው
አባቴ ፡ እጅዎ ፡ ተክሊሌን ፡ ይባርከው ።

አባ ፡ ሎራ ።

ያሰብከውን ፡ ነገር ፡ ንገረኝ ፡ አትፍራ ፤
ከመልካሟ ፡ እጮኛህ ፡ ከሮዛሊን ፡ ጋራ ፡
የተክሊል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ዛሬ ፡ ልትሞላ ፡
የመጣህ ፡ መሰለኝ ፡ ሳስበው ፡ በመላ ።

ሮሜዎ ።

ሮዛሊን ፡ ቀርታለች ፡ አያንሷት ፡ አባቴ ፡
ትናንትና ፡ ማታ ፡ ተመታ ፡ ደረቴ ፡
ባዲስ ፡ የፍቅር ፡ ጦር ፡ በሰላ ፡ ጐራዴ ፤
ከመውደዷ ፡ ጋራ ፡ ገጠመ ፡ መውደዴ ፡
ስሜታችን ፡ እኩል ፡ ፍቅራችን ፡ የጋራ ፡
ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ አባቴ ፡ አባ ፡ ሎራ ፡
ተክሊሉን ፡ ይሙሉልን ፡ በሥልጣንዎ ፡ ባርከው ፡
እኛ ፡ ቂም ፡ የለንም ፤

አባ ፡ ሎራ ።

መንፈሴን ፡ አወከው
ምን ፡ አመጣህብኝ ፡ የማላውቀው ፡ ምስጢር ፡
መላ ፡ መትቶ ፡ ያውቃል ፡ ብለህ ፡ አትጠርጥር ፤
አልገባኝምና ፡ ያሁኑ ፡ ንግግር ።
ይህን ፡ እንቆቅልሽ ፡ እንደ ፡ ሾላ ፡ ድፍን ፡
ትተህ ፡ ግለጥልኝ ፡ ነገሩን ፡ ሳትሸፍን ።

ሮሜዎ ።

አባቴ ፡ አልደብቅም ፡ ሁሉንም ፡ ገልጬ ፡

ለርስዎ ፣ ልነግር ፣ ነው ፣ የመጣሁ ፣ ሮጬ ፣
የነካፑሌን ፣ ልጅ ፣ ገዖልዬትን ፣ ወድጄ ፤
ራሴ ፣ እስቲጠፋ ፣ በፍቅሯ ፣ አብጄ ፣
እሷም ፣ በጣም ፣ ወዳኝ ፣ አድርገን ፣ መሐላ ፣
ተስማምተን ፣ ተዋደን ፣ ከቄረጥን ፣ በኋላ ፣
አሁን ፣ የሚቀረን ፣ ተክሊል ፣ የሚሞላ ፣
ካህን ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ የሚሰጥ ፣ ቡራኬ ፣
ከሷ ፣ ጋር ፣ መጥቼ ፣ ፊትዎ ፣ ተንበርክኬ ፣
ሞልተው ፣ ያሰናብቱን ፣ የተክሊሉን ፣ ሥርዐት ፣
ሰዓቱን ፣ ይንገሩኝ ፣ መቼ ፣ እንደምጠራት ።

አባ ፣ ሎራ ።

አይጣል ፣ ነው ፣ እናንተ ፣ የወጣቶች ፣ ወረት ፤
ፍቅራቸው ፣ ታላቸው ፣ የለውም ፣ መሠረት ፣
የቀድሞ ፣ እጮኛህ ፣ ሮዛሊን ፣ ተረስታ ፣
ሌላ ፣ ልጅ ፣ አግኝተህ ፣ አሁን ፣ ትናንት ፣ ማታ ፣
እንዴት ፣ ተለወጠ ፣ አሳብህ ፣ ባንድ ፣ አፍታ ፣
በሮዛሊን ፣ ፍቅር ፣ ልብህ ፣ እንዲያ ፣ ግሎ ፣
ዘላለም ፣ የማይበርድ ፣ እውነተኛ ፣ መስሎ ፣
ታሟውተኝ ፣ ነበር ፤ አሁን ፣ ይኸውና ፣
ያ ፣ ሁሉ ፣ መውደድህ ፣ ከመቼው ፣ ቀረና ፣
መጣህ ፣ ባዲስ ፣ ፍቅር ፣ ልብህ ፣ ተብረክርኮ ፣
ለምታያት ፣ ሁሉ ፣ መንፈስህ ፣ ተማርኮ ፣

ከተሸንፍክማ ፣ በጉንጮቿ ፣ ቅላት ፣
በወገቧ ፣ ቅጥነት ፣ በደረቷ ፣ ሙላት ፣
አበድኩ ፣ ካልክማ ፣ ለጥርሶቿ ፣ ንጣት ፣
ለባቷ ፣ አቀራረጽ ፣ ለጠጉርዋ ፣ ቀለም ፣
ፍቅርህ ፣ ባይንህ ፣ ላይ ፣ ነው ፤ በልብህ ፣ አይደለም ።
ይቅር ፣ በለኝ ፣ ልጄ ፣ ባሁኑ ፣ ወቀሣ ፣
ለዚች ፣ ከንፈሀላት ፣ ያችን ፣ ስትረሳ ፣
አመዛዘንኩና ፣ ሠጋሁ ፣ አስተውዬ ፣
ይችንም ፣ እንደዚያች ፣ ትረሳለህ ፣ ብዬ ።

ሮሜዎ ።

አባቴ ፣ በፍጹም ፣ ይህን ፣ አይጠርጥሩ ፤
የዚችና ፣ የዚያች ፣ ልዩ ፣ ነው ፣ ነገሩ ፣
በምን ፣ ቃል ፣ ልናገር ፣ ይህን ፣ ለማሳመን ፤
በግሪክ ፣ በሮማ ፣ በጥንታዊው ፣ ዘመን ፣
ያነቡ ፣ እንደ ፣ ነበር ፣ የእንስሳውን ፣ ሞራ ፣
ይችሉ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ አባቴ ፣ አባ ፣ ሎራ ፣
እርስዎም ፣ እንደዚሁ ፣ የልቤን ፣ ብራና ፣
በጥበብ ፣ አውጥተው ፣ ገልጠው ፣ ያንቡና ፣
የወረት ፣ ምልክት ፣ ቢያገኙ ፣ በውስጡ ፣
ያን ፣ ጊዜ ፣ ይገባል ፣ ቢንቁኝ ፣ ቢቈጡ ።

አባ ፣ ሎራ ።

መልካም ፣ ነው ፣ አመንኩህ ፣ ግን ፣ ከዚህ ፣ በኋላ

አንድ ፣ ነገር ፣ አለ ፣ የሚያስቸግር ፣ ሌላ ፤
ካፑሌና ፣ ሞንታግ ፣ የናንተ ፣ አባቶች ፣
ወገኖቻቸውን ፣ ጨምረው ፣ ጠላቶች ፣
ባላንጦች ፣ ቂመኞች ፣ ደመኞች ፣ ሲሆኑ ፤
በየመንገዱ ፣ ላይ ፣ እንዳውሬ ፣ እያደኑ ፣
አንዱ ፣ አንዱን ፣ ሲገድለው ፣ ባይኑ ፣ ሲያየው ፣ ብቻ
እንዴት ፣ ሊፈጸም ፣ ነው ፣ የናንተ ፣ ጋብቻ ?
ይኖሩ ፣ የለም ፣ ወይ ፣ ዘወትር ፣ በዘመቻ ፣
ዘለዓለም ፣ ለውጊያ ፣ ለጠብ ፣ ተሰልፈው ፣
ለቁስ ፣ ላስታራቂ ፣ ለዳኛ ፣ አሸንፈው ።

ሮሚዎ ።

ይኸው ፣ አባቴ ፣ ሆይ ፤ ይህ ፣ ነው ፣ ዋናው ፣ ነገር ፤
በዚህ ፣ ላይ ፣ ይገባል ፣ በብዙ ፣ መማከር ፣
እውነት ፣ ነው ፣ ቢኖሩ ፣ ዘለዓለም ፣ እነሱ ፣
በጠብ ፣ ባምባጓሮ ፣ ደም ፣ እያፈሰሱ ፣
ለፍርድ ፣ ቢያስቸግሩ ፣ የቂስ ፣ ቃል ፣ ባይሰሙ ፣
እኔና ፣ ዠልዬት ፣ ግን ፣ ንጹሕ ፣ ነን ፣ ከቂመ ፣
አለ ፣ ወይ ፣ አባቴ ፣ በሃይማኖት ፣ መንገድ ፣
የሚከለክል ፣ ሕግ ፣ እኛ ፣ እንዳንዋደድ ፣
እንግዲህ ፣ አባቴ ፣ ይህንን ፣ ካወቁ ፣
ዘዴውን ፣ ለማግኘት ፣ እርስዎም ፣ ይጨነቁ ፣

ቤተ ፣ ሰቦቻችን ፣ ወሬውን ፣ ሳይሰሙ ፣
ተክሊሉን ፣ በምስጢር ፣ እርስዎ ፣ ይፈጽሙ ።

አባ ፣ ሎራ ።

ይህንን ፣ ታልህማ ፣ ዘዴ ፣ ጠፍቶ ፣ ለርቁ ፣
ካህንም ፣ አልቀረም ፣ አብሮ ፣ መጨነቁ ፣
ለሁለቱ ፣ ወገን ፣ ሰላምን ፣ መልሶ ፣
ያባቶቻችሁን ፣ ክፉ ፣ ቂም ፣ ደምስሶ ፣
ስለታቸው ፣ ዘወትር ፣ የሰው ፣ ደም ፣ ከማፍሰስ ፣
እንዲቆም ፣ ለማድረግ ፣ ትንሽ ፣ እንዲታገሥ ፣
ለሻምላ ፣ ለጩቤ ፣ ለሰይፍ ፣ ለጦራዴ ፣
ከዚህ ፣ የተሻለ ፣ መች ፣ ይገኛል ፣ ዘዴ ።
የናንተ ፣ ጋብቻ ፣ ይህን ፣ ቂም ፣ አብርዶ ፤
ዕርቅ ፣ ይመሠረታል ፣ ሰላምን ፣ አውርዶ ።

ሮሚዎ ።

እንግዴህ ፣ አባቴ ፣ እንፍጠን ፣ በቶሎ ፣
ተክሊሉ ፣ ይፈጸም ፣ በዛሬ ፣ ቂን ፣ ውሎ ፣
ጊዜና ሰዓቱን ፣ ካልተሻማን ፣ በጣም ፣
እንዲህ ፣ ያለ ፣ ፍቅር ፣ ዕንቅፋት ፣ አያጣም ።

አባ ፣ ሎራ ።

እንግዲያው ፣ መልካም ፣ ነው ፣ ኑና ፣ ባሥር ፣ ሰዓት ፣
ትፈጽማላችሁ ፣ የተክሊሉን ፣ ሥራት ።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ትይንት ፡ ፫ ።

የዠልዬት ፡ ሞግዚትና ፡ ሮሜዎ ።

ሞግዚት ።

መልሱን ፡ ተቀብለሽ ፡ እንድትመጪ ፡ ብላ ፡
ልካኝ ፡ እመቤቴ ፡ በቶሎ ፡ አስቸኵላ ፡
ይኸው ፡ መጥቻለሁ ፡ መልሱን ፡ ለመቀበል ፤
ቸኵያለሁና ፡ ንገረኝ ፡ ቶሎ ፡ በል ።

ሮሜዎ ።

መላሴ ፡ ያሞግስ ፡ አፌም ፡ ያመስግናት ፤
በውነት ፡ ያንቺ ፡ እመቤት ፡ የተባረከች ፡ ናት ፡
ዐመሏ ፡ ጠባይዋ ፡ በለጠ ፡ ከመልኳ ፤
ቃሏን ፡ ፈጸመችው ፡ አንቺን ፡ በመላኳ ፡
ዦሮቼ ፡ ተከፍተው ፡ እሰማለሁና ፡
እንግዲህ ፡ ንገሪኝ ፡ የዠልዬትን ፡ ዜና ።

ሞግዚት ።

ለተነጋገርነው ፡ ትናንትና ፡ ማታ ፡
እንድትልክብኝ ፡ ያሳብህን ፡ ሁኔታ ፡
በመጠበቅ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ አስታውቀኝ ፡ በቶሎ ፤
በዬና ፡ ንገሪው ፤ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
አሳቡን ፡ ሲነግርሽ ፡ ተቀብለሽ ፡ አምጪ ፡
ብላኝ ፡ መጥቻለሁ ።

ሮሜዎ ።

መልሴን ፡ ስትሰጪ ፡

እንግዲያው ፡ ንገሪያት ፡ ሮሜዎ ፡ ከልቡ ፡
ይወድሻል ፡ ብለሽ ፡ መንፈሱም ፡ አሳቡ ፡
ወዳንቺ ፡ ነው ፡ በያት ፡ ንገሪያት ፡ አደራ ፤
እስቲ ፡ ልለምንሽ ፡ እባክሽ ፡ ሳልፈራ ፡
እኔ ፡ እንደምወዳት ፡ እንደዚሁም ፡ እሷ ፡
ትወደኝ ፡ እንደሆን ፡ ዠልዬት ፡ በመንፈሷ ፡
ታውቂዋለሽና ፡ እባክሽ ፡ ንገሪኝ ፡
አሳቧን ፡ ጠባይዋን ፡ እንዳውቀው ፡ ምከሪኝ ።

ሞግዚት ።

ምንም ፡ አልደብቅህ ፡ ልንገርህ ፡ ካንዠቴ ፡
አንተን ፡ ስታፈቅር ፡ ዠልዬት ፡ እመቤቴ ፡
እመነኝ ፡ ልንገርህ ፡ በውነት ፡ ከልቧ ፡ ነው ፤
የመስፍኑ ፡ ዘመድ ፡ ፓሪስ ፡ የሚባለው ፡
ሊያገባት ፡ ፈልጎ ፡ መሞቱ ፡ ነው ፡ ደክሞ ፡
ጨርሳ ፡ አትወደውም ፡ እሷ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡
አታንሡ ፡ ትላለች ፡ የሱን ፡ ስም ፡ ከፊቴ ፤
ትቈጣለችና ፡ ስቈይ ፡ እመቤቴ ፡
ልመለስ ፡ እባክህ ፡ መልሱን ፡ ስጠኝና ፤

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

ሮሜዎ ።

አቀርብልሻለሁ ፡ በሰፈው ፡ ምስጋና ።
እንደዚህ ፡ በዩና ፡ መልሱንም ፡ ንገሪያት ፤
ከቀትር ፡ በኋላ ፡ ዛሬ ፡ ባሥር ፡ ሰዓት ፡
አባ ፡ ሎራ፡ ድረስ ፡ አስፈቅዳ ፡ ትምጣ ፤
ተናዘን ፡ ተባርከን ፡ የተክሊሉን ፡ ጣጣ ፡
ደብቀው ፡ በሙሉ ፡ ሊፈጽሙ ፡ ቄሱ ፡
ተስማምተናል ፡ በያት ፡ ዛሬ ፡ ሊጨርሱ ።

ትይንት ፡ ፬ ።

አባ ፡ ሎራ ፡ ዠልዬት ፡ ሮሜዎ ።

አባ ፡ ሎራ ።

የናንተ ፡ ጋብቻ ፡ ፍጻሜው ፡ እንዲያምር ፡
ፈጣሪ ፡ ጸጋውን ፡ ምሕረቱን ፡ ይጨምር ።

ሮሜዎ ።

አሳቤ ፡ ሞላልኝ ፡ እንግዲህ ፡ አባቴ ፡
ይህ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ የቀረኝ ፡ ምኞቴ ።
ከሷ ፡ ጋራ ፡ መጥቼ ፡ ቀርበን ፡ ከመንበሩ ፡
ሥራቱን ፡ ከሞላን ፡ አለቀ ፡ ነገሩ ፡
እንግዲህ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ የመጣ ፡ ቢመጣ ።

አባ ፡ ሎራ ።

ልጄ ፡ ሆይ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጣጣ ።

ለደስታ ፡ ሐዘን ፡ ለማር ፡ አለው ፡ እሬት ፤
ጠፊ ፡ ካጥፊው ፡ ጋራ ፡ ይኖራል ፡ በመሬት ፡
ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ መጥፎውን ፡ አርቆ ፡
ልጄ ፡ ያኑራችሁ ፡ በሰላም ፡ ጠብቆ ።

(ዠሊዬት ፡ መጣች) ።

ፍቅሯንና ፡ ጌጧን ፡ በልቧ ፡ ሸፍና ፡
አልማዟ ፡ ማስተዋል ፡ ወርቋ ፡ ትሕትና ፡
ምስጢሯን ፡ ባሳቧ ፡ በጥበብ ፡ ሰውራ ፡
ይኸው ፡ መጣችልን ፡ መልካሟ ፡ ሙሽራ ።

ዠልዬት ።

ሰላም ፡ ለርስዎ ፡ ይሁን ፡ አባቴ ፡ አባ ፡ ሎራ ።

አባ ፡ ሎራ ።

ደኅና ፡ ነሽ ፡ ወይ ? ልጄ ፡ ወጣት ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፤
መልካም ፡ ጊዜ ፡ መጣሽ ፡ ልክ ፡ በቀጠሮ ።

ዠልዬት ።

አመሰግናለሁ ፡ ለኔም ፡ ለሮሜዎ ፡
አባቴ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በመቸገርዎ ።

ሮሜዎ ።

እንዳንቺ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ በፍቅር ፡ ተሳስረው ፡
ለመጡ ፡ ወጣቶች ፡ ሥራቱን ፡ አክብዶው ፡
ፍቅራችውን ፡ ባርኮ ፡ በእጁ ፡ ሊቀድሰው ፡
ምን ፡ ጊዜም ፡ ሥራው ፡ ነው ፡ ካህን ፡ የሆነ ፡ ሰው።

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

አባ ፡ ሎራ ።

እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፡ ካህን ፡ ይጠብቃል ፤
እውነት ፡ ነው ፡ ሮሚዎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንግባና ፡ በሉ ፡
ሳይዘገይ ፡ በቶሎ ፡ ይፈጸም ፡ ተክሊሉ ።
(ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገቡ)።

ሦስተኛ ፡ አክት ።

ትይንት ፡ ፩ ።

(በሼሮና ፡ ከተማ ፡ መንገድ) ።

ሜርኩቲዎ ፡ ቤንቮሊዎ ፡ አንድ ፡ የእልፍኝ፡አሽከር።

ቤንቮሊዎ ።

ሜርኩቲዎ ፡ እንሂድ ፡ የካፑሌ ፡ ሰዎች ፡
ይጠፉ ፡ አይመስለኝም ፡ በነዚህ ፡ መንደሮች ፡
ድንገት ፡ ብንገናኝ ፡ ኋላ ፡ ጠብ ፡ ይነሣል ፤
ደግሞ ፡ ጠብ ፡ ሲነሣ ፡ ጸጥታ ፡ ይፈርሳል ፡
ብንሸሽ ፡ ይሻላል ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ።

ሜርኩቲዎ ።

እነሱም ፡ አስበው ፡ ነገር ፡ እንዳይመጣ ፡
እንደ ፡ እኛ ፡ ለሰላም ፡ ካልተጠነቀቁ ፡
ዳኝነትን ፡ ፈርተው ፡ ሕጉን ፡ ካልጠበቁ ፡
ዕወቅ ፡ እንዳይበቃ ፡ ጠብ ፡ ብንሸሽ ፡ እኛ ።

ለምሳሌ ፡ መጥቶ ፡ አንዱ ፡ ጥጋበኛ ፡
ያላንድ ፡ ምክንያት ፡ ከመሬት ፡ ተነሥቶ ፡
እንዴት ፡ ታደርጋለህ ፡ ቢጣላህ ፡ ደንፍቶ ?
ያውም ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ የባስክ ፡ ነህ ፡ ከኛ ፤
ትንሽ ፡ የሚበቃህ ፡ ቁጡ ፡ ግልፍተኛ ።

ቤንቮሊዎ ።

እኔስ ፡ ቢዋጣልን ፡ እወድ ፡ ነበረTelegram:Amharic Bo
ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ዐዋጁ ፡ አስቸገረ ፡
ለጠብ ፡ ይነሣና ፡ ልቤም ፡ ሰውነቴ ፡
የመስፍኑ ፡ ቅጣ ፡ ይመጣል ፡ ከፊቴ ።

ሜርኩቲዎ ።

የፈራኸው ፡ ነገር ፡ አልቀረም ፡ ደረሰ ፤
ቲባልት ፡ ይመስለኛል ፡ ጥቅር ፡ የለበሰ ፡
እነሱ ፡ አይደሉም ፡ ወይ ፡ ወዲህ ፡ የሚመጡት ?

ቤንቮሊዎ ።

ተመልከት ፡ ካሁኑ ፡ ደሜን ፡ እንዳስቄጡት ፡
(ቲባልት ፡ ለወገኖቹ) ።

ነቃ ፡ ነቃ ፡ በሉ ፡ አሳዩ ፡ ጉብዝና ፤
ጠብ ፡ ቄስቋሽ ፡ ለመሆን ፡ ፈልጌያለሁና ፡
ይህ፡የማነው፡ሻምላ፡የዛገ፡ሳይሠራ ? (ወደ ፡ ጠላቶቹ፡እያየ)።

ሜርኩቲዎ ።

ምነው ፡ ቢመለከት ፡ ዐይንህ ፡ እያጠራ ፡

Telegram:Amharic Books t.me/amharicbookss

አሁንም ፣ ይሻላል ፣ ብታየው ፣ አስተውለህ ፤
የደረቀ ፣ ደም ፣ ነው ፣ ዝገት ፣ የመሰለህ ።

ቲባልት ።

እረግ ፣ እንዲህ ፣ነው ፣ ወይ ! የበግ ፣ ነው ፣ የዶሮ ?

ቤንቮሊዎ ።

ፈሶ ፣ የተገኘ ፣ ካንገቱ ፣ ጉረሮ ፣
የወገንህ ፣ ደም ፣ ነው ፣ ከበግ ፣ የማይሻል ።

ቲባልት ።

በመሳደብ ፣ ብቻ ፣ ጊዜያችን ፣ ይመሻል ፣
እንግዲህ፣ ይቀጥል ፣ የወንዶቹ ፣ ሥራ ። (ሽምላ፣ መዘዘ)።

ሜርኩቲዎ ።

ዘወትር፣ዝግጁ፣ነኝ፣ማንንም፣አልፈራ፤(ሜርኩቲዎም፣መዘዘ)
(ሮሜዎ ፣ መጣ) ።

ቲባልት ።

ከናንተ ፣ አልዋጋም ፣ መጣ ፣ የኔ ፣ እኩያ ፤
ስማኝ ፣ ሮሜዎ ፣ ወጥቼ ፣ ገበያ ፣
አቃተኝ ፣ ለማግኘት ፣ ፈልጌ ፣ ክፉኛ ፣
አንተን ፣ የመሰለ ፣ የወንድ ፣ መናኛ ።

ሮሜዎ ።

ተፍቋል ፣ ጨርሶ ፣ ቂም ፣ በቀል ፣ ከልቤ ፤
በመጥፎ ፣ ንግግር ፣ ሮሜዎን ፣ ሰድቤ ፣
ላስቄጣው ፣ በማለት ፣ ቂሙን ፣ ልቄስቅሰው ፣

በከንቱ ፣ ይደክማል ፣ የተጣጣረ ፣ ሰው ፣
የፍቅሬ ፣ ምክንያት ፣ ሆኗልና ፣ ብርቱ ፣
ቲባልት ፣ የኔ ፣ ወዳጅ ፣ አትድከም ፣ በከንቱ ።

ቲባልት ።

ጎይለኛው ፣ ቂማችን ፣ ያከማቸው ፣ ዕዳ ፣
መች ፣ እንዲህ ፣ ይፋቃል ፣ ይልቅ ፣ ተሰናዳ ።

ሮሜዎ ።

ቲባልት ፣ ስማኝ ፣ እኔ ፣ ንጹሕ ፣ ነኝ ፣ ከቂሙ ፣
ካጠሌ ፣ የሚሉት ፣ የዘራችሁ ፣ ስሙ ፣
እንደ ፣ ማር ፣ ጣፋጭ ፣ ነው ፣ አይመረኝም ፣ ለኔ ፤
ጠባችሁ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ በውነቱ ፣ ሐዘኔ ።
የፍቅሬን ፣ ምክንያት ፣ ሳታውቀው ፣ መርምረህ ፤
አትድከም ፣ በከንቱ ፣ ክፉ ፣ ቃል ፣ ተናግረህ ፣
ቲባልት ፣ እኔና ፣ አንተ ፣ መቼም ፣ አንጣላም ፤
ደኅና ፣ ዋል ፣ ወዳጄ ፣ እንሂድ ፣ በሰላም ፣
ደግሞም ፣ ከዚህ ፣ በቀር ፣ የሕጉን ፣ ወቀሣ ፣
የመስፍኑን ፣ ዐዋጅ ፣ ልብህ ፣ እንዳይረሳ ።

ሜርኩቲዎ ።

ገሮሮዬ ፣ አይሰማም ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ፍራት ፣
ቲባልት ፣ እይ ፣ ሽምላዬ ፣ ሲያበራ ፣ እንደ ፣ መብ
ራት ። (መዘዘ)።
ተመልሶ ፣ እንግዴህ ፣ አይገባም ፣ ካፎቱ ፣

በደም ፣ ካልታጠበ ፣ የዛገው ፣ ስለቱ ።
(ኩቲባልት ፣ ጋራ ፣ ውጊያ ፣ ገጠሙ) ።

ሮሜዎ ።

ፍጠን ፣ ቤንቮሊዎ ፣ እንገላግላቸው ፤
ሁለቱም ፣ አይረቡ ፣ በውነት ፣ እብዶች ፣ ናቸው ።
ቲባልት ! ሜርኩቲዎ ! አስቡት ፣ አትርሱ ፤
ልዑል ፣ በቀደም ፣ ለት ፣ ደም ፣ እንዳታፈሱ ፣
ብለው ፣ የሰጡትን ፣ ዐዋጁን ፣ አስታውሱ ።
(ገላገላቸውና ፣ ቲባልት ፣ ከወገኖቹ ፣ ጋራ ፣ ሄደ) ።

ሜርኩቲዎ ።

ቄስያለሁ ፣ እኮ ፣ በቃ ፣ የኔ ፣ ነገር ፤
ተበላሸሁ ፣ እኔ ፣ ወይ ፣ አለመመከር ።

ቤንቮሊዎ ፣ (ቊስሉን ፣ ያያል) ።

ለካ ፣ ቄስለሃል ፣ ወይ ? አላየሁም ፣ እኮ !

ሜርኩቲዎ ።

ሐኪም ፣ ይጠራልኝ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ተልኮ ።
(የልፍኝ ፣ አሽከር ፣ ሄደ) ።

ቤንቮሊዎ ።

አይዞህ ፣ የኔ ፣ ወንድም ፣ ትንሽ ፣ ነው ፣ ቊስሉ ፤

ሜርኩቲዎ ።

ምንም ፣ ትንሽ ፣ ቢሆን ፣ አይቀርም ፣ መግደሉ ፣
ካፑሌና ፣ ሞንታግ ፣ ትውልዳቸው ፣ ይጥፋ ፤

በነሱ ፣ ምክንያት ፣ ስንት ፣ ሰው ፣ ተደፋ ፣
በምን ፣ ጎጢአታችን ፣ እንሞታለን ፣ እኛ ፤
ለማይረባ ፣ ነገር ፣ ተሳድቦ ፣ እንደ ፣ እረኛ ፣
በሰው ፣ እጅ ፣ መሞት ፣ በሆነ ፣ ባልሆነው ፣
ከንቱ ፣ ሞት ፣ ይሉሃል ፣ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ነው ።
ተመቸውና ፣ ነው ፣ ይኸ ፣ ፈሪ ፣ መጥፎ ፣
በሮሜዎ ፣ እጅ ፣ ሥር ፣ ታቹን ፣ አሳልፎ ፣
በድንገት ፣ የወጋኝ ፣ በቃ ፣ የኔ ፣ ነገር ፤
ባትገላግሉኝ ፣ አይነካኝም ፣ ነበር ።
(ሜርኩቲዎን ፣ ቤንቮሊዎ ፣ ደግፎት ፣ አብረው ፣ ሄዱ) ።

ሮሜዎ ፣ (ብቻውን) ።

ወዳጄ ፣ ሜርኩቲዎ ፣ የመስፍኑ ፣ ዘመድ ፣
አባቴን ፣ ወገኔን ፣ እኔንም ፣ በመውደድ ፣
እንሆ ፣ ቄሰለ ፣ ለኛ ፣ ሲል ፣ ተጣልቶ ፤
ቲባልት ፣ አዋረደኝ ፣ ከመሬት ፣ ተነሥቶ ።
ዠልዬትን ፣ ወድጄ ፣ ፍቅር ፣ መፈለጌ ፣
ስድቡንም ፣ ሸሽቼ ፣ ከጠብ ፣ ማፈግፈጌ ፣
ወደ ፣መለማመጥ፡ወገኖቼን ፣ መሪ ፣
ወንድነት ፣ ያነሰኝ ፣ አስመሰለኝ ፣ ፈሪ ።
(ቤንቮሊዎ ፣ መጣ) ።

ቤንቮሊዎ ።

አልቅስ ፣ ሮሜዎ ፣ እንባህን ፣ አፍስሰው ፤
ሜርኩቲዎ ፣ ሞተ ፣ መልካሙ ፣ ደጉ ፣ ሰው ።

ሮሚዎ ።

መልካሙ ፡ ወዳጄ ፡ ሚርኩቲዎ ፡ ከሞተ ፡
እንግዴህ ፡ መታረቅ ፡ ሰላም ፡ ተከተተ ፡
ጠባችን ፡ ነደደ ፡ በሱ ፡ የተነሣ ፤
ወደ ፡ ፊት ፡ ይወድቃል ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ሬሳ ።

(ቲባልት ፡ ተመልሶ ፡ መጣ) ።

ቤንቮሊዎ ።

ቲባልት ፡ ይኸ ፡ ሰይጣን ፡ መጥፎ ፡ ጥጋበኛ ፡
እየው ፡ ተመልሶ ፡ ሲመጣ ፡ ወደ ፡ እኛ ።

ሮሚዎ ፡ (ለብቻው ፡ ይናገራል) ።

ወይ ፡ ጥሎኝ ፡ ወይ ፡ ጥዬው ፡ አንጀቴን ፡ ላርሰው ፤
ቄይ ፡ ይምጣ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ደም ፡ ነው ፡ የመለሰው ።
ጉዞልዬት ፡ ደግነቷ ፡ ፍቅሯ ፡ ሰላም ፡ ሆኖ ፡
ይዞህ ፡ የነበርከው ፡ በትዕግሥት ፡ ሸፍኖ ፡
በልቤ ፡ ያለኸው ፡ የቂሜ ፡ ትዙሳት ፡
ለብልበኝ ፡ ጥበሰኝ ፡ አቃጥለኝ ፡ እንደ ፡ እሳት ።

(ለቲባልት ፡ ይናገራል) ።

ቲባልት ፡ በል ፡ ስደበኝ ፡ አሁን ፡ እንደ ፡ ቅድም ፡
የሚርኩቲዎ ፡ ነፍስ ፡ ብቻዋን ፡ አትሂድም ፡
ወይ ፡ እኔን ፡ ወይ ፡ አንተን ፡ እንዱን ፡ ሳታስከትል ፤
ሻምላህን ፡ ምዘዘው ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ሳትል ፡
የምትሻው ፡ ቂሜ ፡ የነደደ ፡ ይሁን ።

ቲባልት ።

አንተም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ትሞታለህ ፡ አሁን ።

(ይዋጉና ፡ ቲባልት ፡ ይወድቃል) ።

ቤንቮሊዎ ።

ሮሚዎ ፡ እትቁም ፡ ቶሎ ፡ ከዚህ ፡ ጥፋ ፤
ቲባልት ፡ ከሞተ ፡ ምንም ፡ የለህ ፡ ተስፋ ፡
መስፍኑ ፡ ሲያገኝህ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶት ፡
ዕወቅ ፡ አይምርህም ፡ ይቀጣሃል ፡ በሞት ።

(ሮሜዎ ፡ ሸሸ ፡ ሰዎች ፡ መጡ) ።

ወታደር ።

እንዴህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ዘለዓለም ፡ የማይበርድ ፡
ነጋ ፡ ጠባ ፡ ሬሳ ፡ በየዋናው ፡ መንገድ ፡
ጠብ ፡ መሆኑን ፡ ሰምተው ፡ ይኸው ፡ ልዑል ፡ መጡ ፤
ማነው ፡ የገደለው ? አሁን ፡ በቶሎ ፡ አሡ ።

መስፍን ።

አወይ ፡ ዘመዴ ፡ ሆይ ፡ ሚርኩቲዎ ፡ ሞተ ፤
ማነው ፡ ጠብ ፡ ሲጀመር ፡ የተመለከተ ?

ቤንቮሊዎ ።

ልዑል ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ያየሁ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፤
ፈቃድዎ ፡ ቢሆን ፡ ፈጥኜ ፡ ልናገር ።

መስፍን ።

ንገረኝ ፡ ሁሉንም ፡ ከምንጩ ፡ ጀምሮ ፤

ቤንቮሊዎ ።

ጠቡን ፣ የጀመረው ፣ ክፉ ፣ ቃል ፣ ተናግሮ ፣
ይሽው ፣ ቲባልት ፣ ነው ፣ ሌላ ፣ ሰው ፣ አይደለም ፤
ከሱ ፣ በቀር ፣ ዛሬ ፣ ጠብ ፣ ያነሣ ፣ የለም ።
እኔና ፣ ሜርኩቲዎን ፣ ሰደበን ፣ ሳንሰድበው ፤
ሮሜዎ ፣ ደረሰ ፣ ድንገት ፣ ሳናስበው ።
እሱም ፣ በደግነት ፣ ቃሉን ፣ እለስልሶ ፣
ልውል ፣ የሰጡትን ፣ ያዋጅ ፣ ቃል ፣ አስታውሶ ፣
ቲባልትን ፣ ለመነው ፣ ጠብ ፣ እንዳያነሣ ፤
መቼም ፣ መጥቷልና ፣ እሱ ፣ ግን ፣ ላበሳ ፣
በእልህ ፣ እንቢ ፣ ብሎ ፣ ስድቡን ፣ ሲቀጥል ፣
ከሜርኩቲዎ ፣ ጋራ ፣ ተማረሩ ፣ በጥል ፤
ሻምላ ፣ ቢግዘዙ ፣ ቱሎ ፣ መገላገል ፣
አሰብንና ፣ ገባን ፣ ከነሱ ፣ መካከል ።
እኔና ፣ ሮሜዎ ፣ ስንገላግላቸው ፣
ሜርኩቲዎን ፣ ለመውጋት ፣ ቲባልት ፣ ተመቸው ፤
እኛም ፣ አላየንም ፣ ሜርኩቲዎን ፣ ሲወጋው ፣
ጓላ ፣ ግን ፣ አየነው ፣ ቁስሉን ፣ ከነ ፣ አደጋው ፣
ከሸሸ ፣ በጓላ ፣ ቲባልት ፣ እንደ ፣ ገና ፣
ቢመጣ ፣ ሮሜዎ ፣ ነዶት ፣ ነበርና ፤
ደሙን ፣ ለመበቀል ፣ በንዴት ፣ ተነሥቶ ፣
ከቲባልት ፣ ጋራ ፣ በቅጽበት ፣ ተዋግቶ ፣

ወዲያው ፣ በደቂቃ ፣ ውጊያው ፣ በጣም ፣ ሲግል ፣
እኔም ፣ ሳያደርሰኝ ፣ ችዬ ፣ ሳልገላግል ፣
ቲባልት ፣ ቁሰለና ፣ በፍጥነት ፣ ወደቀ ፣
ሮሜዎም ፣ ሸሸና ፣ በዚሁ ፣ አለቀ ፤
ከተናገርኩትም ፣ ከውነቱ ፣ የራቀ ፣
ውሸት ፣ ቢገኝብኝ ፣ ተደርጎ ፣ ምርመራ ፣
ይድረስብኝ ፣ በኔ ፣ የቅጣት ፣ መከራ ።

የካፑሌ ፣ ሚስት (መጣች) ።

መሠረት ፣ የለውም ፣ ምስክርነቱ ፤
ከእውነተኛው ፣ ነገር ፣ ይበልጣል ፣ ሐሰቱ ፣
ይህንን ፣ ቢናገር ፣ እያስመሰለ ፣ እሱ ፣
የሞንታግ ፣ ወገን ፣ ነው ፣ ልውል ፣ ሆይ ፣ አይርሱ ፣
በፍርድ ፣ ሮሜዎ ፣ ይሙት ፣ ነው ፣ የምለው ።

መስፍን ።

ሮሜዎ ፣ ቲባልትን ፣ ወግቶ ፣ ከገደለው ፣
እናንተ ፣ ስለሱ ፣ ፍርድ ፣ ስጥ ፣ ስትሉ ፣
የሜርኩቲዎን ፣ ደም ፣ ማን ፣ ይክፈለኝ ፣ ለኔ ፤
ዘመዴ ፣ ነው ፣ እኮ ፣ ሥጋዬ ፣ ወገኔ ።

ሞንታግ ።

ልውል ፣ ሆይ ፣ ሜርኩቲዎን ፣ ቲባልት ፣ ገደለው ፤
ወዋጁ ፣ ቲባልትን ፣ ይሙት ፣ ነው ፣ የሚለው ።

ስለዚህ ፣ ቢያስቡት ፣ አሁን ፣ የኔ ፣ ልጅ ፤
ቲባልትን ፣ ሲገድለው ፣ ዐዋጅ ፣ ፈጸመ ፣ እንጂ ፣
ሌላ ፣ ምን ፣ ጨመረ ፣ እስቲ ፣ ምን ፣ አጠፋ ?

መስፍን ።

ሞንታግ ፣ ምሕረት ፣ አለ ፣ ብለህ ፣ እንዳትለፋ ፣
ሮሜዎ ፣ በፍጥነት ፣ ዛሬ ፣ ካገር ፣ ይውጣ ፤
ጠባችሁ ፣ በኔ ፣ ላይ ፣ ይኸው ፣ ዞሮ ፣ መጣ ፣
በናንተ ፣ ምክንያት ፣ የሞተው ፣ ደጉ ፣ ሰው ፣
ሥጋዬ ፣ ነው ፣ ዛሬ ፣ ደሙ ፣ የፈሰሰው ፣
በሰጠሁት ፣ ዐዋጅ ፣ ራሴ ፣ ወሸኜ ፣
እገኛለሁ ፣ እኔ ፣ ጨካኝ ፣ ቀጭ ፣ ሆኜ ፣
የፍርዴንም ፣ ሥራ ፣ በትጣት ፣ ስሠራ ፣
ይቅርታ ፣ የለኝም ፣ ለማንም ፣ አልራራ ።
አማላጅ ፣ ልመና ፣ ጸጸትና ፣ ለቅሶ ፣
ፍርዴን ፣ ሊመልሱት ፣ አይችሉም ፣ ጨርሶ ፣
ስማ ፣ ልጅህ ፣ ዛሬ ፣ የኔን ፣ ትእዛዝ ፣ ሽሮ ፣
የተገኘ ፣ እንደሆን ፣ በከተማው ፣ አድሮ ፣
ዛሬ ፣ ከቬሮና ፣ በፍጥነት ፣ ካልወጣ ፣
ዕወቀው ፣ ያለፍርድ ፣ በሞት ፣ እንዲቀጣ ።

ትይንት ፣ ፪ ።

ዠልዬትና ፣ ሞግዚቷ ፣ (በቤታቸው) ።

ዠልዬት ።

እኔና ፣ ሮሜዎ ፣ ዕድላችን ፣ ክፉ ፤
ይደንቃል ፣ ሰርጋችን ፣ እንደዚህ ፣ ማለፉ ፣
ሰርጉ ፣ አልነበረም ፣ ወይ ፣ የሰው ፣ ልጅ ፣ ደስታ ፤
እኛ ፣ ግን ፣ ምስኪኖች ፣ በዚህ ፣ ሁሉ ፣ ፈንታ ፣
መሥጋትና ፣ መፍራት ፣ ያባት ፣ የናት ፣ ቁጣ ፣
ሆነና ፣ ተገኘ ፣ የተሰጠን ፣ ዕጣ ።
አልገሠግሥ ፣ አለ ፣ ጊዜና ፣ ሰዓቱ ፤
ምነው ፣ የዛሬ ፣ ቀን ፣ ደከመ ፣ ፍጥነቱ ?
ሰዓቱም ፣ ለገመ ፣ ዳተኛ ፣ መሆኑ ፣
ሮሚዎን ፣ ስጠብቅ ፣ አልመሸ ፣ አለኝ ፣ ቀኑ ።
ደግሞ ፣ ሞግዚቴ ፣ ነች ፣ ዋና ፣ ጥፋተኛ ፤
ምነው ፣ ሆነችብኝ ፣ እንደዚህ ፣ ዳተኛ ?
በፊት ፣ ደጎንነቱን ፣ ነግራኝ ፣ ተመልሳ ፣
መሄድ ፣ ትችል ፣ ነበር ፣ ዳግም ፣ በግሥግሣ ፣
ሌሊቱ ፣ ሲጨልም ፣ ጨረቃ ፣ ሳትወጣ ፣
ንገሪው ፣ አልኩና ፣ ሮሜዎ ፣ እንዲመጣ ፣
ብልካት ፣ እንሆ ፣ ቀረች ፣ እዚያው ፣ ቀልጣ ።
እባክህ ፣ ጨለማ ፣ ፍጠን ፣ በቶሎ ፣ ና ፤
ካልመሸ ፣ ሮሜዎ ፣ ደፍሮ ፣ አይመጣምና ።

ሌሊቱ ፡ ይተካ ፡ የቀን ፡ ብርሃን ፡ ሄዶ ፤
ሮሚዎን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲያስገባው ፡ ጋርዶ ።
ቀኑ ፡ እየደከመ ፡ ብርሃን ፡ እየሸሸ ፡
ፀሓይ ፡ እየጠፋች ፡ ሰዓቱ ፡ እየመሸ ፡
አንተ ፡ ከባድ ፡ ጽልመት ፡ የሌሊት ፡ ጨለማ ፡
ፈጥነህ ፡ ቶሎ ፡ ድረስ ፡ አትሁን ፡ ደካማ ።
ገሥግሠህ ፡ ሸፍናት ፡ ዓለምን ፡ በጥላ ፤
ጥላህ ፡ ለሮሚዎ ፡ ይሁነው ፡ ከለላ ፡
ፀሓይም ፡ ጥለቂ ፤ ብርሃንን ፡ አትስጪ ፤
ኮከብ ፡ ተሰወሪ ፡ ጨረቃም ፡ አትውጪ ፡
ካለም ፡ ገለል ፡ በሉ ፡ ብርሃንና ፡ ፋና ፡
ብርሃን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ሮሚዎ ፡ ነውና ፡
ያቻት ፡ ወዲህ ፡ መጣች ፡ ብቅ ፡ አለች ፡ ሞግዚቴ ፡
ደርሳ ፡ እስክትነግረኝ ፡ ወሬውን ፡ ከፌቴ ፡
ቸኩያለሁ ፡ በጣም ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ወሬ ፡
ይዘሽልኝ ፡ መጣሽ ፡ ሞግዚቴ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ?
ምነው ፡ ምን ፡ ሆነሻል ፡ ፊትሽ ፡ ተለወጠ ?

ሞግዚት ።

አዬ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ በቃ ፡ ተቈረጠ ፡
ባጭር ፡ ተቀጠፈ ፡ ያን ፡ መሳይ ፡ መኰንን ፤
አዬ ፡ ጉድ፡አዬ ፡ ጉድ ! ጠላሁ ፡ ሰው ፡ መሆንን ፤

ጁልዬት ።

አሁን ፡ ባሁን ፡ ሄደሽ ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ከወጣሽ ፡
ምን ፡ ዐይነት ፡ ጎዘን ፡ ነው ፡ ይዘሽው ፡ የመጣሽ ?

ሞግዚት ።

አወይ ፡ ሮሚዎ ፡ ቲባልት ፡ መልካሙ ፡ ሰው፡
እንደ ፡ ፋሲካ ፡ በግ ፡ ደሙ ፡ የፈሰሰው ።

ጁልዬት ።

ሐዘኑን ፡ ሰምቼ ፡ ልቤ ፡ ሳይመታ ፡
መናገር ፡ አቃተሽ ፡ አፍሽ ፡ አመነታ ፡
ሮሚዎ ፡ ሞተ ፡ ወይ ? ሞቶም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ንገሪኝ ፡ ምላስሽ ፡ እየሸፋፈነ ፡
ሳይደብቅ ፡ ገልጠልኝ ፡ መርዶውን ፡ ልረዳ ፤
ልቤም ፡ ተሠንጥቆ ፡ በሐዘን ፡ ይፈንዳ ።

ሞግዚት ።

ቊስሉንም ፡ አየሁት ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል ፤
ሐኪም ፡ አይጠሩለት ፡ ሞቶ ፡ ምን ፡ ይሆናል ።
ምንም ፡ ትንፋሽ ፡ የለው ፡ አልፋለች ፡ ሕይወቱ፡
ደሙ ፡ ይመነጫል ፡ ቈስሎ ፡ ከደረቱ ፤
ከሞተ ፡ ቈይቷል ፡ ደርቋል ፡ ሰውነቱ ፡

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ መቼም ፡ አልተሠራም
ዠልዬት ፡ የዛሬ ፡ ጉድ ፡ ይቅር ፡ አይወራም
ቲባልት ! ሮሜዎ ! አየሁ ፡ ደሙ ፡ ፈሶ ፡
ልብሱ ፡ ተበክሎ ፡ መሬቱም ፡ ርሶ ።

ዠልዬት ።

ቲባልት ! ሮሜዎ ! ሁለቱንም ፡ ጠርተሽ ፡
ከምታስጨንቂኝ ፡ ንገሪኝ ፡ ለይተሽ ፡
ሮሜዎ ፡ ባሌ ፡ ነው ፡ ቲባልት ፡ ዘመዴ ፤
የቱ ፡ ነው ፡ የሞተው ፡ ተጨነቅ ፡ ሆዴ ።
ባለም ፡ ላይ ፡ ከሌሉ ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡
መታከት ፡ ነውና ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡
የምጽአት ፡ ቀን ፡ ይሁን ፡ መለከት ፡ ይነፋ ፤
አሁን ፡ ተደምሰሶ ፡ ፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ይጥፋ፡
ባሕር ፡ ጫካ ፡ ገደል ፡ ጅረትም ፡ ተራራ ፡
ፍጡር ፡ እዴዴ ፡ በል ፡ አልቅስ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ።

ሞግዚት ።

ሟቹ ፡ ቲባልት ፡ ነው ፡ ካለም ፡ ላይ ፡ የሄደ ፤
ገዳዩ ፡ ሮሜዎ ፡ ካገር ፡ ተሰደደ ።

ዠልዬት ።

ሮሜዎ ፡ ቲባልትን ፡ ብትዪኝ ፡ ገደለው ፡
አይችልም ፡ መንፈሴ ፡ አምኖ ፡ ሊቀበለው

ሞግዚት ።

የተሠራውን ፡ ጉድ ፡ እንግዲህ ፡ ዕወቂው ፤
እርገሚው ፡ ሮሜዎን ፡ ከልብሽም ፡ ናቂው ፡
በቀልሽን ፡ ቂምሽን ፡ አድርጊው ፡ የጸና ፤
በውነቱ ፡ ሮሜዎ ፡ ሰው ፡ አይደለምና ።
አብነት ፡ ይሁንሽ ፡ ይህ ፡ መጥፎ ፡ ደመኛ ፤
ሰውን ፡ አትመኝ ፡ እንግዲህ ፡ ዳግመኛ ፡
ፍቅሩም ፡ ደግነቱም ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው ፡ ከንቱ ፤
ፈጽሞ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ ሰዓቱ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሮሜዎ ፡ ሲሠራ ፡
ማነው ፡ የሚታመን ? ማነው ፡ ባለአደራ ?

ዠልዬት ።

ምንም ፡ አልተገኘ ፡ የሚበጀኝ ፡ ለኔ ፤
ሁለት ፡ ስለት ፡ ያለው ፡ ሰይፍ ፡ ነው ፡ ጎዘኔ ፡
ቲባልት ፡ ባይሞት ፡ ኖሮ ፡ ሮሜዎ ፡ ይሞታል ፤
ቲባልት ፡ ባይሸነፍ ፡ ሮሜዎ ፡ ይረታል ፡
ሮሜዎን ፡ ከልብሽ ፡ ትይኛለሽ ፡ ጥዬው ፤
ምነው ፡ ልቤን ፡ ገብተሽ ፡ መርምረሽ ፡ ብታዪው ፡
ለኔም ፡ ገዳይ ፡ ቢሆን ፡ ለናቴም ፡ ላባቴ ፡
ሮሜዎን ፡ ለመጥላት ፡ አይችልም ፡ አንጀቴ ።

ቲባልትም ፡ መጥፎ ፡ ነህ ፡ ሮሜዎም ፡ አትረባ ፤
መሪር ፡ ነው ፡ ከናንተ ፡ የሚተርፈኝ ፡ እንባ ፡
ባሌ ፡ ካገር ፡ ወጣ ፤ ቲባልት ፡ ሞተ ፡ በፊት ፤
ሐዘኔ ፡ ዐንጐል ፡ የሌለው ፡ መድኀኒት ፡
እንደ ፡ ምን ፡ አድርጌ ፡ ደግሞስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡
እኖራለሁ ፡ እኔ ፡ እናንተን ፡ አጥቼ ፡
ከቲባልት ፡ መሞት ፡ ሮሜዎ ፡ ስደቱ ፡
ከሮሜዎ ፡ ስደት ፡ ቲባልት ፡ መሞቱ ፡
ቢሆን ፡ ምን ፡ ችግረው ፡ ሐዘኔ ፡ በተራ ፤
ለማንኛው ፡ ላልቅስ ፡ ወይ ፡ የኔ ፡ መከራ ፤
ዛሬ ፡ በሠርጌ ፡ ቀን ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ መዋሌ ፡
ቀረና ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡ እንዲሰደድ ፡ ባሌ ፡
ቲባልትም ፡ እንዲሞት ፡ አድርጎ ፡ ዕድሌ ፡
ሐዘን ፡ ከሆነማ ፡ ለኔ ፡ የደገሰው ፡
ልቤ ፡ ሳያደላ ፡ እንባዬን ፡ ላፍስሰው ።

ሞግዚት ።

በእውነት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ባሏን ፡ ከወደደች ፡ አይቀ
እንዳንች ፡ አድርጎ ፡ ነው ፡ ከልቡና ፡ ማፍቀር ፡
ከልብ ፡ አዘንኩልሽ ፡ በጣሙን ፡ አድርጌ ፤
አለበት ፡ ገብቼ ፡ ሮሜዎን ፡ ፈልጌ ፡
እኔ ፡ አመጣዋለሁ ፡ እንባሽን ፡ አድርቂው ፤
እመኝታ ፡ ቤትሽ ፡ ግቢና ፡ ጠብቂው ።

ፃፎ

በስደተኛነት ፡ ሳይሄድ ፡ ነገ ፡ ርቆ ፡
ተሰነባበቱ ፡ ይምጣ ፡ ተደብቆ ።

ዠልዬት ።

መልካም ፡ ነው ፡ ሞግዚቴ ፡ ሙሽራ ፡ ሲገባ ፡
አጊጦ ፡ ታጅቦ ፡ በዘፈን ፡ ባበባ ፡
በወግ ፡ በማዕርግ ፡ ባለም ፡ በደስታ ፡
በክብር ፡ ነበረ ፡ በብዙ ፡ እልልታ ፤
ሌሊት ፡ ጨለማውን ፡ ከለላው ፡ አድርጎ ፡
የኔ ፡ ሙሽራ ፡ ግን ፡ ይግባ ፡ ተሸሽጎ ።
እንቢ ፡ ብሎ ፡ እንዳይቀር ፡ ጠርተሽ ፡ ስታመጪው ፡
እንቺ ፡ ለምልክት ፡ ቀለበቴን ፡ ስጪው ፡
(ቀለበቷን ፡ ሰጠቻት) ።

ትይንት ፡ ፫ ።

አባ ፡ ሎራ ፡ (ባባ ፡ ሎራ ፡ ቤት) ።

ሮሜዎ ፡ ብቅ ፡ በል ፡ውጣ ፡ ከጨለማ ፤
የፍርዱን ፡ ቃል ፡ ይገፍ ፡ መጣሁ ፡ ልጄ ፡ ስማ ።

ሮሜዎ ።

ሳልሰማው ፡ ቢዘገይ ፡ ይሻለኝ ፡ ነበረ ፤
ፍርዱ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ? ልቤ ፡ ተሸበረ ።

አባ ፡ ሎራ ።

መስፍኑ ፡ ፈቀደ ፡ በቀላል ፡ ሊቀጣ ፤

የሞት ፣ ፍርድ ፣ ቀርቶ ፣ ካገር ፣ እንድትወጣ ።

ሮሜዎ ።

ጨካኝ ፣ ቅጣት ፣ እንጂ ፣ ከሞትም ፣ የከፋ ፤
ይህ ፣ ፍርድ ፣ መሪር ፣ ነው ፣ ያስቄርጣል ፣ ተስፋ ፣
ዠልዬት ፣ ካለችበት ፣ ከተማ ፣ ወጥቼ ፣
ስደተኛ ፣ ሆኜ ፣ አገሬንም ፣ ትቼ ፣
የምኖረው ፣ ኑሮ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ይገፋል ፤
ቀኑና ፣ ሰዓቱ ፣ ደቂቃው ፣ መች ፣ ያልፋል ፣
እንዴት ፣ እችላለሁ ፣ ዠልዬትን ፣ ለመርሳት ፣
ሲአል ፣ ነው ፣ ኩነኔ ፣ ሞት ፣ ገሃነመ ፣ እሳት ።

አባ ፣ ሎራ ።

ደስታህ ፣ ቀረና ፣ በማመስገን ፣ ፈንታ ፣
ለምን ፣ ትረሳለህ ፣ የእግዜርን ፣ ውለታ ፣
ወዋጁ ፣ የሚያዘው ፣ የሞት ፣ ቅጣት ፣ ነበር ፣
ለምን ፣ አታስብም ፣ ይህን ፣ ትልቅ ፣ ነገር ፣
ሄደህ ፣ ብትቀመጥ ፣ በማንቱ ፣ ከተማ ፣
አገሩ ፣ ጥሩ ፣ ነው ፣ በጣም ፣ የሚስማማ ፣
ልጄ ፣ ሆይ ፣ ቅጣቱ ፣ በጣም ፣ የቀለለ ፣
ጥሩ ፣ ነው ፣ ሺ ፣ ጊዜ ፣ ከሞት ፣ የተሻለ ።

ሮሜዎ ።

ያስቡት ፣ አባቴ ፣ ነገሩን ፣ ያስተውሉት ፤
ምኑን ፣ ነው ፣ እርስዎ ፣ ቀላል ፣ ነው ፣ የሚሉት ።

አባ ፣ ሎራ ።

ብስጭት ፣ አታብዛ ፣ በጣም ፣ አትናደድ ፤
ከመሞት ፣ ይሻላል ፣ ሺ ፣ ጊዜ ፣ መሰደድ ።
ልጄ ፣ ዓለም ፣ ሰፊ ፣ ነች ፤ ወጥተህ ፣ ከቬሮና ፣
የትም ፣ ሄደህ ፣ መኖር ፣ ትችላለህና ።

ሮሜዎ ።

ወጥቼ ፣ ከሄድኩኝ ፣ እኔ ፣ ከቬሮና ፣
ውሸት ፣ ነው ፣ አባቴ ፣ ምን ፣ ዓለም ፣ አለና ፣
ሕይወት ፣ ነው ፣ አይበሉት ፣ የምኖረው ፣ ኑሮ ፤
ዓለም ፣ እዚህ ፣ ቀረ ፣ ከሚስቴ ፣ ጋር ፣ አብሮ ፣
ሰው ፣ እንስሳ ፣ ዕንጨት ፣ አበባና ፣ ቅጠል ፣
ፀሐይ ፣ ተከልሎ ፣ አየር ፣ ሳይቀበል ፣
የኖረ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ይሞታል ፣ ይደርቃል ፤
ለኔም ፣ እንደዚህ ፣ ነው ፣ ስደት ፣ የሚሉ ፣ ቃል ።
አገሬ ፣ ንብረቴ ፣ አየሬ ፣ ፀሐዬ ፣
ዓለሜ ፣ ትንፋሼ ፣ ሕይወቴ ፣ ሰማዬ ፣
የነበረችውን ፣ ዠልዬትን ፣ አጥቼ ፣
እሷ ፣ ካለችበት ፣ ከተማ ፣ ወጥቼ ፣
መሄዴ ፣ ከሆነ ፣ እሷም ፣ ከኔ ፣ ርቃ ፣
ነጣጥለው ፣ ከለዩን ፣ የኔ ፣ ነገር ፣ በቃ ።
ሕይወቴም ፣ ኑሮዬም ፣ ሞተ ፣ ተበላሸ ፤
ደስታ ፣ ተለየኝ ፣ ከኔ ፣ ርቆ ፣ ሸሸ ፣
እንግዲህ ፣ መቆሜ ፣ ለምንም ፣ አይበጅ ፤

ይህን ፡ ኑሮ ፡ አይበሉት ፡ መናወዝ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡
ፍርድ ፡ ማሻሻያ ፡ የተባለው ፡ ዘዴ ፡
ከመርዝም ፡ ይብሳል ፡ ከጦር ፡ ከጐራዴ ፡
ስደት ፡ የሚሉ ፡ ቃል ፡ ጨለማ ፡ ነው ፡ ገደል ፤
እኔን ፡ አስጨንቆ ፡ የመጣ ፡ ለመግደል ።

አባ ፡ ሎራ ።

እረ ፡ ስማኝ ፡ ልጄ ፡ ምክሬንም ፡ ተቀበል ፡
ሞትና ፡ መሰደድ ፡ እኩል ፡ ነው ፡ አትበል ።

ሮሜዎ ።

ተመልሰው ፡ ስደት ፡ ወደሚባለው ፡ ቃል ፡
ሊመጡ ፡ ነውና ፡ አባቴ ፡ ይበቃል ፡
ምን ፡ አደከመዎት ፡ በቃ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
እኔን ፡ የሚያጥናና ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ፡
ከሞት ፡ የባሰ ፡ ነው ፡ የመከራ ፡ ጭቃ ፤
የሮሜዎ ፡ ነገር ፡ ተከተተ ፡ በቃ ።

አባ ፡ ሎራ ።

ዐውቃለሁ ፡ እንዲሆን ፡ ስደትህ ፡ መራራ ፤
ግን ፡ መድኀኒት ፡ አለው ፡ ለዚህ ፡ ለመከራ ፡
ዕረፍት ፡ እንድታገኝ ፡ ባሳብ ፡ በኅሊና ፡
የደረሰብህን ፡ ጭንቅህን ፡ እርሳና ፡
ልብህን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ፍልስፍና ።

ሮሜዎ ።

ዝፍልዬትን ፡ ፈጥሮልኝ ፡ ካልሰጠኝ ፡ አምጥቶ ፡

የመስፍኑን ፡ ብይን ፡ በጥበብ ፡ አጥፍቶ ፡
እኔን ፡ ካላዳነኝ ፡ የርስዎ ፡ ፍልስፍና ፡
ለምንም ፡ አይበጀኝ ፤ የለውም ፡ ርባና ።

(የዝፍልዬት ፡ ሞግዚት ፡ ከደጅ ፡ ሆና ፡ በር ፡ መጣች) ።

አባ ፡ ሎራ ።

ተነሣ ፡ ሮሜዎ ፡ ግባ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፤
ስማ ፡ በር ፡ ይመታል ፡ መጣብን ፡ እንግዳ ፡
ተደበቅ ፡ በቶሎ ፡ ጥግ ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡
ይይዙሃልና ፡ ያገኙህ ፡ እንደሆን ።

(በሩ ፡ ይመታል) ።

ሮሜዎ ።

በስደት ፡ ከሆነ ፡ እኔ ፡ የምቀጣ ፡
ምን ፡ ያስጨንቀኛል ፡ የፈቀደው ፡ ይምጣ ።

አባ ፡ ሎራ ።

ለምን ፡ ትሆናለህ ፡ አንተ ፡ እንደዚህ ፡ ደረቅ ፤
እባክህ ፡ ግባና ፡ በቶሎ ፡ ተደበቅ ፡ (ሮሜዎ ፡ ሄደ) ።
እንዲህ ፡ ባሁን ፡ ሰዓት ፡ የመጣ ፡ በማታ ፡
ማነው ፡ በጨለማ ፡ በሬን ፡ የሚመታ ?

ሞግዚት ።

መጥቻለሁና ፡ ልካኝ ፡ እመቤቴ ፤
የዝፍልዬት ፡ ሞግዚት ፡ ነኝ ፡ ያስገቡኝ ፡ አባቴ ።

አባ ፡ ሎራ ።

እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣሽ ፡ ነይ ፡ ግቢ ፡ ወዳጄ ፤
(ከፍተውላት ፡ ገባች) ።

ሞግዚት ።

ሮሜዎን ፡ አጣሁት ፡ ብፈልገው ፡ ሄጄ ።
ይንገሩኝ ፡ አባቴ ፡ ከመሸ ፡ አሁን ፡ ማታ ፤
አይተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ።

አባ ፡ ሎራ ።

በሐዘኑ ፡ ሰክሮ ፡ ያለቅሳል ፡ ተጨንቆ ፤
ያውልሽ ፡ ከጓዳ ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ።

ሞግዚት ።

ዠልዬት ፡ እመቤቴም ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡
ስታለቅስ ፡ ዋለች ፡ ይኸው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡
ጥሩልኝ ፡ አባቴ ፡ መልክቴን ፡ ልንገረው ።

ሮሜዎ ፡ (ከጓዳ ፡ ወጣ) ።

ዠልዬት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነች?መልካም ፡ የነበረው ፡
ልቧ ፡ ተለውጦ ፡ ባደረግሁት ፡ ነገር ፡
አልጠላችኝም ፡ ወይ ? ምላስሽ ፡ ይናገር ፡
ልብሽ ፡ አይደብቀኝ ፡ ንገሪኝ ፡ አትፍሪ ፤
ያየሽውን ፡ ሁሉ ፡ አስተካክለሽ ፡ አውሪ ።

በሠራሁት ፡ ሥራ ፡ ፍቅራችን ፡ መጥፋቱ ፡
እንግዴህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተቀብሮ ፡ መቅረቱ ፡
እርግጥ፡አይደለም ፡ ወይ ? እንዴት ፡ ነው ፡ መንፈሷ ፤
እኔን ፡ ስታነሣ ፡ ምን ፡ ትላለች ፡ እሷ ።

ሞግዚት ።

በሐዘን ፡ ተጨንቃ ፡ ከማልቀስ ፡ በተቀር ፡
ከፉም ፡ ሆነ ፡ በጎ ፡ ምንም ፡ አትናገር ፡
ቲባልት ! ሮሜዎ ! አዬ ፡ ጕድ ፡ እያለች ፡
እንባዋን ፡ በማፍሰስ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ዋለች ፡
ሐዘኗ ፡ ግን ፡ ሆኗል፡ አለመጠን ፡ ብርቱ ፡
ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ ተሰነባበቱ ፤
እንሂድ ፡ በቶሎ ፡ መሸብን ፡ ሰዓቱ ።

ሮሜዎ ።

ገላዬን ፡ ብወጋ ፡ እስቲ ፡ ከምን ፡ ቦታ ፡
መሞት ፡ እንደምችል ፡ በቅጽበት ፡ አንዳፍታ ፡
ብልኅ ፡ ነዎትና ፡ ጥበብን ፡ መርማሪ ፤
ተምረው ፡ እንደሆን ፡ ያከላትን ፡ ባሕሪ ፡
በፍጥነት ፡ ይንገሩኝ ፡ አባቴ ፡ አባ ፡ ሎራ ፤
የት ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ነፍሱ ፡ ያለችበት ፡ ስፍራ ?
አድርጊያለሁና ፡ ጸጸቷን ፡ መራራ ፡
ሐዘኔ ፡ጥልቅ ፡ ነው ፡ አልችልም ፡ ልጥናና ፤
በገዛ ፡ እጄ ፡ ልሞት ፡ ቈርጫለሁና ። (ሰይፉን ፡ መዘዘ።)

አባ ፣ ሎራ ።

ለምን ፣ ታስባለህ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ነገር ፤
ብላሽ ፣ ሰው ፣ አትሁን ፣ ሲመክሩህ ፣ ተመከር
እንደ ፣ ሴት ፣ አታልቅስ ፣ እንዳውሬ ፣ አትቄጣ ፤
እንደ ፣ እብድ ፣ አትበሳጭ ፣ ከሰው ፣ ግብር ፣ አትውጣ
ትመስለኝ ፣ ነበረ ፣ በውነቱ ፣ ጠንካራ ፤
ሰው ፣ ለምን ፣ ይረባል ፣ ካልቻለ ፣ መከራ ።
መቀጣት ፣ ከወደድህ ፣ በገዛ ፣ እጅህ ፣ ሞተህ ፣
ስለምን ፣ ገደልከው ፣ ቲባልትን ፣ ተዋግተህ ?
በገዛ ፣ እጅህ ፣ ብትሞት ፣ ባለማመዛዘን ፣
መግደልህ ፣ እኮ ፣ ነው ፣ ሚስትህን ፣ በሐዘን ፣
ለዚህ ፣ ነው ፣ ልጄ ፣ ሆይ ፣ ጎሊናና ፣ አእምሮ ፣
ከእግዜር ፣ የተሰጠ ፣ ለሰው ፣ ልጅ ፣ ተፈጥሮ ፤
ዠልዬት ፣ ጠልታኛለች ፣ ብለህ ፣ ስትሠጋ ፣
ሰው ፣ ልካ ፣ ጠራችህ ፣ ምሕረትን ፣ አድርጋ ፣
ቲባልት ፣ ሊገድልህ ፣ ቢመጣ ፣ ደንፍቶ ፣
በገዛ ፣ ጥጋቡ ፣ ወደቀ ፣ ተወግቶ ፣
ባንተም ፣ የሞት ፣ ቅጣት ፣ ሊወድቅ ፣ የነበረው ፣
በስደት ፣ ለውጠ ፣ መስፍናችን ፣ ሻረው ፣
ብትመለከተው ፣ በውነቱ ፣ የት ፣ አለ ፤
እንዳንተ ፣ የቀናው ፣ በጣም ፣ የታደለ ፣
ተጠንቀቅ ፣ በውነቱ ፣ ልጄ ፣ በጣም ፣ ሥጋ ፤

ሳታውቀው ፣ ብትቀር ፣ የደስታን ፣ ዋጋ ፣
ኑሮህ ፣ ይበላሻል ፣ አለመጠን ፣ ፍራ ፣
ምን ፣ ጊዜም ፣ አይለቅህ ፣ ጭንቅና ፣ መከራ ።
ሚስትህን ፣ ምከራት ፣ እንዳትሞት ፣ አልቅሳ ፤
መምሸቱ ፣ ነውና ፣ በል ፣ ቶሎ ፣ ተነሣ ፣
ነገ ፣ ግን ፣ ለመሄድ ፣ ልብህ ፣ ይሰናዳ ፤
ውጣ ፣ ከቬሮና ፣ ሌሊት ፣ በማለዳ ፣
ተዛውረህ ፣ ተቀመጥ ፣ ሄደህ ፣ ወደ ፣ ማንቱ ፤
እኛ ፣ ጊዜ ፣ አግኝተን ፣ ሲመቸን ፣ ሰዓቱ ፣
ወገኖቻችሁን ፣ በምክር ፣ አስታርቀን ፣
ጋብቻችሁንም ፣ በገሃድ ፣ አስታውቀን ፣
ላንተም ፣ ከመስፍኑ ፣ ምሕረትን ፣ ጠይቀን ፣
እንጣጣራለን ፣ ቶሎ ፣ እንድትመለስ ፣
እግዜር ፣ ይጠብቅህ ፣ በል ፣ እስከዚያ ፣ ድረስ ፤
አሁን ፣ ወደ ዠልዬት ፣ በቶሎ ፣ ሂድ ፣ ተነሥ ።

ትይንት ፣ ፬ ።

የካፑሌ ፣ ሚስት ፣ ካፑሌ ፣ ፓሪስ ።

ፓሪስ ።

ጉዳዩ ፣ ዘገየ ፣ በመዋል ፣ በማደር ፤
ታዲያስ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ የጋብቻው ፣ ነገር ?

ካፑሌ ።

ነገሩን ፡ ለዝልዬት ፡ ሳልነግር ፡ መቅረቴ ፡
ወድጄን ፡ አይደለም ፡ እንዲህ ፡ መዘግየቴ ፡
በቲባልት ፡ መሞት ፡ አዝናለች ፡ በብርቱ ፤
ታፈቅረው ፡ ነበረ ፡ ከልቧ ፡ በውነቱ ፡
ስለዚህ ፡ ሐዘኑ ፡ ጥቂት ፡ ሳይረሳ ፡
አልቻልኩም ፡ ጕዳዩን ፡ ለጊዜው ፡ ላነሣ ፡
አድርግልኝና ፡ ከልብህ ፡ ይቅርታ ፤
እኔ ፡ እጨርሳለሁ ፡ ነገሩን ፡ አንድ ፡ አፍታ ፡

ፓሪስ ።

እውነት ፡ ነው ፡ ሐዘኑ ፡ ፈጽሞ ፡ አልተመቸም ፤
ተስማምተንበታል ፡ ይህን ፡ ጕዳይ ፡ መቼም ፡
እሷም ፡ እንቢ ፡ እንዳትል ፡ እናንተ ፡ አስቡበት ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

ግድ ፡ የለም ፡ ሠርጋችሁ ፡ ይሆናል ፡ በፍጥነት ፡

ካፑሌ ።

ፓሪስ ፡ ሆይ ፡ አትሥጋ ፤ አይዞህ ፡ ይህን ፡ ጕዳይ ፡
መሄድ ፡ ትችላለህ ፡ ጥለኸው ፡ በኔ ፡ ላይ ፡
እንዴት ፡ ትወጣለች ፡ ከኔ ፡ ፈቃድ ፡ ልጄ ፤
ያቀረብኩላትን ፡ መርጬ ፡ ወድጄ ፡
ያላንድ ፡ ቅሬታ ፡ አለባት ፡ መቀበል ፤
እንዲያውም ፡ እንፍጠን ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ አንበል ።

በይ ፡ ፍጠኝ ፡ ሚስቴ ፡ ወደ ፡ ልጅሽ ፡ ሂጂ ፤
በዘዴ ፡ በርጋታ ፡ ነገሩን ፡ አስረጂ ፡
መልካሙ ፡ ልጃችን ፡ ፓሪስ ፡ አንቺን ፡ ወዶ ፡
እኔም ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ አባትሽም ፡ ፈቅዶ ፡
ይኸው ፡ በዚህ ፡ ሰሞን ፡ ሊያገባሽ ፡ ነውና ፡
ተዘጋጂ ፡ በያት ፡ በሙሉ ፡ ልቡና ፡
በል ፡ አንተም ፡ ንገረኝ ፡ እንደምትፈልገው ፤
ሰርጉ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለመቼ ፡ እናድርገው ?

ፓሪስ ።

እንደ ፡ እኔ ፡ ሰርጋችን ፡ የራቀ ፡ ከሚሆን ፡
ቢፈጸም ፡ ይሻላል ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ሰሞን ።

ካፑሌ ።

እንግዲያው ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ባጭር ፡ እንደግስ ፤
ተክሊሉም ፡ ይፈጸም ፡ በሚመጣው ፡ ኀሙስ ፡
ጃጃታ ፡ አላበዛም ፡ ብዙም ፡ ሰው ፡ አልጠራ ፤
ልጄን ፡ እድራለሁ ፡ ብዬም ፡ አላወራ ፡
ሐዘን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቲባልት ፡ በመሞቱ ፡
ቅር ፡ ያሰኛልና ፤ ዘመድ ፡ በጥቂቱ ፡
በድብቅ ፡ እንጥራ ፡ ነገር ፡ ሳናበዛ ፤
እንደዚህ ፡ ብናደርግ ፡ ወሬው ፡ ሳይነዛ ፡
ጕዳያችን ፡ ያልቃል ፡ ያገር ፡ ሰው ፡ ሳይሰማ ፤
እንግዲህ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ በዚሁ ፡ እንስማማ ።

ፓሪስ ።

እኔም ፡ እስማማለሁ ፡ ይሁን ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፤
በሉ ፡ እስከዚያው ፡ድረስ ፡እግዜር ፡ ይጠብቀን ። (ሄደ)፡

ካፑሌ ፡ (ለሚስቱ ።)

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ባል ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ የበቃ ፡
ቢሄዱ ፡ አይገኝም ፡ እግር ፡ እስቲነቃ ፡
በይ ፡ ቶሎ ፡ ፍጠኚ ፡ ወደ ፡ ልጅሽ ፡ ሂጂ ፤
ነግ ፡ ጪት ፡ አሳቢን ፡ ልቢን ፡ አዘጋጂ ።

ትይንት ፡ ፭ ።

ሮሜዎና ፡ ገ፩ልዬት ፡ (በገ፩ልዬት ፡ መኝታ ፡ ቤት) ።

ገ፩ልዬት ።

አይዞህ፡አትቸኩል ፡ አልነጋም ፡ ሌሊቱ ፤
ቁጭ ፡ በል ፡ እናውጋ ፡ ገና ፡ ነው ፡ ሰዓቱ ፡
ተመልከት ፡ ጨለማ ፡ መሬቱን ፡ ሲሸፍን ፡
የሰማናትም ፡ ወፍ ፡ አሁን ፡ ስትዘፍን ፡
ዞትር ፡ ልማጁ ፡ ነው ፡ ሌሊቱ ፡ ሳይነጋ ፡
መጮህ ፡ ትወዳለች ፡ እመነኝ ፡ አትሥጋ ።

ሮሜዎ ።

ይህች ፡ የንጋት ፡ ወፍ ፡ ነች ፡ አሁን ፡ የጮኸችው ፤
ትክክል ፡ ይታያል ፡ ገ፩ልዬት ፡ ተመልከችው ፡

ሰማይ ፡ ወገግ ፡ አለ ፡ ያው ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፤
ሰዓቱ ፡ ደረሰ ፡ እንግዴህ ፡ ልቸኩል ፡
በቬሮና ፡ አድራ ፡ ቢያገኙኝ ፡ ሳልወጣ ፡
መስፍኑ ፡ ፈርደዋል ፡ በሞት ፡ እንድቀጣ ፡
ልዳን ፡ ያልኩ ፡ እንደሆን ፡ ሕይወቴን ፡ ወድጄ ፡
መሄድ ፡ ይገባኛል ፡ አሁን ፡ ተሰድጄ ።

ገ፩ልዬት ።

እኔ ፡ መች ፡ አጣሁት ፡ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ ብርሃን ፡
የሰማይ ፡ ፋና ፡ ነው ፡ የኮከብ ፡ ውጋጋን ፡
ሌሊት ፡ በጨለማ ፡ ሳይነጋ ፡ ሌሊቱ ፡
ለምን ፡ ትሄዳለህ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ማንቱ ፡
አይዞህ ፡ እንጫወት ፡ ሌቱ ፡ አልነጋም ፡ ገና ፤
ጊዜ ፡ አለን ፡ እስኪታይ ፡ የንጋቱ ፡ ፋና ።

ሮሜዎ ።

ዘፈኑ ፡ ሲወጣ ፡ አልሰማንም ፡ ካቼ ፡
አልነጋም ፡ ሌሊቱ ፡ አልጮኸችም ፡ ወቼ ፡
ይህም ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚታይ ፡ ውጋጋን ፡
አይደለም ፡ የመጣ ፡ ከፀሓይዋ ፡ ብርሃን ፡
ብለን ፡ እንካደው ፤ አምጄ ፡ ልቀበል ፡
ሳልወጣ ፡ ይያዙኝ ፡ ተይዤም ፡ ልገደል ፡

ካንቺ ፡ ተለይቼ ፡ የሐዘን ፡ ኵነኔ ፡
ከሚያገኘኝ ፡ መሞት ፡ እመርጣለሁ ፡ እኔ ።
አልፈራም ፡ ፈጽሞ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ብቀጣ ፤
ዥልዬት ፡ ከፈቀደች ፡ የፈለገው ፡ ይምጣ ፤
ወፎች ፡ አልተንጫጩም ፡ ሌሊቱም ፡ አልነጋ ፤
ዥልዬት ፡ ጨዋታ ፡ አምጪ ፡ እንግዴህ ፡ እናውጋ ፤

ዥልዬት ።

እኔ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ ገና ፡ ነው ፡ ሌሊቱ ፤
አሁን ፡ ገና ፡ ታየኝ ፡ ትክክል ፡ መንጋቱ ፡
ንጋት ፡ ነው ፡ የመጣው ፡ ሂድ ፡ ቶሎ ፡ ተነሣ ፤
አምልጠህ ፡ ሽሽ ፡ ቶሎ ፡ ብረር ፡ በግሥገሣ ፡
እየው ፡ ተመልከተው ፡ የንጋት ፡ ወገግታ ፤
ጨለማውን ፡ ቀዶ ፡ ሄደ ፡ እየበረታ ፡
አስተውለው ፡ መሬቱ ፡ ሲታየን ፡ ተገልጦ ፤
አሞኘችኝ ፡ ወኛ ፡ ድምፅዋ ፡ ተለውጦ ፡
ፍጠን ፡ ቶሎ ፡ ውጣ ፡ እየው ፡ እንደ ፡ ነጋ ፤
ተነሥ ፡ ቶሎ ፡ ጥፋ ፤ አይንካህ ፡ አደጋ ።

ሞግዚት ።

እናትሽ ፡ ነቅተዋል ፡ እመቤቴ ፡ ዕወቂ ፤
መንጋቱ ፡ ነውና ፡ በጣም ፡ ተጠንቀቂ ።

ዥልዬት ።

ደኅና ፡ ሰንብት ፡ ልበል ፡ እኔው ፡ አስቀድሜ ፤
እንግዴህ ፡ ደኅና ፡ ሁን ፡ ሮሜዎ ፡ ወንድሜ ።

ሮሜዎ ።

ዥልዬት ፡ ደኅና ፡ ሁኝ ፡ ደኅና ፡ ሰንብች ፡ ፍቅሬ ፤

ዥልዬት ።

አደራ ፡ እንዳገኘው ፡ እኔ ፡ ያንተን ፡ ወሬ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጻፍልኝ ፡ መሆንህን ፡ ጤና ፤
መቼ ፡ እንደማገኝህ ፡ አላውቀውምና ።

ሮሜዎ ።

መቼም ፡ ቢሆን ፡ ካንቺ ፡ አይለይም ፡ ልቤ ፤
እጽፍልሻለሁ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ደብዳቤ ።

ዥልዬት ።

አንተ ፡ ስታስበው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ዳግመኛ ፡
እንገናኛለን ፡ ትላለህ ፡ ወይ ፡ እኛ ?

ሮሜዎ ።

አምናለሁ ፡ ፍቅሬ ፡ ሆይ ፡ አምላክ ፡ እንዲራራ ፤
ትምህርት ፡ ይሆነናል ፡ ያሁኑ ፡ መከራ ።

ዥልዬት ።

የሆንኩትን ፡ እንጃ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ለራሴ ፤
መጥፎ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ያስባል ፡ መንፈሴ ።

ሮሜዎ ።

ያገኘን ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ብርቱ ፡
ከመንፈሳችን ፡ ውስጥ ፡ አይጠፋም ፡ ስሜቱ ፤
ዠልዬት ፡ ደጎና ፡ ሁኝ ፡ ረፈደ ፡ ሰዓቱ ፡ (ሄደ) ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ፡(የዠልዬት ፡ እናት)

ወዴት ፡ ነው ፡ ያለሽው ፡ ልጄ ፡ ተነሣሽ ፡ ወይ ?

ዠልዬት።

ይኸው ፡ ተነሣሁኝ ፡ ምነው ፡ እናቴ ፡ ሆይ ?

(ለብቻዋ ፡ ቀስ ፡ ብላ) ።

ምን ፡ ነካት ፡ እናቴ ፡ እንዲህ ፡ ጢት ፡ ተነሥታ ፡
ፈልጋኝ ፡ አታውቅም ፡ በማለዳ ፡ መጥታ ።

(የካፑሌ ፡ ሚስት ፡ ወደ፡ልጅዋ፡ወደ፡ዠልዬት ፡ መኝታ ፡ ቤት፡ገባች፡

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

ወፈር ፡ አስመሰለሽ ፡ የቲባልት ፡ ሐዘን ፡
ያስፈልጋል ፡ ልጄ ፡ ማሰብ ፡ ማመዛዘን ፡
እንባ ፡ ቢያፈሱለት ፡ ቢያለቅሱለት ፡ በጣም ፡
ሰው ፡ እንዴ ፡ ከሞተ ፡ ተመልሶ ፡ አይመጣም ፡
ሐዘን ፡ የሚያስረሳ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ወሬ ፡
ይዤ ፡ ወዳንቺ ፡ ዘንድ ፡ መጥቻለሁ ፡ ዛሬ ።

ዠልዬት ።

እናቴ ፡ ንገሪኝ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ነው ?

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

በቲባልት ፡ መሞት ፡ በብዙ ፡ ያዘነው ፡
ልብሽ ፡ እንዲጽናና ፡ በጣም ፡ በማሰቡ ፡
መልካሙ ፡ አባትሽ ፡ አላረፈም ፡ ልቡ ፤
በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ሳይውልም ፡ ሳያድር ፡
ቄርጪል ፡ ለጥሩ ፡ ባል ፡ ጎሙስ ፡ አንቺን ፡ ሊድር ።
ባልሽ ፡ የሚሆነው ፡ ቆንጆ ፡ ነው ፡ ጌታ ፡ ሰው ፤
በዘርም ፡ በገንዘብ ፡ ምንም ፡ የማያንሰው ፡
እንዲያውም ፡ ገልጬ ፡ ልንገርሽ ፡ ካሁኑ ፤
መልካሙ ፡ ፓሪስ ፡ ነው ፡ ወጣት ፡ መኰንኑ ።

ዠልዬት ።

እናቴ ፡ ሆይ ፡ምነው ፡ በፊት ፡ ሳንማከር ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡
አስቀድመን ፡ እኛ ፡ ተጫጭተን ፡ በደንቡ ፡
ሳላውቀው ፡ ሳያውቀኝ ፡ በፍጥነት ፡ ተጋቡ ፡
እንዴት ፡ ትላላችሁ ፡ እንዲህ ፡ በችኰላ ?
አሁንም ፡ በቶሎ ፡ ፈልጉለት ፡ መላ ፡
እኔ ፡ አልችልምና ፡ ለማግባት ፡ በቶሎ ፤
አባቴን ፡ ንገሪው ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብሎ

ቃል ፡ ቢኖር ፡ ምናልባት ፡ ለፓሪስ ፡ የሰጠው ፡
አንድ ፡ ዘዴ ፡ ፈጥሮ ፡ ቶሎ ፡ እንዲለውጠው ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

አፍሽን ፡ አታጥፊ ፡ ምክንያት ፡ አታምጪ ፡
ያለቀ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ዐርፈሽ ፡ ተቀመጪ ።

ዡልዬት ።

አድምጪኝ ፡ እናቴ ፡ እንግዲያውስ ፡ ስሚ ፤
አባቴም ፡ አይልፋ ፡ አንቺም ፡ አትድከሚ ፡

የመጣ ፡ ቢመጣ ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ደግሞ ፡
እኔ ፡ አላገባም ፡ ፓሪስን ፡ ፈጽሞ ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

አልገባም ፡ ጨርሼ ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡ ጣጣ ፤
ንገሪው ፡ ላባትሽ ፡ ይኸው ፡ ወዲህ ፡ መጣ ።

ካፑሌ ፡ (ገባ) ።

ምነው ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ? በይ ፡ ልመለስ ፡ ሄጄ ፡
ታዲያስ ፡ ነገርሻት ፡ ወይ ፡ ነገሩን ፡ ለልጄ ?

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

እኔ ፡ ከሷ ፡ ጋራ ፡ አልችልም ፡ ክርክር ፤
ትችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስረዳት ፡ በምክር ።

ካፑሌ ።

እስቲ ፡ እኮ ፡ ንገሪኝ ፡ ምንድነው ፡ ነገሩ ፡
አሁን ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ደርሶ ፡ ግርግሩ ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

ትችል ፡ ትመስላለህ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ደርሶ ፡
የምሥራች ፡ « እንቢ» ፡ ብላለች ፡ ጨርሶ ፡
የመጣ ፡ ቢመጣ ፡ ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡
አላገባም ፡ አለች ፡ ፓሪስን ፡ ፈጽሞ ።

ካፑሌ ።

እግራችንን ፡ ስማ ፡ እኛን ፡ አመስግና ፡
በትልቅ ፡ ደስታ ፡ መቀበል ፡ ቀረና ፡
እንቢ ፡ አለች ፡ ብትይኝ ፡ ጉሮዬም ፡ አይሰማ ፤
እስቲ ፡ ልስማው ፡ እኔ ፡ ትናገረው ፡ ደግማ ።

ዡልዬት ።

ለክፋት ፡ አይደለም ፡ አትቄጣ ፡ አባቴ ።

ካፑሌ ።

እረግ ፡ የኛ ፡ ሕፃን ፡ ትንሿ ፡ ማሚቴ ፡
የማነሽ ፡ ለዛ ፡ ቢስ ፡ የማነሽ ፡ ወልጋዳ ፤
የማነሽ ፡ አመዳም ፡ የማነሽ ፡ ገዳዳ ፡
ባለወግ ፡ አድርገን ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ያጠፋን ፡
ብታውቂው ፡ ባታውቂው ፡ ኧረ ፡ ምን ፡ አለፋን ።

በግድ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በጎይል ፣ የምንድር ፣
መች ፣ ያስፈልግና ፣ ይህ ፣ ሁሉ ፣ ንግግር ፣
ነገ ፣ በማለዳ ፣ ተዘጋጅተሽ ፣ ውጪ ፤
ከተክሊሉ ፣ ቦታ ፣ ዐውቀሽ ፣ እንድትመጪ ፣
ታዛዤ ፣ ነሽና ፣ የወለድኩሽ ፣ ልጄ ፤
እኔ ፣ እድርሻለሁ ፣ በጎይል ፣ አስገድጄ ፤
ለወግ ፣ መጠየቄ ፣ ቅብጠት ፣ ነው ፣ አብጄ ፣
እስከዚያ ፣ ድረስ ፣ ግን ፣ በፊቴ ፣ አትለፊ ፤
ዐይንሽን ፣ አልየው ፣ ካጠገቤ ፣ ጥፊ ።

ገጾልዬት ።

ነገሩን ፣ ላስረዳህ ፣ አባቴ ፣ እድምጠኝ ፤
ጋብቻው ፣ ፈጠነ ፣ ጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ስጠኝ ።

ካፑሌ ።

ነገርሽ ፣ እሬት ፣ ነው ፣ መራር ፣ ነው ፣ ኰምጣጣ ፤
ካፍሽ ፣ ካንደበትሽ ፣ አንድ ፣ ቃል ፣ አይውጣ ፣
ሴት ፣ ልጅ ፣ እንቢ፡ብትል፡አለው ፣ አንድ ፣ አገባ
መች ፣ ተሠርቶ ፣ ያውቃል ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ጥጋ
ዘሩ ፣ የታወቀ ፣ መልኩ ፣ የሚያኰራ ፣
ገንዘብ ፣ የተረፈው ፣ ስሙ ፣ የተጠራ ፣
ደኅና ፣ ባል ፣ ፈልጎ ፣ በሽንት ፣ መከራ ፣
አባቷ ፣ ሲያመጣ ፣ ወዲያ ፣ ወዲህ ፣ ዞሮ ፣

ከቤት ፣ ተወዝፋ ፣ የኛ ፣ ሴት ፣ ወይዘሮ ፣
እኔ ፣ ባል ፣ አልሻም ፣ ትላለች ፣ ሞጋጌ ፤
መካን ፣ ሰው ፣ ይሻላል ፣ ከመውለድ ፣ ባለጌ ።
ጥጋብሽ ፣ ነው ፣ እኮ ፣ ደሜን ፣ የሚያፈላው ፤
ምኑ ፣ ነው ፣ እባክሽ ፣ ፓሪስ ፣ የሚጠላው ?
ያለባል ፣ ለመኖር ፣ ከሆንሽ ፣ የምትወጂ ፣
ምን ፣ ቸገረኝ ፣ እኔ ፣ ወደ ፣ ገዳም ፣ ሂጂ ፣
ነገር ፣ ግን ፣ ከሆነ ፣ ማግባትሽ ፣ የማይቀር ፣
የመረጥኩልሽን ፣ ይገባሻል ፣ ማፍቀር ፣
ያላንድ ፣ ክርክር ፣ ያላንድ ፣ ቅሬታ ፣
ፈቃዴን ፣ መቀበል ፣ አለብሽ ፣ ግዴታ ።
የምትይ ፣ ከሆነ ፣ የኔን ፣ ፈቃድ ፣ እንቢ ፣
ከዛሬ ፣ ጀምረሽ ፣ ሂጂ ፣ ገደል ፣ ግቢ ፤
ዐይንሽን ፣ አልየው ፣ በዚህ ፣ በኔ ፣ ግቢ ።

የካፑሌ ፣ ሚስት ።

ቀስ ፣ ብሎ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ አባት ፣ ከመከረ ፣
አንተም ፣ አበዛኸው ፣ ነገርህ ፣ ከረረ ።

ካፑሌ ።

እትግቢ ፣ ፈጽሞ ፣ አንቺ ፣ በኔ ፣ ሥራ ፤
ሂጂ ፣ ወደ ፣ ጓዳ ፣ ከሴቶቹ ፣ ጋራ ፣
ቀኑን ፣ ሙሉ ፣ ባሳብ ፣ ሌሊቱን ፣ በሕልሜ ፣
ባል ፣ ስፈልግላት ፣ በመኖር ፣ ደክሜ ፣

በስንት ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ እኔ ፡ ተጣጥሬ ፡
እግዚአብሔር ፡ ረድቶኝ ፡ ይኸውና ፡ ዛሬ ፡
የሚሆን ፡ ሰው ፡ ባገኝ ፡ ጨዋ ፡ ባለገንዘብ ፡
እሜቴ ፡ ፈጠሩ ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ሰበብ ።
ስሚኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ልንገርሽ ፡ ካሁኑ ፤
እሱን ፡ ካላገባሽ ፡ ታዘቢኝ ፡ በውኑ ፡
የትም ፡ ትሄጃለሽ ፡ አብርሬሽ፡ ከቤቴ ፤
እርሜን ፡ አወጣለሁ ፡ ቈርጬ ፡ ካንጀቴ ።
ልጅና ፡ አባት ፡ ሆነን ፡ መኖራችን ፡ ቀርቶ ፡
ክጄሽ ፡ ትሄጃለሽ ፡ አልምርሽም ፡ ከቶ ፡
ስለዚህ ፡ አስቢ ፡ ከልብሽ ፡ ምከሪ ፤
የሚከተለውን ፡ ተመልክተሽ ፡ ፍሪ ፡
ካሁኑ ፡ ጀምረሽ ፡ በነገሩ ፡ ሥጊ ፤
ቃሌ ፡ አይታጠፍም ፡ ኋላ ፡ ልብ ፡ አድርጊ ።

(ካፑሌ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ) ።

ዥልዬት ።

እባክሽ ፡ እናቴ ፡ ለልጅሽ ፡ እዘኚ ፤
ባይሆን ፡ እንኳን ፡ አንቺ ፡ ከኔ ፡ ወገን ፡ ሁኚ ፡
ቀኑ ፡ ረዘም ፡ ይበል ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ስጡኝ ፤
አሳቤን ፡ ሳታውቁ ፡ በከንቱ ፡ አትቈጡኝ ።

ግዴታ ፡ ካልሆነ ፡ በጣም ፡ ካልቸገረኝ ፡
እንቢ ፡ አልልምና ፡ ምክንያት ፡ ካልኖረኝ ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

ዕዳሽን ፡ በጨርቅሽ ፡ እንደምትፈልጊ ፡
አንቺ ፡ እንደ ፡ ፈቃድሽ ፡ እንዳሻሽ ፡ አድርጊ ።

(እናቷም ፡ ወጥታ ፡ ሄደች) ።

ዥልዬት ።

ርጂኝ ፡ አንቺ ፡ እባክሽ ፡ ምከሪኝ ፡ ሞግዚቴ ፤
ምስጢር ፡ ተካፋዬ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፡ እናቴ ፡
የኛን ፡ ተክሊል ፡ ማንም ፡ አይችልም ፡ ሊያፈርሰው ፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ ድብቅ ፡ ነው ፡ አያውቅም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡
እባክሽ ፡ ምከሪኝ ፡ ዘዴ ፡ አታጭምና ፤
ጨነቀኝ ፡ ጠበበኝ ፡ አገኘኝ ፡ ፈተና ።

ሞግዚት ።

ቃሌን ፡ ብትሰሚ ፡ ተራዬን ፡ ልናገር ፤
ሮሜዎ ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡ ተሰደደ ፡ ካገር ፡
ልትኖሩ ፡ ከሆነ ፡ ለብቻ ፡ ለብቻ ፡
በዚሁ ፡ ይፈርሳል ፡ የናንተ ፡ ጋብቻ ፡
በዚሁ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አባትሽ ፡ ላባቱ ፡
ቂመኛ ፡ ነውና ፡ ደመኛ ፡ ጠላቱ ፤
ዕርቅ ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ መጓጓት ፡ ነው ፡ ከንቱ ።

ስለዚህ ፡ ፓሪስን ፡ እሺ ፡ ብለሽ ፡ አግቢ ፤
ሮሜዎን ፡ በልብሽ ፡ በቃሽ ፡ አታስቢ ፡
ደግሞስ ፡ ምንና ፡ ምን ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፤
ፓሪስ ፡ የላቀ ፡ ነው ፡ በውበት ፡ በሀብቱ ፡
በዘር ፡ በጌትነት ፡ ይበልጣል ፡ በሁሉ ፤
ደግሞስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ሕግስ ፡ ቢሆን ፡ ቅሉ ፡
በድብቅ ፡ የሆነው ፡ አይረጋም ፡ ተክሊሉ ።

ዠልዱት ።

እውነት ፡ ካንጀት ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የምትናገሪ ?

ሞግዚት ።

ከልቤ ፡ መሆኑን ፡ አትጠራጠሪ ።

ዠልዱት ።

መልካም ፡ ነው ፡ በይ ፡ ሄደሽ ፡ ንገሪያት ፡ ለናቴ ፤
መሄዴ ፡ ነውና ፡ በፍጥነት ፡ መውጣቴ ፡
ወደ ፡ አባ ፡ ሎራ ፡ ዘንድ ፡ በፍጥነት ፡ ደርሼ ፡
እመጣለሁ፡በያት፡አሁን፡ተመልሼ ። (ሞግዚት ፡ ሄደች)።

(ዠልዱት ፡ ብቻዋን) ።

ለማ ፡ ልናገረው ፡ ምስጢሬን ፡ ገልጬ ፡
ወደ ፡ አባ ፡ ሎራ ፡ ዘንድ ፡ ልሂድ ፡ እንጂ ፡ ሮጬ ፡
ከካህናቶች ፡ ዘንድ ፡ ቢበጅም ፡ ቢከፋ ፡
የነፍስ ፡ መድኀኒት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይጠፋ ።

ሌላስ ፡ አላገኝም ፡ ልቤን ፡ ጠልቆ ፡ የሚያይ ፡
ሁሉም፡አውሬ፡ናቸው፡ሰው፡የለም፡ባለም፡ላይ፡ (ሄደች)።

አራተኛ ፡ አክት ።
ትይንት ፡ ፩ ።
አባ ፡ ሎራና ፡ ዠልዱት ።
ዠልዱት ።

ይዘኑልኝ ፡ በጣም ፡ አባቴ ፡ አባ ፡ ሎራ ፤
በኔ ፡ ላይ ፡ ዘንድሮ ፡ የመጣው ፡ መከራ ፡
ፍጻሜ ፡ የለውም ፡ ቁርጫለሁ ፡ ተስፋ ፤
ይርዱኝ ፡ እባክዎ ፡ ጨርሼ ፡ ሳልጠፋ ።

አባ ፡ ሎራ ።

አዝኛለሁ ፡ ልጄ ፡ ነገሩን ፡ ሰምቼው ፤
አሁን ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፡ ፓሪስን ፡ አግኝቼው ፡
ተክሊሉን ፡ ለናንተ ፡ ጎሙስ ፡ እንድሞላ ፡
ለምኖኝ ፡ ነበረ ፡ እንዲህ ፡ በችኮላ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ መለስኩለት ፤
በነገሩ ፡ በጣም ፡ አዝኛለሁ ፡ በውነት ።

ዠልዱት ።

እንግዲያው ፡ ከሰሙት ፡ እንሆ ፡ ችግሬ ፤
ሥቃዬ ፡ የጠና ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ አሳሬ ፡

እሄድ ፣ ነበር ፣ በውነት ፣ ሴት ፣ ባልሆን ፣ ጠፍቼ ፤
ለፓሪስ ፣ ሊድሩኝ ፣ ቁርጠው ፣ ዘመዶቼ ፣
አስጨንቀው ፣ ያዙኝ ፣ ይሽው ፣ በግዴታ ፤
አባትም ፣ እናትም ፣ የምድር ፣ ሁሉ ፣ ጌታ ፣
ቅጣዜር ፣ የዳረውን ፣ አይችልም ፣ ሊያፋታ ።
እኔና ፣ ሮሜዎን ፣ ሁለቴ ፣ ሲድረን ፣
በፊት ፣ በጥበቡ ፣ ከልብ ፣ አፋቀረን ፤
ቀጥሎ ፣ በርስዎ ፣ በካህኑ ፣ ሥልጣን ፣
ባርኮ ፣ አገናኘን ፣ በተክሊል ፣ ቃል ፣ ካዳን ።
አባቴና ፣ እናቴ ፣ ይሀን ፣ አላወቁ ፤
ለፓሪስ ፣ ሊድሩኝ ፣ እንሆ ፣ ታጠቁ ፣
እንግዴህ ፣ አባቴ ፣ እርስዎ ፣ ከግዜር ፣ ጋራ ፣
በርትተው ፣ ያድኑኝ ፣ ከዚህ ፣ ከመከራ ፣
የማይቻል ፣ ሆኖ ፣ ካልተገኘ ፣ ዘዴ ፣
ብልሃቱን ፣ መፈለግ ፣ አለብኝ ፣ በግዴ ፣
ይሽው ፣ በዚህ ፣ ጩቤ ፣ ሆዴን ፣ እቀድና ፣
እገላገላለሁ ፣ ከዚህ ፣ ኪፈተና ።

አባ ፣ ሎራ ።

ጎጢአቱ ፣ ትልቅ ፣ ነው ፣ በነፍስ ፣ የሚያስቀጣ ፤
በገዛ ፣ እጅሽ ፣ መሞት ፣ ባሳብሽ ፣ አይምጣ ።

ፓሪስን ፣ ለማግባት ፣ ልብሽ ፣ ካልፈቀደ ፣
ይሀን ፣ ያሽል ፣ በውነት ፣ ሆድሽ ፣ ካልወደደ ፣
ግልጥ ፣ አድርጊና ፣ ንገሪኝ ፣ አትፍሪ ።

ዝልዬት ።

እግዚአብሔር ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ መንፈስን ፣ መርማሪ ፣
ፓሪስን ፣ ከማግባት ፣ በውነቱ ፣ አባቴ ፣
አሁን ፣ ባሁን ፣ ፈጥኖ ፣ ይምጣ ፣ ጊዜ ፣ ሞቴ ፣
ልገረፍ ፣ ልሰቀል ፣ በሥቃይ ፣ ልገደል ፤
ወስዳችሁ ፣ ወርውሩኝ ፣ ጣሉኝ ፣ ወደ ፣ ገደል ፣
የትም ፣ ተረስቼ ፣ ልዋረድ ፣ ልጉላላ ፤
ብትፈልጉ ፣ ዳሩኝ ፣ ለዱር ፣ ወሮ ፣ በላ ፣
ከዥብ ፣ ጋራ ፣ እሰሩኝ ፣ ከነብር ፣ ካንበሳ ፤
ካፅም ፣ ጋራ ፣ ቅበሩኝ ፣ ከትዙስ ፣ ሬሳ ፣
እሳት ፣ እንድዳችሁ ፣ አሁን ፣ ከነ ፣ ነፍሴ ፣
አቃጥሉኝ ፣ በቁሜ ፣ ከእግር ፣ እስከ ፣ ራሴ ፣
ወደ ፣ አራዊት ፣ ጕሬ ፣ ጣሉኝ ፣ ወደ ፣ ዋሻ ፤
ሮሜዎ ፣ ከቀረ ፣ ምንም ፣ ባል ፣ አልሻ ።

አባ ፣ ሎራ ።

እኔም ፣ ባንቺ ፣ ነገር ፣ እጅግ ፣ ተጠብቤ ፣
ልጄ ፣ ሆይ ፣ ሐዘንሽ ፣ ተሰማኝ ፣ ለልቤ ፣

የሚቻልሽ ፡ ቢሆን ፡ ልብሽ ፡ የሚደፍር ፡
አድምጭኝ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ልስጥሽ፡አንድ ፡ ምክር
አሁን ፡ ተመልሰሽ ፡ ስትገቢ ፡ ከቤትሽ ፡
እንደዚህ ፡ በዬና ፡ ንገሪው ፡ ላባትሽ ፡
« ፈቃድህን ፡ ልፈጽም ፡ ፓሪስን ፡ አግብቼ ፡
« መጥቻለሁና ፡ ይኸው ፡ ተጸጽቼ ፡
« እንግዴህ ፡ ይደገስ ፡ ሰርጉ ፡ ይሰናዳ » ፤
አባትሽ ፡ ይህነን ፡ ነግረሽው ፡ ሲረዳ ፡
ይታረቃል ፡ ካንቺ ፡ መንፈሱም ፡ ይረጋል ፤
ከንዴቱ ፡ በርዶ ፡ ይቅርታ ፡ ያደርጋል ።
እኔም ፡ የምሰጥሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢረዳ ፡
አንድ ፡ መድኀኒት ፡ ነው ፡ ምንም ፡ የማይጐዳ ፡
ልብስሽን ፡ አውልቀሽ ፡ ስትተኝ ፡ ማታ ፡
ደብቀሽ ፡ ሰው ፡ ሳያይ ፡ ጠጪው ፡ በቀስታ ፡
ሌሊቱን ፡ ሳትሰሚ ፡ መድኀኒቱ ፡ ሠርቶ ፡
ነገ ፡ ጧት ፡ ከእንቅልፍሽ ፡ መነሣትሽ ፡ ቀርቶ ፡
ሞተሽ ፡ ትገኛለሽ ፡ ትንፋሽሽም ፡ ጠፍቶ ፡
ወስደው ፡ ይቀብሩሻል ፡ ሞታለች ፡ ተብሎ ፤
ለቤተ ፡ ሰባችሁ ፡ በሰፊው ፡ ተንጣሎ ፡
አምሮ ፡ በተሠራው ፡ በመቃብር ፡ ቤት ፡
ተኝተሽ ፡ ቈይተሽ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡

ታዝኖ ፡ ተለቅሶልሽ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡
ዐውቀሽ ፡ ትነሻለሽ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲሞላ ።
እስከዚያ ፡ እሠራለሁ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ተግቼ ፤
ደብዳቤ ፡ እጽፍና ፡ ሮሜዎን ፡ ጠርቼ ፡
እሱም ፡ በቬሮና ፡ ተደብቆ ፡ ገብቶ ፡
ወዳንቺ ፡ መቃብር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ መጥቶ ፡
አንቺ ፡ ሳትነሺ ፡ አጠገብሽ ፡ ደርሰን ፡
በምስጢር ፡ በፍጥነት ፡ ልብስሽን ፡ አልብሰን ፡
አንቺና ፡ ሮሜዎ ፡ ከዚህ ፡ ከከተማ ፡
ማንም ፡ ሳይጠረጥር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሳይሰማ ፡
ወጥታችሁ ፡ ሄዳችሁ ፡ የትም ፡ በሌላ ፡ አገር ፡
ዕረፍት ፡ አግኝታችሁ ፡ ያለ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
ኑሩልኝ ፡ በሰላም ፡ በፍጹም ፡ ደስታ ፡
ከናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ የእግዚአብሔር ፡ እርዳታ ።
ትጠጭው ፡ እንደሆን ፡ ዠልዬት ፡ ሳትፈሪ ፡
አስቢና ፡ ቶሎ ፡ ገልጠሽ ፡ ተናገሪ ፡
እኔም ፡ መድኀኒቱን ፡ ልስጥሽ ፡ አሁን ፡ ሳልቈይ ፤
ከዚህ ፡ በቀር ፡ ዘዴ ፡ የለኝም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ።

ዠልዬት ።

መልካም ፡ ነው ፡ አባቴ ፡ ያላንድ ፡ ቅሬታ ፡
ሳልፈራ ፡ እጠጣለሁ ፡ በትልቅ ፡ ደስታ ።

ደግሞስ ፣ በገዛ ፣ እጇ ፣ ለመሞት ፣ ስቃጣ ፣
ከዚህ ፣ የተሻለ ፣ ምን ፣ ዘዴ ፣ ሊመጣ ።
አባ ፣ ሎራ ፣ (ከጓዳ፣ገብተው፣መድኀኒቱን፣በብልቃጥ ፣ አመጡ)
እንግዲያውስ፡እንቺ ፣ ይኸው ፣ መድኀኒቱ ፤
እግዚአብሔር ፣ ልብሽን ፣ ያድርግልሽ ፣ ብርቱ ።

ዡልዬት ።

አዝነው ፣ ስለ ፣ ረዱኝ ፣ ልብዎ ፣ ስለ ፣ ራራ ፣
እግዚአብሔር ፣ ይስጥልኝ ፣ አባቴ ፣ አባ ፣ ሎራ ።

አባ ፣ ሎራ ።

ግድ ፣ የለሽም ፣ ልጄ ፣ ሳልዘገይ ፣ ፈጥኜ ፣
እንደ ፣ ምንም ፣ ብዬ ፣ አንድ ፣ ቄስ ፣ ለምኜ ፣
ወደ ፣ ሮሜዎ ፣ ዘንድ ፣ ጒዳዩን ፣ ሸሽጌ ፣
ደብዳቤውን ፣ ጽፌ ፣ በምስጢር ፣ አድርጌ ፣
እልክለታለሁ ፣ በቶሎ ፣ እንዲመጣ ፣
ዡልዬት ፣ በኔ ፣ ጣዪው ፤ የቀረውን ፣ ጣጣ ።

ትይንት ፣ ፪ ።

ካፑሌ ፣ የካፑሌ ፣ ሚስት ፣ ዡልዬት ።
(ዡልዬት ፣ ከውጭ ፣ መጣች) ።

ካፑሌ ።

በጣም ፣ ያሳዝናል ፣ ባሕሪሽ ፣ ተበላሸ ፤
ወዴት ፣ ሄደሽ ፣ ኖሯል ፣ ደግሞ ፣ እንዲህ ፣ ከመሸ ፣

ዡልዬት ።

ወደ ፣ አባ ፣ ሎራ ፣ ዘንድ ፣ ደርሼ ፣ ነበረ ፤
ምክራቸው ፣ ገሠጸኝ ፣ ልቤ ፣ ተሰበረ ፣
ያንተን ፣ ያባቴን ፣ ቃል ፣ ልፈጽም ፣ ፈቅጄ ፣
የምጠላውን ፣ ሰው ፣ ስላንተ ፣ ወድጄ ፣
ፓሪስን ፣ ላገባ ፣ ሆኛለሁ ፣ ዝግጁ ፤
ሰርጌ ፣ ይሰናዳ ፣ ሁሉንም ፣ አብጁ ፣
ደግሞም ፣ ብለውኛል ፣ አጥብቀው ፣ በብርቱ ፣
« ምሕረቱን ፣ ለምኚ ፣ ወድቀሽ ፣ ከጕልበቱ » ፣
(ተንበረከክች) ።

ንጼት ፣ አይግባችሁ ፣ በኔ ፣ የተነሣ ፤
ያለፈው ፣ ጥፋቴ ፣ እንግዴህ ፣ ይረሳ ፣
የሰላም ፣ ቤት ፣ ይሁን ፣ ያለም ፣ የደስታ ፣
ለኔም ፣ ለልጃችሁ ፣ አድርጉ ፣ ይቅርታ ።

ካፑሌ ።

እንዲህ ፣ ያለ ፣ ካህን ፣ እግዜር ፣ የባረከው ፣
ምክሩ ፣ ንግግሩ ፣ ለሰው ፣ የሚሰብከው ፣
ከጻድቅ ፣ የመጣ ፣ ንጹሕ ፣ በመሆኑ ፣
ጠልቆ ፣ ልብ ፣ ይገባል ፣ ያጠግባል ፣ በውኑ ፣
እስቲ ፣ አሁን ፣ ባሁን ፣ እንደ ፣ ምን ፣ አድርጎ ፣
መልሶ ፣ ላከልኝ ፣ አንቺን ፣ ወደ ፣ በጎ ።

(ከተንበረከክችበት ፡ ቦታ ፡ ያስነሣታል ።)

ተነሺ ፡ ከመሬት ፡ ይብቃ ፡ አትንበርከኪ ፡
ምክሩን ፡ መከተልሽ ፡ አንቺም ፡ ተባረኪ ።

(ወደ ፡ ሚስቱ ፡ መለስ ፡ ብሎ)።

እንግዴህ ፡ ይፋጠን ፡ ይቀጥል ፡ ድግሡ ፤
አሽከሮቹ ፡ ሁሉ ፡ በሌሊት ፡ ይነሡ ፡
ተክሊሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ ነግ ፡ በማለዳ ፡
ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ዛሬ ፡ ይሰናዳ ።

ትይንት ፡ ፫ ። (ብካፑሌ ፡ ቤት ፡ ጫ

ካፑሌ ።

ሰዎቼ ፡ ተኝተው ፡ ሳይነሡ ፡ ካልጋ ፡
ወፎቹ ፡ ተንጫጩ ፡ ይኸው ፡ ሌቱ ፡ ነጋ ፡
ተነሡ ፡ ረፈደ ፡ እሳቱን ፡ አንድዱ ፤
መብሉን ፡ መጠጡን ፡ በቶሎ ፡ አሰናዱ ።

የገዮልዬት ፡ ሞግዚት ፡

ርስዎ ፡ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ ጨርሰው ፡ ሳይተኙ ፡
ቁጭ ፡ ብለው ፡ ነጋ ፡ ሥራውን ፡ ሲቃኙ ፡
በጣም ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ጥቂት ፡ ቢያር

ካፑሌ ።

አታስቡ ፡ ለኔ ፡ ይልቅ ፡ አትስነፉ ፡
አያሽንፈኝም ፡ ዱሮም ፡ ቢሆን ፡ እንቅልፍ ፡
መብልና ፡ መጠጥ ፡ ደኅና ፡ የሚያሳልፍ ፡

ኈት ፡ አገኝ ፡ ይሆን ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው ፤
ምንም ፡ ሳይዘጋጅ ፡ አንዱንም ፡ ሳንይዘው ፡
ስትተራመሱ ፡ እንዲሁ ፡ በከንቱ ፡
የሙሽራው ፡ መምጫ ፡ ደረሰ ፡ ሰዓቱ ፡
ዕቃ ፡ ማነሱ ፡ ነው ፡ አንዱም ፡ የሚያውከው ፡

(አሽከሮቹ ፡ ገቡ ፡ በያይነቱ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው) ።

ምንድነው ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ ይህ ፡ የተሸከምከው ?

አሽከር ።

የጠቦት ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ለጥብስ ፡ የታረደ ።

ካፑሌ ።

በል ፡ ፍጠን ፡ ቶሎ ፡ በል ፡ ሰዓቱ ፡ ረፈደ ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

ከምን ፡ ጊዜ ፡ ነጋ ፡ አለፈ ፡ ሌሊቱ ፤

ካፑሌ ።

አንቺን ፡ አይጠብቅም ፡ ጊዜና ፡ ሰዓቱ ፡
ሙሽራው ፡ ይመጣል ፡ አንዱን ፡ ሳትጨብጪው ፤
የሚያስፈልገውን ፡ ለወጥ ፡ ቤቱ ፡ ስጪው ፡
አለዚያ ፡ ሲቸኮል ፡ ይበላሻል ፡ ወጡ ፡
አንችም ፡ ቶሎ ፡ ልበሽ ፡ ሰርገኞች ፡ ሳይመጡ ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

ዠልዬት ፡ ሳትነሣ ፡ እኔም ፡ ልብሴን ፡ ሳልለብስ፣
በጣም ፡ ያስደንቃል ፡ የሰዓቱ ፡ መድረስ ፡
እመጣለሁ ፡ ብሏል ፡ ፓሪስ ፡ በመዚቃ ፡
እንግዴህ ፡ ዠልዬትም ፡ መተኛት ፡ ይብቃ።

(ሞግዚቷ ፡ ገባች) ።

እንዴት ፡ ረፈደ ፡ በጣም ፡ ያስገርማል ፤
ሰርገኞቹ ፡ መጡ ፡ መዚቃው ፡ ይሰማል ፡
እባክሽ ፡ ፍጠኚ ፡ ቶሎ ፡ በይ ፡ አስነሻት ፤
ገላዋን ፡ ትታጠብ ፡ ልብሷንም ፡ አልብሻት ፡
ቶሎ ፡ እንደ ፡ ጨረስሽ ፡ ለብሳና ፡ አጊጣ ፡
እብራችሁ ፡ ካንቺ ፡ ጋር ፡ ወደኛ ፡ እንድትመጣ፣
እኔም ፡ ሰርገኞቹን ፡ እስከዚያ ፡ ልቀበል ፤
እሽክር ፡ በሩን ፡ ክፈት ፡ እባክህ ፡ ቶሎ ፡ በል ።

ትይንት ፡ ፬ ።

በዠልዬት ፡ መኝታ ፡ ቤት ።

ሞግዚት ፡ (ዠልዬትን፣ትቀሰቅሳለች) ።

ተነሺ ፡ ረፈደ ፡ ዠልዬት ፡ እመቤቴ ፤
ተነሺ ፡ ይሉሻል ፡ እናትሽ ፡ እሚቴ ፡
ሰርገኞች ፡ ሲመጡ ፡ መዚቃ ፡ ሲሰማ ፡
አትንቀሳቀስም ፡ እሷ ፡ ግን ፡ ፊጽማ ፤
ምነው ፡ ምን ፡ ሆንሽብኝ ፡ ተነሺ ፡ እንጂ ፡ ቶሎ ፤

አንቺን ፡ ይጠብቃል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቸኩሎ ።
(ገልጣ ፡ ታያታለች) ።

እኔ ፡ ጠፋሁ ፡ ዛሬ ፡ ያለትንሹሽ ፡ ቀርታ ፡
ገላዋ ፡ ቀዝቅዟል ፡ እመቤቴ ፡ ሞታ ፡
እረ ፡ ትልቅ ፡ ጉድ ፡ ነው ፡ ኑ ፡ ቶሎ ፡ ድረሱ !

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

ማነው ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ የሚጮኸው ፡ እሱ ?

ሞግዚት ።

አሁን ፡ በገደለኝ ፡ መሬት ፡ እኔን ፡ ውጦ ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

አትጩሂ ፡ እባክሽ ፡ እንግዳ ፡ ተቀምጦ ።

ሞግዚት ።

ልጅዎን ፡ ያስተውሏት ፡ በመኝታ ፡ ቤቷ ፤

የካፑሌ ፡ ሚስት ፡ (ገባች) ።

ለምን፡ነው ፡ እስካሁን ፡ አለመነሣቷ ?
ልጄ ፡ ዠልዬት ፡ ተነሽ ፡ ዐይንሽን ፡ ግለጪ ፤
አባቷን ፡ ጥሩልኝ ፡ በቶሎ ፡ ከውጪ ፡
ልጄን ፡ ምን፡ አገኛት ፡ ሞታለች ፡ ጨርሶ ።

ካፑሌ ፡ (ገባ) ።

እንግዲህ ፡ መንጫጫት ፡ ይወዳሉ ፡ ደርሶ ፡
ዠልዬት ፡ አትመጣም ፡ ወይ ፡ ሙሽራው ፡ ሲጠብቅ?

ሞግዚት ።

ሞታለች ፣ ሞታለች ፣ ጒድ ፣ ነው ፣ የሚያስደንቅ ።

የካፑሌ ፣ ሚስት ።

ሞታለች ፣ የት ፣ ልግባ ፣ ጒድ ፣ ነው ፣ አወይ ፣ ልጂ
ምን ፣ መድኀኒት ፣ ላምጣ ፣ ወዴት ፣ ስፍራ ፣ ሄጂ ።

ካፑሌ ።

ቄዩ፣እስቲ፣እኔ፣ልያት፣ የታለች ፣ ቀዝቅዛ ፣ (እየዳበሳት)
ፈጽማ ፣ ሞታለች ፣ በምን ፣ ጒዴ ፣ በዛ ።
ሌሊት ፣ በጨለማ ፣ ፀሓይዋ ፣ ሳትወጣ ፣
ልጂ ፣ አበባዬ ፣ ወድቃለች ፣ ተቈርጣ ።

ሞግዚት ።

የተረገመ ፣ ነው ፣ አወይ ፣ የዛሬ ፣ ቀን ፤

የካፑሌ ፣ ሚስት ።

ምነው ፣ ብንቀበር ፣ ሁላችንም ፣ አልቀን !

ካፑሌ ።

ምንም ፣ አልናገር ፣ ምላሴ ፣ ታሰረ ፤
ልሳኔ ፣ በሐዘን ፣ ተቈልፎ ፣ ቀረ ።

(አባ ፣ ሎራና ፣ ፓሪስ ፣ በሙዚቃ ፣ ገቡ ።)

አባ ፣ ሎራ ።

ወደ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ እንሂድ ፣ ፍጠኑ ፤
ሙሽራዋን ፣ ጥሩ ፣ እናንተም ፣ ቶሎ ፣ ኑ ።

ካፑሌ ።

ጒድ ፣ ሆነናል ፣ ዛሬ ፣ ይተዉኝ ፣ አባቴ ፤

ጒድ ፣ ለማየት ፣ ኖሯል ፣ የቈየች ፣ ሕይወቴ ፣
እኔ ፣ ወዴት ፣ ልድረስ ፣ የት ፣ አባቴ ፣ ልግባ ፤
ሞቶች ፣ ተቀጠፈች ፣ ልጂ ፣ የኔ ፣ እበባ ።
እናቷ ፣ ሳታስብ ፣ አባቷ ፣ ሳይሰማ ፣
ሞት ፣ የሚባል ፣ ሌባ ፣ ሌሊት ፣ በጨለማ ፣
ለካ ፣ ከቤታችን ፣ ገብቶ ፣ ተደብቆ ፣
ይዟት ፣ ሄዶ ፣ ኖሯል ፣ ልጃችንን ፣ ሰርቆ ፤
እንዴት ፣ ጒድ ፣ ሆነናል ፣ እንዲህ ፣ ተደግሶ ፣
ሰርጓ ፣ ሐዘን ፣ ሆነ ፣ ደስታችን ፣ ለቅሶ ።

ፓሪስ ።

እኔ ፣ ዕድለ ፣ ቢሱ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ መርዶ ፣
እንዴት ፣ ያለ ፣ ሐዘን ፣ ጠበቀኝ ፣ ተወልዶ ።

የካፑሌ ፣ ሚስት ።

የተረገመ ፣ ነው ፣ አወይ ፣ የዛሬ ፣ ቀን ፣
ቀረን ፣ እኮ ፣ ሰዎች ፣ እንደዚህ ፣ ተሳቀን ፣
ያይኖቼ ፣ ማረፊያ ፣ ብትኖረኝ ፣ አንዲት ፣ ልጅ ፣
ያንድ ፣ ቀን ፣ ደስታ ፣ ለማየት ፣ ስዘጋጅ ፣
ለማን ፣ አቤት ፣ ልበል ፣ ሞት ፣ ይዞብኝ ፣ ሄደ ፤
ሆዴ ፣ ተቃጠለ ፣ አንጀቴ ፣ ነደደ ።

አባ ፣ ሎራ ።

ይብቃ ፣ ለሐዘኑ ፣ አድርጉለት ፣ መጠን ፤
አስቡ ፣ ይችን ፣ ልጅ ፣ እግዜር ፣ ነው ፣ የሰጠን ፣

አሁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰዳት ፡ መልሶ ፤
ሐዘናችሁ ፡ አይሁን ፡ ያረመኔ ፡ ለቅሶ ፡
ቀረባት ፡ ብላችሁ ፡ የመሬት ፡ ደስታ ፡
ጸጸታችሁ ፡ አይሁን ፡ በጣም ፡ የበረታ ፡
የመሬት ፡ ደስታ ፡ ምንም ፡ የለው ፡ ዋጋ ፤
ይልቅ ፡ አይበልጥም ፡ ወደ ፡ የሰማይ ፡ ቤት ፡ ጸጋ
ከሚያልፍ ፡ ዓለም ፡ ወጥታ ፡ ከዘለዓለም ፡ ቤቷ ፡
መተላለፍ ፡ ነው ፡ በሰላም ፡ መግባቷ ፡
መሆኑ ፡ ቀረና ፡ ሰርጓ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፤
ብርሃን ፡ ወዳለበት ፡ ሄደች ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡
እናድርጋት ፡ ስንል ፡ ምድራዊት ፡ ሙሽራ ፡
አይሆናትም ፡ ብሎ ፡ የመሬት ፡ መከራ ፡
ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ የላቀ ፡ ደስታ ፡ አዘጋጅቶ ፡
እግዚአብሔር ፡ ወሰዳት ፡ በፈቃዱ ፡ ጠርቶ ፡
የሰርግ ፡ ልብሷን ፡ ብሳ ፡ እንዳማረች ፡ በክብር ፡
በሉ ፡ ያዟትና ፡ እንሂድ ፡ መቃብር ።

አምስተኛ ፡ አክት ።

ትይንት ፡ ፩ ።

ሮሜዎ ። (በተሰደደበት ፡ አገር ፡ ሆኖ) ።

መሠረት ፡ ቢኖረው ፡ የኔ ፡ ሕልም ፡ ዛሬ ፡
አገኝ ፡ ይመስለኛል ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ወሬ ፡

ገቦልዬት ፡ ስትመጣ ፡ ስታገኝኝ ፡ ሞቼ ፡
አልቅሳ ፡ ስትስመኝ ፡ እኔ ፡ ተዘርግቼ ።
ኋላም ፡ በሷ ፡ ትንፋሽ ፡ ሕይወቴን ፡ አድሼ ፡
ከሞት ፡ ተነሥቼ ፡ አየሁኝ ፡ ነግሼ ።
በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡ ዛሬ ፡ ዉት ፡ ጀምሮ ፤
ሰላም ፡ ይሰማኛል ፡ የመንፈስ ፡ የአእምሮ ።

(ቤልሻጥር ፡ ቦት ፡ ጫማ ፡ አድርጎ ፡ መጣ) ።

ቤልሻጥር ፡ ጐበዙ ፡ እንኳን ፡ ገባህ ፡ ደኅና ፡
ምን ፡ ወሬ ፡ ይዘህ ፡ መጣህ ፡ ዛሬ ፡ ከቤሮና ?
ገቦልዬት ፡ ደኅና፡ነች፡ወይ፧አባቴስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
እሷ ፡ ደኅና ፡ ብትሆን ፡ ግድ ፡ የለም ፡ የቀረው ።
ገቦልዬት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነች ? አሁንም ፡ አድሼ ፡
ልጠይቅህ ፡ በጣም ፡ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ መልሼ ።

ቤልሻጥር ።

ደኅና ፡ ነች ፡ ልበልህ ፡ አልነካትም ፡ ዐፈር ፤
እንደሌላው ፡ ፍጥረት ፡ መሬት ፡ ሳትቀበር ፡
ከመቃብሩ ፡ ቤት ፡ ሠርተው ፡ አባቶቹ ፡
ካዘጋጁት ፡ ገብታ ፡ እግሮቿም ፡ እጆቿ ፡
ታስረው ፡ ሳትገነዝ ፡ በማዕርግ ፡ ተንጋላ ፡
ተኝታ ፡ አየናት ፡ ያንቀላፋች ፡ መስላ ።
እንዲህ ፡ በጌትነት ፡ ዝልዬት ፡ ተቀበረች ፤
በቃ ፡ የሷ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ዘበት ፡ ቀረች ።

ነፍሷ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዜር ፡ ዐረገች ፡ ወደ ፡ ላይ ፤
ዐርፋ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ወጣች ፡ ወደ ፡ ሰማይ ።
ሮሜዎ ። (ዐድንጋጤ ፡ ፊቱ ፡ ተለወጠ) ።
ምን ፡ አገኛትና ? በምን ፡ የተነሣ ?

ቤልሻጥር ።

ጧት ፡ ባልጋዋ ፡ ላይ ፡ በድን ፡ ሆና ፡ ሬሳ ፡
ተገኘች ፡ ከእንቅልፏ ፡ ሳትነቃ ፡ ሞታ ፤

ሮሜዎ ።

እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ የዠልዬት ፡ ሁኔታ ፡
ደግ ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ብርዕ ፡ ቀለም ፡ እምባ
ፈረሶች ፡ ተከራይ ፡ ፈጥነህ ፡ መንደር ፡ ውጣ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያየኝ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሳይሰማ ፡
መሪዴ ፡ ነውና ፡ ሌሊት ፡ በጨለማ ።

ቤልሻጥር ።

እባክህ ፡ ጌታዬ ፡ ፊትህ ፡ ተለወጠ ፤
ደምህም ፡ ጠቈረ ፡ ልቤ ፡ ደነገጠ ፡
ቻለው ፡ ሐዘንህን ፡ ከትዕግሥት ፡ ጋራ ።

ሮሜዎ ።

አትሥጋ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ቤልሻጥር ፡ አትፍራ ።
የማይሆን ፡ አይሆንም ፡ የሚሆን ፡ ይሆናል ፤

ይልቅ ፡ ቶሎ ፡ ፍጠን ፡ ጊዜው ፡ ያልፍብናል ።
(ቤልሻጥር ፡ ሄደ ፤ ሮሜዎ ፡ ብቻውን) ።
እንገናኛለን ፡ ዠልዬት ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፤
ወዳንቺ ፡ ለመድረስ ፡ ቶሎ ፡ በደስታ ፡
መንገዱን ፡ መፈለግ ፡ አለብኝ ፡ ግዬታ ፡
መድኀኒት ፡ የሚሸጥ ፡ አንድ ፡ ጎረቤቴ ፡
መኖሩን ፡ ዐውቃለሁ ፡ እኔ ፡ በሕይወቴ ፡
አይቼ ፡ አላውቅም ፡ ችግረኛ ፡ እንደ ፡ እሱ ፤
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያደፈ ፡ ቀዳዳ ፡ ነው ፡ ልብሱ ፡
የተጐዳ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ድህነት ፡ ያጠቃው ፤
ሰውነቱ ፡ ከስቷል ፡ የመደብር ፡ ዕቃው ፡
አሮጌ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ቄሻሻ ፡ ሰባራ ፤
ተጠርጎ ፡ የማያውቅ ፡ የለበሰ ፡ ዐቢራ ።
ከሱቁ ፡ ስገባ ፡ እኔም ፡ አስተውዬ ፡
እሱን ፡ ባየሁ ፡ ቅጥር ፡ አሰብኩ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፤
በማንቱ ፡ ከተማ ፡ ለሰው ፡ መርዝ ፡ የሸጠ ፡
በምንም ፡ አኳኋን ፡ አውጥቶ ፡ የሰጠ ፡
ምንም ፡ እንኳ ፡ የሚያዝ ፡ በሞት ፡ እንዲቀጣ ፡
ጎይለኛ ፡ ዐዋጅ ፡ ቢኖር ፡ ተጽፎ ፡ የወጣ ፡
መርዝ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ግንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡
ይህን ፡ ችግረኛ ፡ ቢጠይቀው ፡ መጥቶ ፡

አይጠረጠርም ፣ እንቢ ፣ እንደማይለው ፤
ስለዚህ ፣ ጠርቼ ፣ እስቲ ፣ ልሞክረው ፣
አንተ ፣ መድኀኒት ፣ ሽያጭ ፣ እባክህ ፣ ወዲህ ፣ ና ፣
መድኀኒት ፣ ሽያጭ ።
ምነው ፣ ሮሜዎ ፣ አይዶለም ፣ ወይ ፣ ደኅና ?
ሮሜዎ ።
ሰው ፣ አንተን ፣ ይሻሃል ፣ ባጣ ፣ ጊዜ ፣ ጤና ፣
አንድ ፣ ነገር ፣ አሁን ፣ ልንገርህ ፣ አድምጠኝ ፤
ቶሎ ፣ የሚገድል ፣ ብርቱ ፣ መርዝ ፣ ስጠኝ ፣
አርባ ፣ ዱካ ፣ ልስጥህ ፣ ለመርዝህም ፣ ዋጋ ፤
አንተም ፣ ትሆናለህ ፣ በዚህ ፣ ባለጸጋ ፣
አንተን ፣ ለመሰለ ፣ በጣም ፣ ለተጐዳ ፣
ይህ ፣ ብዙ ፣ ገንዘብ ፣ ነው ፣ በጣም ፣ የሚረዳ ።
መድኀኒት ፣ ሽያጭ ።
ኀይለኛ ፣ መርዝ ፣ አለኝ ፣ በመደብሬ ፣ ውስጥ ፣
ግን ፣ ባዋጅ ፣ ክልክል ፣ ነው ፣ ለማንም ፣ እንዳልሸጥ ፣
ሮሜዎ ።
ሞኝ ፣ ነህ ፣ መሰለኝ ፣ ዐዋጅ ፣ ብሎ ፣ ጣጣ ፣
ራብ ፣ ለገደለህ ፣ ዐጥንትህ ፣ ለወጣ ፣
ሳንቲ ፣ ምን ፣ ጠቀመህ ፣ ይልቅ ፣ ስጠኝ ፣ ቶሎ ፤
ድኽነት ፣ ይታያል ፣ በመልክህ ፣ ተሥሎ ፣
ጕዳት ፣ አቈራምዶ ፣ ችግር ፣ ያሸነፈህ ፣

ክሕጉስ ፣ ካዋጁስ ፣ ላንተ ፣ ምን ፣ ተረፈህ ፣
እንዲህ ፣ ያለ ፣ ገዢ ፣ ሁል ፣ ጊዜ ፣ አታገኝም ፤
ፍጠን ፣ ቸኩያለው ፣ ጊዜ ፣ እኔ ፣ የለኝም ።
መድኀኒት ፣ ሽያጭ ።
ኅሊና ፣ አገደኝ ፣ ችግር ፣ ሲገፋፋኝ ።
ሮሚዎ ።
በከንቱ ፣ ክርክር ፣ እባክህ ፣ አታልፋኝ ።
መድኀኒት ፣ ሽያጭ ።
በል ፣ እንካ ፣ ይህንን ፣ በውሃ ፣ በጥብጠህ ፣
ጠጣው ፣ ስትፈልግ ፣ በሙሉ ፣ ጨልጠህ ፣
እንደ ፣ ሶምሶን ፣ እንኳ ፣ ኀይልህ ፣ ቢበረታ ፣
ክንትር ፣ ያደርግሃል ፣ በቅጽበት ፣ አንድ ፣ አፍታ ።
(መርዝ ፣ ሰጠው ።)
ሮሜዎ ።
አንተም ፣ እንካ ፣ ውሰድ ፣ ወርቁን ፣ ተቀብለህ ፤
አትፍራ ፣ በከንቱ ፣ መርዝ ፣ ሸጥኩ ፣ ብለህ ፣
ዋና ፣ መርዝ ፣ ወርቅ ፣ ነው ፣ ከሁሉም ፣ የከፋ ፣
ብዙ ፣ ሕዝብ ፣ የፈጀ ፣ ዓለምን ፣ ያጠፋ ፣
ዐዐ ርዝህን ፣ ወሰድኩት ፣ ስጥቼ ፣ ሌላ ፣ መርዝ ፣
ክፉ ፣ ሠራሁ ፣ ብለህ ፣ ሰቂስ ፣ አትናዘዝ ።

ትይንት ፡ ፪ ።

በአባ ፡ ሎራ ፡ ቤት ።

አባ ፡ ዮሐንስ ፡ (ከውጭ ፡ መጣ) ።

ወዴት ፡ ነው ፡ ያለኸው ፡ አባቴ ፡ አባ ፡ ሎራ ?

አባ፡ ሎራ ።

ተሳሳትኩ ፡ ብዬ ፡ በልቤ ፡ ባልፈራ ፡

በድምፅህ ፡ መሰልከኝ ፡ የኛ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ።

አባ ፡ ዮሐንስ ።

ዐውቀሃል ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

አባ ፡ ሎራ ።

አንተ ፡ እስክትመለስ ፡

እጠብቅህ ፡ ነበር ፡ ቸኵዬ ፡ ባሳቤ ፡

ፈጥነህ ፡ ደረስክልኝ ፡ ስሠጋ ፡ በልቤ ፡

መልሱን ፡ ከሮሜዎ ፡ ለጻፍኩት ፡ ደብዳቤ ፡

አመጣህልኝ ፡ ወይ ? እስቲ ፡ ቶሎ ፡ ስጠኝ ፤

አባ ፡ ዮሐንስ ።

የሆንኩትን ፡ ነገር ፡ ልንገርህ ፡ አድምጠኝ ፡

ደብዳቤህን ፡ ቶሎ ፡ ለመስጠት ፡ ወስጄ ፡

አንዱን ፡ የኛ ፡ ካህን ፡ ልፈልገው ፡ ሄጄ ፡

ወደ ፡ ሮሜዎ ፡ ቤት ፡ እንዲወስድኝ ፡ መርቶ ፡

እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ሊወስደኝ ፡ ተነሥቶ ፡

ዘበኞች ፡ መጡና ፡ ከቤት ፡ እንዳንወጣ ፡

ዘግተውብን ፡ ሄዱ ፤ ከውጭ ፡ የመጣ ፡

በሽታ ፡ ስላለ ፡ ማንም ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡

ሲመጣ ፡ አስቀድሞ ፡ ለካ ፡ እስቲመረመር ፡

ለብቻው ፡ እንዲሆን ፡ የወጣው ፡ ሥራቱ ፡

የሚያስገድድ ፡ ኖሮ ፡ ሳልሄድ ፡ ወደ ፡ ማንቱ ፡

ሮሜዎን ፡ ሳላገኝ ፡ ሳላየው ፡ ደርሼ ፡

ያንተንም ፡ ደብዳቤ ፡ አመጣሁ ፡ መልሼ ።

ልልከው ፡ አስቤ ፡ ብሞክር ፡ ብለፋ ፡

ብጠይቅ ፡ ባስጠይቅ ፡ የሚላክ ፡ ሰው ፡ ጠፋ ፡

አልሆንልህ ፡ አለኝ ፡ ነገሩ ፡ አልሳካ ፤

ይቅርታ ፡ አድርግልኝ ፡ ደብዳቤህን፡እንካ ። (ሰጠው)።

አባ ፡ ሎራ ።

ምንኛ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ ያመጣኸው ፡ ወሬ !

አይ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ጉድ ፡ ሠራኸኝ ፡ ዛሬ ።

መልክቴ ፡ በውነቱ ፡ ትልቅ ፡ ጉዳይ ፡ ነበር ፤

በጣም ፡ የከበደ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡

ባለመፈጸሙ ፡ የመልክቴ ፡ አደራ ፡

እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ በጣም ፡ የሚያስፈራ ፡

ነገር ፡ ለማስከተል ፡ ይችላል ፡ ወዳጄ ፤

ጽፌ ፡ የሰጠሁህ ፡ ያ ፡ ወረቀት ፡ በእጄ ፡

ለሮሜዎ ፡ ቶሎ ፡ መድረስ ፡ ነበረበት ፤

አይ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ጉድ ፡ ሠራኸኝ ፡ በውነት !

እባክህ ፣ አሁንም ፣ ቶሎ ፣ እንረዳዳ ፤
ጒጠት ፣ ፈልግና ፣ አምጣልኝ ፣ ከጓዳ ።

አባ ፣ ዮሐንስ ።

ሳልችል ፣ ቀርቼ ፣ ነው ፣ በጣም ፣ ተቸግሬ ፣
ምን ፣ ሁን ፣ ትለኛለህ ፣ ስቀመጥ ፣ ታስሬ ፣
እንዴት ፣ ብዬ ፣ ልሂድ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ አድርጌ ፤
መልካም ፣ ነው ፣ ጒጠቱን ፣ ላምጣልህ ፣ ፈልጌ ፣

(አባ ፣ ዮሐንስ ፣ ወደ ፣ ጓዳ ፣ ገባ) ።

አባ ፣ ሎራ ፣ (ብቻውን) ።

ከዙልዬት ፣ መቃብር ፣ ብቻዬን ፣ ገሥግሼ ፣
መዝጊያውን ፣ ልከፍተው ፣ በቶሎ ፣ ደርሼ ፤
መድረስ ፣ ይገባኛል ፣ በቶሎ ፣ በቅጽበት ፤
ጊዜው ፣ ደርሷልና ፣ የምትነሣበት ።
በተነሣች ፣ ጊዜ ፣ ሮሜዎን ፣ ስታጣ ፣
እንደ ፣ ምን ፣ ትረግመኝ ፣ በንዴት ፣ በቍጣ ፣
አምቼ ፣ ላስቀምጣት ፣ ከቤቴ ፣ ሸሽጌ ፤
ከዚያም ፣ እንደ ፣ ገና ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ፈልጌ ፣

ደግሞ ፣ ለሮሜዎ ፣ ሲሆን ፣ ዛሬ ፣ ማታ ፣
ጽፌለት ፣ ይመጣል ፣ ሁሉንም ፣ ሐተታ ።
ትይንት ፣ ፫ ።

(ፓሪስ ፣ ካሽከሩ ፣ ጋር ፣ አበባና ፣ ሙሐራት ፣ ይዞ ፣ ወደ ፣ ገዖልዬት ፣ መቃብር ፣ መጣ) ።

ፓሪስ ።

መብራቱንም ፣ አጥፋው ፣ እንግዲህ ፣ ይበቃል ፤
ሰው ፣ የመጣ ፣ እንደሆን ፣ ምናልባት ፣ ማን ፣ ያውቃል ፣
እዚህ ፣ ሰው ፣ እንዲያየኝ ፣ አልፈልግምና ፤
በል ፣ ቅረብ ፣ ተጠጋ ፣ አንተም ፣ ወደዚህ ፣ ና ።
ጒሮህን ፣ አቁመህ ፣ ተጠንቅቀህ ፣ ስማ ፤
ኰሽታ ፣ ስትሰማ ፣ ወይም ፣ የሰው ፣ ጫማ ፣
ምልክት ፣ እንዲሆን ፣ አፍጭተህ ፣ አስታውቀኝ ፣
አስቀድሜ ፣ እንዳውቀው ፣ ፈጥነህ ፣ አስጠንቅቀኝ ፤
በል ፣ እንግዲህ ፣ አሁን ፣ አበባውን ፣ ስጠኝ ።

(ፓሪስ ፣ ሄደ) ።

አሽከር ፣ (ብቻውን) ።

የተሻለ ፣ ስፍራ ፣ ባገኝ ፣ ደግ ፣ ነበር ፤
ይህ ፣ ቦታ ፣ ቀፈፈኝ ፣ አልወድም ፣ መቃብር ።

(አልፍ ፣ ብሎ ፣ ሄደ) ።

ፓሪስ ። (በዙልዬት ፣ መቃብር ፣ ላይ) ።

ይህንን ፣ አበባ ፣ መርጬ ፣ ፈልጌ ፣
ላቀርብልሽ ፣ መጣሁ ፣ በረከት ፣ አድርጌ ።

ገጸ ፡ በረከቱ ፡ ጸጸት ፡ ነው ፡ አበባ ፤
ሐዘን ፡ ነው ፡ ለቅሶ ፡ ነው ፡ የመረረ ፡ እንባ ፡
ትተሽኝ ፡ ብትሄጂ ፡ ብቻዬን ፡ ቀርቼ ፡
ልጐበኝሽ ፡ መጣሁ ፡ ሌሊት ፡ ተነሥቼ ።

(አሽከሩ ፡ አፏጨ) ።

እንሆ ፡ አፍጨ ፡ ሰማሁት ፡ አሽከሬ ፤
አሁን ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ አውሬ ፡
ሰላም ፡ የሚነሳኝ ፡ ማነው ፡ ባሁን ፡ ሰዓት ?
እንዴት ? ደግሞ ፡ ያውም፡ይዚል ፡ በእጁ ፡ መብራት
እስክረዳው ፡ ድረስ ፡ ምስጢሩን ፡ ዐውቄ ፡
ከለላ፡ፈልጌ፡ልየው ፡ ተደብቄ ። (እልፍ ፡ ብሎ ፡ ተደበቀ)

(ሮሜዎና ፡ ቤልሻጥር ፡ መብራትና ፡ ጉጠት ፡ ይዘው ፡ መጡ) ።

ሮሜዎ ።

በል ፡ መብራቱን ፡ ስጠኝ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ተመለስ
እገባለሁ ፡ እኔ ፡ መቃብሯ ፡ ድረስ ፤
አንተ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ እንዳትንቀሳቀስ ፡
ገሮሀን ፡ አቁመህ ፡ ሰው ፡ ሲመጣ ፡ ስማ ፤
ተደብቀህ ፡ ጠብቅ ፡ እዚህ ፡ በጨለማ ።
ያየህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ ወዲህ ፡ ሲመጣ፡
ከተደበቅህበት ፡ ቦታ ፡ ሳትወጣ ፡

በፉጨት ፡ ምልክት ፡ እኔን ፡ አስጠንቅቀኝ ፤
ምናልባት ፡ ሰው ፡ ደርሶ ፡ ድንገት ፡ እንዳያያዥኝ ።
የገቦልዬት ፡ ሬሳ ፡ ካለበት ፡ ገብቼ ፡
በመቃብሯ ፡ ውስጥ ፡ እሷን ፡ ተመልክቼ ፡
ካየኋት ፡ በኋላ ፡ ከልቤ ፡ አልቅሼ ፡
አንብቼ ፡ ሲያበቃኝ ፡ ሐዘኔን ፡ ጨርሼ ፡
የጣቷን ፡ ቀለበት ፡ አውልቄ ፡ ከሷ ፡ ላይ ፡
ልወስድ ፡ አስቤያለሁ ፡ ላንድ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳይ ።
ከወጣሁ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡
ይህንን ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረህ ፡ ሰላምታ ፡
ላባቴ ፡ ስጥልኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተጠንቀቅ ፤
ምን ፡ ይሠራል ፡ ብለህ ፡ አሳቤን ፡ ለማወቅ ፡
መሰለል ፡ አስበህ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አትጠጋ ፤
ያገኝሃልና ፡ የመሞት ፡ አደጋ ፡
በውነቱ ፡ ባገኝህ ፡ ይህንን ፡ ስትሠራ ፡
እጄም ፡ አያዝንልህ ፡ መንፈሴም ፡ አይራራ ፤
ልብ ፡ በል ፡ ተጠንቀቅ ፡ ለሕይወትህ ፡ ፍራ ።

ቤልሻጥር ።

እኔ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ አልንቀሳቀስም ፤
ስታስጠነቅቀኝ፡ትእዛዝ ፡ አላፈርህም ። (ሮሜዎ ፡ ሄደ)።

ሮሜዎ ፣ (የዝምልዱትን ፣ የመቃብርዋን ፣ በር ፣
ሲከፍት ፣ ይታገላል) ።

ከጥንት ፣ ጀምረህ ፣ ብትበላ ፣ ብትበላ ፣
ጠገብኩኝ ፣ የማትል ፣ ሆድህ ፣ የማይሞላ ፣
መቃብር ፣ የሚሉህ ፣ አንተ ፣ መጥፎ ፣ ከርሣም ፣
ለወጣት ፣ አታዝን ፣ ለቄንጦ ፣ አትሣሣም ።
ዝምልዱትን ፣ ከጥርስህ ፣ ፈልቅቄ ፣ ላወጣ ፣
መጥቻለሁና ፣ የዋጥከውን ፣ አምጣ ፣
አንዴ ፣ ልያትና ፣ እንባዬን ፣ አፍስሼ ፣
እርሜንም ፣ አውጥቼ ፣ ተራዬን ፣ አልቅሼ ፣
ሐዘኔን ፣ ገልጬ ፣ ከበቃኝ ፣ በኋላ ፣
እኔንም ፣ ከሷ ፣ ጋር ፣ አብረህ ፣ እንድትበላ ።

ትይንት ፣ ፬ ።

ፓሪስ ።

መብራት ፣ በጁ ፣ ይዞ ፣ የመጣው ፣ ከደጅ ፣
ሮሜዎ ፣ ይመስላል ፣ ያ ፣ የሞንታግ ፣ ልጅ ፣
ጐበዙን ፣ ቲባልትን ፣ የዝምልዱትን ፣ ዘመድ ፣
አሁን ፣ በቅርብ ፣ ቀን ፣ ተጣልቶት ፣ በመንገድ ፣
ገድሎ ፣ ተፈርዶበት ፣ ተሰዶ ፣ የወጣ ፣
አሁን ፣ ደግሞ ፣ እዚህ ፣ ምን ፣ ሊፈጥር ፣ መጣ ?

ለክፋት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ አልመጣም ፣ በደኅና ፤
እንግዴህ ፣ ልያዘው ፣ ድንገት ፣ ልድረስና ።

(ቀረበ) ።

አንተ ፣ የሞንታግ ፣ ልጅ ፣ ዐመፀኛ ፣ መጥፎ ፣
በሰላም ፣ ጸጥታ ፣ የተኛውን ፣ ዐርፎ ፣
ምን ፣ ልታደርግ ፣ ነው ፣ ትኩሱን ፣ ሬሳ ፣
ከመቃብሩ ፣ ላይ ፣ በል ፣ እጅህን ፣ አንሣ ፣
ና ፣ ወዲህ ፣ ልያዝህ ፣ ከዚህ ፣ ቦታ ፣ ውጣ ፤
አሳልፌ ፣ ልስጥህ ፣ በሞት ፣ ለሚቀጣ ።

ሮሜዎ ።

አንተ ፣ መልካም ፣ ወጣት ፣ ዐርፈህ ፣ ሂድ ፣ በደኅና ፤
እኔ ፣ ሞገደኛ ፣ አጥፊ ፣ ሰው ፣ ነኝና ፣
መዘዜ ፣ የበዛ ፣ አሳር ፣ የጐተተኝ ፣
ሕይወቴን ፣ የጠላሁ ፣ ኑሮ ፣ የታከተኝ ፣
ሞትና ፣ መቃብር ፣ ጥፋት ፣ የሸተተኝ ፣
የከፋው ፣ ወንድ ፣ ነኝ ፣ ወደኔ ፣ አትጠጋ ፤
ጠብ ፣ አትፈልገኝ ፣ ለሕይወትህ ፣ ሥጋ ።
ቲባልት ፣ እንደዚሁ ፣ ደርሶ ፣ ሳይቸግረው ፣
በመጥፎ ፣ ንግግር ፣ ሆዴን ፣ አሳረረው ፣
ሳልፈልግ ፣ ገደልኩት ፣ እሱ ፣ ባነሣው ፣ ጠብ ፤
አሁን ፣ ደግሞ ፣ አንተ ፣ ይብቃህ ፣ አትሳደብ ።

ነፍሴን ፣ የጠላሁ ፣ ሰው ፣ በመሆኔ ፣ ፍራኝ ፤
ሳልወድ ፣ በግዴታ ፣ ዐመፅ ፣ አታሠራኝ ፣
የሚወጣው ፣ ምክር ፣ አሁን ፣ ከመላሴ ፣
አልሠራሁበትም ፣ እኔ ፣ እንኳ ፣ ለራሴ ፣
ስለዚህ ፣ ከራሴ ፣ አብልጬ ፣ ስወድህ ፣
እኔን ፣ አመስግነህ ፣ ይሻላል ፣ መሄድህ ፣
አንድ ፣ እብድ ፣ ሰው ፣ ዛሬ ፣ የሰጠኝን ፣ ምክር
ሰምቼ ፣ ድኛለሁ ፣ ብለህ ፣ ይልቅ ፣ ፎክር ።

ፓሪስ ።

እኔስ ፣ አለቅህም ፣ ከያዝኩህ ፣ በኋላ ፤
መስጠት ፣ ትችላለህ ፣ ምክርህን ፣ ለሌላ ።

ሮሜዎ ።

መሞት ፣ ከፈለገህ ፣ እንቢ ፣ ብለህ ፣ በጀ ፣
እንግዲያው ፣ ሞክረኝ ፣ መልካም ፣ ነው ፣ ወዳ

(ይዋጉና ፣ ፓሪስ ፣ ይወድቃል) ።

ቲባልትና ፣ ፓሪስ ፣ እኔን ፣ እያስቈጡ ፣
እኔ ፣ ሳልነካቸው ፣ በግድ ፣ እየመጡ ፣
በእጄ ፣ እየተወጉ ፣ ክዚህ ፣ ዓለም ፣ ወጡ ።
እንዲህ ፣ መሞታቸው ፣ ተናግረውኝ ፣ ክፉ ፣
ተፈርዶባቸው ፣ ነው ፣ በኔ ፣ እጅ ፣ እንዲጠፉ ፣
እንደዚህ ፣ ከሆነ ፣ ፓሪስ ፣ ያንተም ፣ ዕጣ ፣
ጥፋቱ ፣ ያንተ ፣ ነው ፣ በኔ ፣ እንዳትቈጣ ፣

የገ፦ልዬት ፣ ቊንሻና ፣ ደምቆ ፣ እንደ ፣ ብርሃን ፣
ጽርሐ ፣ አርያም ፣ መስሎ ፣ የሰማይ ፣ ውጋጋን ፣
እያንጸባረቀ ፣ ከኮከብ ፣ ሲያበራ ፣
ግርማ ፣ ተጐናጽፎ ፣ በታየበት ፣ ስፍራ ፣
እንሙት ፣ ወዳጄ ፣ አብረን ፣ ከሷ ፣ ጋራ ።

(ሮሜዎ፣በገ፦ልዬት፣መቃብር፣ላይ፣የሐዘን ፣ ንግግር ፣ ያደርጋል)።

ይህችን ፣ ውብ ፣ አበባ ፣ ፍቅር ፣ አሳማሪ ፣
ውሷን ፣ የማትረሳ ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ አክባሪ ፣
ትወድ ፣ የነበረች ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ጨዋታ ፣
እየልኝ ፣ ከዘመድ ፣ ከሰው ፣ ተለይታ ፣
የኔ ፣ ሆደ ፣ ባሻ ፣ ብቻዋን ፣ ተኝታ ፣
ተመልከቱት ፣ እጅዋ ፣ ተመልከቱት ፣ ፊቷ ፤
ወዟ ፣ ገና ፣ አልጠፋም ፣ ከሠራ ፣ አካላቷ ፣
ግንባሯን ፣ ከንፈራን ፣ ተመልከቱ ፣ ጣቷን ፤
ይህን ፣ አበቃቀል ፣ ተክለ ፣ ሰውነቷን ፣
ገላዋ ፣ ያበራል ፣ በደም ፣ ተሸልሞ ፤
ገ፦ልዬት ፣ ሞት ፣ የነካት ፣ አትመስልም ፣ ፈጽሞ ።
እባካችሁ ፣ ሰዎች ፣ ሐዘን ፣ ተካፈሉኝ ፤
ገ፦ልዬት ፣ አልሞተችም ፣ ተኝታለች ፣ በሉኝ ።
ታውቂ ፣ የነበርሽው ፣ ፍቅራዊ ፣ አቀባበል ፣
ሽቊጥቊጥ ፣ እመቤት ፣ ባለመልካም ፣ ዐመል ፣

ተወዳጁ ፡ ድምፅሽ ፡ ውብ ፡ እንደ ፡ ሙዚቃ ፡
በበገናው ፡ ቃሉ ፡ መንፈስ ፡ የሚያነቃ ፡
ዛሬ ፡ ወዴት ፡ ጠፋ? የት ፡ ቦታ ፡ ደረሰ ?
ደግሞስ ፡ ዐይንሽ ፡ ቆቡን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ለበሰ?
ገቦልዬት ፡ ባትሞት ፡ ኖሮ ፡ በውነት ፡ ባትቀበር ፡
ሮሜዎ ፡ እዚህ ፡ ቆሞ ፡ ዝም ፡ አትልም ፡ ነበር ።
ባለም ፡ ላይ ፡ ብንሻ ፡ በውነቱ ፡ የት ፡ አለ ፡
ጨካኝ ፡ አረመኔ ፡ ሞትን ፡ የመሰለ ፡
ጥቂት ፡ አላዘነም ፡ አልሣሣም ፡ ጨርሶ ፡
ይችን ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ሲጥላት ፡ በጥሶ ፡
ይችን ፡ አሳዛኝ ፡ ልጅ ፡ ትተዋት ፡ ሲሄዱ ፡
በሩን ፡ የዘጋ ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ቻለ ፡ ሆዱ ።
እይዋት ፡ ይችን ፡ ቄንጦ ፡ እይዋት ፡ ይችን ፡ ሎጋ
በባዶ ፡ አዳራሽ ፡ በመቃብር ፡ አልጋ ፡
ወፍ ፡ በማይዞርበት ፡ ጭር ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡
ብቻዋን ፡ ቀርታለች ፡ አዲሷ ፡ ሙሽራ ።
በመከራ ፡ ቅመም ፡ ባሳር ፡ ተለውሶ ፡
ገቦልዬት ፡ ሕይወታችን ፡ መሮን ፡ እንደ ፡ ኮሶ ፡
ወጣን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ያላንድ ፡ ደስታ ፤
እንግዲህ ፡ እንኑር ፡ እዚህ ፡ በጸጥታ ።
ባለም ፡ ቦታ ፡ ጠፍቶ ፡ ለመኖር ፡ ተዋደን ፡
እዚህ ፡ ተገናኝን ፡ ካለም ፡ ላይ ፡ ተሰደን ፡

ያሬ

አይቁጩን ፡ እንደዚህ ፡ ካለም ፡ መውጣታችን ፤
በጣም ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ በዛሬው ፡ ዕጣችን ፡
ላለሙ ፡ ደስታ ፡ ለረሻሮሙም ፡ ዕድሜ ፡
ያው ፡ ሞት ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ የሁሉ ፡ ፍጻሜ ?
ገላዬን ፡ ከገላሽ ፡ ዐፅምሽን ፡ ካዕሜ ፡
ሥጋዬን ፡ ከሥጋሽ ፡ ደምሽን ፡ ከደሜ ፡
ቀላቅሎ ፡ የሚያኖር ፡ ከተገኘ ፡ ቦታ ፡
ገቦልዬት ፡ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ደስታ ።
ይቅር ፡ ደኅና ፡ ይሁን ፡ ዓለም ፡ ከነቂሙ ፤
እዚህ ፡ እኔና ፡ አንቺ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡
መቃብር ፡ ሆኖልን ፡ የጸጥታ ፡ ገዳም ፡
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እንኑር ፡ በሰላም ።
ከሚወዱት ፡ ጋራ ፡ እንዲህ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡
ምንኛ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ዐፈር ፡ ትቢያ ፡ መሆን ።

(ሮሜዎ ፡ መርዝ ፡ ጠጥቶ ፡ ሞተ) ።

ትይንት ፡ ፭ ።

አባ ፡ ሎራ ፡ መብራትና ፡ ጉጠት ፡ ይዞ ፡
ወደ ፡ መቃብሩ ፡ ቦታ ፡ መጣ ።

አባ ፡ ሎራ ።

ስፍራው ፡ አያስኬድም ፡ ሆነና ፡ መቃብር ፤
እያደናቀፈ ፡ ያስቸግራል ፡ ለእግር ፡

አዬ ፡ መከራዬ ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡
ምንም ፡ አይታየኝ ፡ ዐይኔ ፡ በጣም ፡ ደክሞ ፡
ማነህ ፡ አንተ ፡ እዚህ ፡ የቆምከው ፡ እንደ ፡ አጥር ?

ቤልሻጥር ።

የሚያውቁኝ ፡ ወዳጅዎ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ቤልሻጥር ።

አባ ፡ ሎራ ።

እግዚአብሔር ፡ ይባርክህ ፡ በል ፡ ልጄ ፡ ንገረኝ ፤
በሩቅ ፡ አላይ ፡ ብሎ ፡ ዐይኔ ፡ አስቸገረኝ ፡
እዚያ ፡ በካፑሌ ፡ የመቃብር ፡ ስፍራ ፡
መብራት ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ የማየው ፡ ሲበራ ?

ቤልሻጥር ።

አዎን ፡ ነው ፡ አባቴ ፡ ሄዷል ፡ እዚያ ፡ ቦታ ፡
ወዳጅዎ ፡ ሮሜዎ ፡ የኔ ፡ መልካም ፡ ጌታ ።

አባ ፡ ሎራ ።

ማን ፡ አልከኝ ?

ቤልሻጥር ።

ሮሜዎ ።

አባ ፡ ሎራ ።

አዬ ፡ የእግዜር ፡ ቍጣ ፡ ፡
ምን ፡ ያኸል ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ እዚህ ፡ ከመጣ ?

ቤልሻጥር ።

ልክ ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ ነው ።

አባ ፡ ሎራ ።

ና ፡ እንሂድ ፡ ወደ ፡ እሱ ፤

ቤልሻጥር ።

አልችልም ፡ አባቴ ፡ አስጠንቅቆ ፡ ራሱ ፡
ወደ ፡ መቃብሩ ፡ እሱ ፡ ወዳለበት ፡
ከቶ ፡ እንዳልጠጋ ፡ ሥራውን ፡ ለማየት ፡
ከልክሎኛልና ፡ በሞት ፡ አስፈራርቶ ፤
ትእዛዙን ፡ ለመጣስ ፡ እኔ ፡ አልችልም ፡ ከቶ ።

አባ ፡ ሎራ ፡

በል ፡ ተወው ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ሠግቷልና ፡ ልቤ ፡
እስቲ ፡ ልመልከተው ፡ ብቻዬን ፡ ቀርቤ ። (አባ ፡ ሎራ ፡ ሄደ) ።

ቤልሻጥር ፡ (ብቻውን) ።

ዛፍ ፡ ተደገፍኩና ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶኝ ፡ ኖሮ ፡
በሕልሜ ፡ ሮሜዎ ፡ አድርጎ ፡ አምባጓሮ ፡
ውጊያ ፡ ገጠሙና ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ሲጥል ፡
አየሁ ፡ ደግሞ ፡ ዛሬ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሲገድል ።

አባ ፡ ሎራ ፡ (ብቻውን) ።

ይህ ፡ ደም ፡ ከየት ፡ መጣ ? ይህ ፡ ሻምላ ፡ ምንድነው ?
እዚህ ፡ የወደቀ ፡ ባለቤት ፡ የሌለው ።

(ዠሊዬት ፡ ነቃች ፤ አባ ፡ ሎራ ፡ ጥግ ፡ ይዞ ፡ ቆመ) ።

ዠልዬት ።

ሮሜዎ ፡ ፍቅሬ ፡ ሆይ ፡ ማን ፡ አምጥቶ ፡ ጣለህ ?

ይኸ ፡ ደም ፡ ምንድነው ? ፓሪስ ፡ ማ ፡ ገደለህ ?
ጨርሰው ፡ አይሰሙም ፡ ሞተዋል ፡ እነሱ ፤
ትንፋሽም ፡ የላቸው ፡ አይንቀሳቀሱ ፡
የእንቅልፍ ፡ የመኝታ ፡ የዕረፍት ፡ የጸጥታ ፡
መሆኑ ፡ ቀረና ፡ ሰላማዊ ፡ ቦታ ፤
ከእንቅልፌ ፡ ስነቃ ፡ አወይ ፡ መቃብሬ ፡
የጦር ፡ ሜዳ ፡ ሆኖ ፡ ጠብቆኛል ፡ ዛሬ ።
ሮሜዎ፡ ምን ፡ ነካው ? ፓሪስን ፡ ማ ፡ መታው ?
ይህን ፡ እንቆቅልሽ ፡ ማነው ፡ የሚፈታው ?

አባ ፡ ሎራ ።

ይኸውልሽ ፡ ልጄ ፡ እግዜር ፡ አልፈቀደም ፤
እንዳሰብኩት ፡ ሆኖ ፡ ነገሩ ፡ አልሄደም ።
አሁንም ፡ ቶሎ ፡ በይ ፡ ውጪ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፤
ሰዎች ፡ መጡ ፡ ከደጅ ፡ ይሰማል ፡ ጫጫታ ፡
እንድትገቢ ፡ አድርጌ ፡ አንቺን ፡ ካንድ ፡ ገዳም ፡
እዚያ ፡ ትኖሪያለሽ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ በሰላም ፡
እባክሽ ፡ ቶሎ ፡ በይ ፡ ሰዎች ፡ ወዲህ ፡ መጡ ፡

ገቦልዬት ።

ከዚህ ፡ እኔ ፡ አልሄድም ፡ እርስዎ ፡ ፈጥነው ፡ይውጡ

(ገቦልዬት ፡ ብቻዋን ፡) ፤ (አባ ፡ ሎራ ፡ ሄደ) ።

ደግሞ ፡ ይህ ፡ ኩባያ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ አመጣው ?
ምን ፡ ይሆን ፡ ሮሜዎ ፡ አግኝቶ ፡ የጠጣው ?

አሁን ፡ ገና ፡ ገባኝ ፡ ዐይኔ ፡ ተከፈተ ፤
መርገዝ ፡ ጠጥቶ ፡ ነው ፡ ሮሜዎ ፡ የሞተ ።
ጥንቱን ፡ ተፈጥሬ ፡ ለዬዬ ፡ ለለቅሶ ፡
እንዴት ፡ ያለው ፡ ሐዘን ፡ ቂየኝ ፡ ተደግሶ ፡
እኔ ፡ እሱን ፡ ስጠብቅ ፡ እዚህ ፡ ተቀብሬ ፡
በድን ፡ ሆኜ ፡ ሬሳ ፡ ቄየሁ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ወይ ፡ አለ ፡ መታደል ፡ መፈጠር ፡ ላበሳ ፤
ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ድክም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ግሥግሣ ፡
ለማየት ፡ ኖሯል ፡ ወይ ፡ ወድቆ ፡ ያንተ ፡ ሬሳ ፤
ለካ ፡ መልካም ፡ ኖሯል ፡ ብቀር ፡ ሳልነሣ ።
ወደ ፡ እሱ ፡ ብመጣ ፡ እኔ ፡ አድርጌው ፡ ዘመድ ፡
እሱስ ፡ ቀድሞኝ ፡ ሄዷል ፡ ባላሰብኩት ፡ መንገድ ።
እንዳልቀየመው ፡ የኔ ፡ ከዳተኛ ፡
መጥቶ ፡ ካጠገቤ ፡ እዩት ፡ እንደ ፡ ተኛ ።
አወይ ፡ ሮሜዎ ፡ የኔ ፡ ሆደ ፡ ባሻ ፡
አንተ ፡ እኔን ፡ ስትፈልግ ፡ እኔም ፡ አንተን ፡ ስሻ ፡
ብቻህን ፡ ሄደሃል ፡ ሰው ፡ ቀርቶኛል ፡ ሳትል ፡
የጭንቅ ፡ ወዳጅህን ፡ እኔን ፡ ሳታስከትል ፡
አልቀርም ፡ ጠብቀኝ ፡ ባለህበት ፡ ቦታ ፤
ኩባያህ ፡ ባዶ ፡ ነው ፡ የለውም ፡ ጠብታ ፡
አንተ ፡ ቢስ ፡ ሥሥታም ፡ ንፉግ ፡ መኰንኔ ፡
ጨልጠህ ፡ ጠጣኸው ፡ ሳታስተርፍ ፡ ለኔ ፡

ቄየኝ ፡ ደረስኩብህ ፡ በርሬ ፡ እንደ ፡ አሞራ ፤
ይኸው ፡ መምጣቴ ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡
አልሠራህበትም ፡ አንተ ፡ ባለቤቱ ፡
እስቲ ፡ ልታቀፈው ፡ ይግባ ፡ በስለቱ ፡
አንጀቴ ፡ ለጨቤህ ፡ ይሁነው ፡ አፎቱ ።
(በሮሜዎ ፡ ጨቤ ፡ ሆዷን ፡ ወግታ ፡ ሞተች) ።

ትይንት ፡ ፮ ።

የመጀመሪያ ፡ ዘበኛ ።

በል ፡ ምራን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ መንገዱና ፡ ስፍራው

የፓሪስ፡ አሽከር ።

ይኸው ፡ እዚህ ፡ ነበር ፡ መብራት ፡ የሚበራው ።

የመጀመሪያ ፡ ዘበኛ ።

ምድሩ ፡ ደም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ምድነው ፡ ነገሩ ?
እስቲ ፡ ቶሎ ፡ ግቡ ፡ ወደ ፡ መቃብሩ ፡
ትልቁ ፡ መኰንን ፡ ፓሪስ ፡ ይኸው ፡ ሞቶ ፡
ቀርቷል ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ እዚህ ፡ ተዘርግቶ ፡
ከሁለት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ የቀበሯት ፡ ሞታ ፡
ገዖልዬትም ፡ ወድቃለች ፡ በጨቤ ፡ ተወግታ ፡
እዩ ፡ ተመልከቱ ፡ በደም ፡ ተለውሳ ፤
አልብሶት ፡ የለም ፡ ወይ ፡ ሚዳውን ፡ ሬሳ ።
ደግሞስ ፡ ሮሜዎ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ አመጣው ፤

እሱም ፡ ደግሞ ፡ ሞቷል ፡ ትንፋሽም ፡ አይወጣው ።
ቶሎ ፡ ንገሯቸው ፡ መስፍኑ ፡ ይጠሩ ፤
ደግሞም ፡ ግማሻችሁ ፡ ስፍራውን ፡ መርምሩ ፡
ይጠሩ ፡ እነ ፡ ሞንታግ ፡ ይምጡ ፡ እነ ፡ ካፑሌ ፤
ፍተሻ ፡ ይደረግ ፡ በዚሁ ፡ ቀበሌ ፡
ምስክር ፡ ተገኝቶ ፡ ታሪኩ ፡ እስቲሰማ ፡
የተሰወረ ፡ ነው ፡ ምስጢሩ ፡ ጨለማ ።

ሁለተኛ ፡ ዘበኛ ።

ይኸው ፡ አገኘነው ፡ የሮሜዎን ፡ አሽከር ።

የመጀመሪያ ፡ ዘበኛ ።

መስፍኑ ፡ እስቲመጡ ፡ እንዳይመረመር ።
(ሦስተኛ ፡ ዘበኛ ፡ ከአባ ፡ ሎራ ፡ ጋራ ፡ መጣ) ።

ሦስተኛ ፡ ዘበኛ ።

እያንቀጠቀጠው ፡ ጥጋ ፡ ይዞ ፡ ሲያለቅስ ፡
ይኸውና ፡ ደግሞ ፡ አገኘሁ ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡
ለምን ፡ እንደ ፡ ያዘው ፡ አልታወቀም ፡ ከቶ ፡
ጐጠቱን ፡ ቀማነው ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ ተገኝቶ ።

የመጀመሪያ ፡ ዘበኛ ።

መስፍኑ ፡ እስቲመጡ ፡ እሱን ፡ አትልቀቁ ፤
የሚጠረጠር ፡ ነው ፡ ይዛችሁ ፡ ጠብቁ ።

(መስፍኑ ፡ ታጅቦ ፡ መጣ) ።

መስፍን ።

እኔን ፡ የሚያስጠራ ፡ ሳይነጋ ፡ ሌሊቱ ፤
ምንድነው ፡ ንገሩኝ ፡ እስቲ ፡ ምክንያቱ ?

(ካፑሌ ፡ ፤ ሚስቱና ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ መጡ)።

ካፑሌ ።

ምስጢሩ ፡ ምንድነው ፡ የሰዉ ፡ ጫጫታ ?

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

እረ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ የሕዝቡ ፡ ጋጋታ ፡
ግማሹ ፡ ሮሜዎ ፡ ግማሹ ፡ ጉልዬት ፡
ግማሾቹም ፡ ፓሪስ ፡ እያሉ ፡ በጩኸት ፡
ወደ ፡ እኛ ፡ መቃብር ፡ ገቡ ፡ እየተጋሩ ።

መስፍን ።

ነገሩን ፡ ንገሩኝ ፡ ደግም ፡ ሆነ ፡ ክፉ ።

የመጀመሪያ ፡ ዘበኛ ።

ልዑል ፡ ሆይ ፡ ያስተውሉ ፡ ፓሪስን ፡ ተግድሎ ፤
እዩት ፡ ሮሜዎ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተንጋሎ ፡

ቀድሞ ፡ የሞተችው ፡ ጉልዬት ፡ ተመልሳ ፡
እይዋት ፡ እሷ ፡ ደግሞ ፡ በደም ፡ ተለውሳ ።

መስፍን ።

ይህ ፡ ዐመፅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡
ፍጠኑ ፡ በቶሎ ፡ ይደረግ ፡ ምርመራ ።

የመጀመሪያ ፡ ዘበኛ ።

የሮሜዎ ፡ ሎሌ ፡ ካንድ ፡ ካህን ፡ ጋራ ፡
እነሆ ፡ ተገኝቷል ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ።

ካፑሌ ።

ሚስቴ ፡ ተመልከቺ ፡ ልጃችን ፡ ተኝታ ፡
እዪው ፡ ደሟ ፡ ሲፈስ ፡ ሆዷ ፡ ላይ ፡ ተወግታ ፤
አስተውዪው ፡ ይህ ፡ ጩቤ ፡ ከመጣበት ፡ ቦታ ፡
ከሞንታግ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ተመልከች ፡ አፎቱ፡
ባዶውን ፡ ይታያል ፡ ይግባሽ ፡ ምክንያቱ ።

የካፑሌ ፡ ሚስት ።

እባክህን ፡ ተወኝ ፡ እኔ ፡ አልችልም ፡ ማየት ፤
ወይ፡ልጄ ፡ ወይ ፡ ልጄ ፡ ወይ ፡ ልጄ ፡ ጉልዬት ።
ሐዘን ፡ ጨፈለቀኝ ፡ ውሃ ፡ ሆንኩኝ ፡ እኔ ፤

ይህንን ፡ ትልቅ ፡ ጉድ ፡ ይህንን ፡ ጭካኔ፡
አይችልም ፡ አይችልም ፡ ሊመለከት ፡ ዐይኔ ።
(ሞንታግና ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ መጡ) ።

መስፍን ።

ሞንታግ ፡ ወዲህ ፡ ቅረብ ፡ ተመልከተው ፡ አንተ ፡
ልጅህን ፡ አስተውለው ፡ እየው ፡ እንደ ፡ ሞተ ።

ሞንታግ ።

የልጅዋ ፡ መሰደድ ፡ ሆኖባት ፡ በሽታ ፡
ሚስቴ ፡ ሌሊት ፡ ሞተች ፡ በሐዘን ፡ ተጐድታ ፡
ያሁን ፡ ሐዘኔ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ መዓት ፤
የባሰ ፡ ጉዳት ፡ ነው ፡ የመጣ ፡ ለቅጣት ።

መስፍን ።

እንባህን ፡ አግደው ፡ አትቸኩል ፡ ለማልቀስ ፤
በፊት ፡ ምርመራውን ፡ ይገባል ፡ መጨረስ ፡
ያመፁን ፡ ምክንያት ፡ ምንጩን ፡ እንወቀው ፤
ምርመራው ፡ ይጀመር ፡ አብረን ፡ እንዝለቀው ፡
የተያዙት ፡ ሰዎች ፡ በፍጥነት ፡ ይቅረቡ ።

አባ ፡ ሎራ ።

እዚህ ፡ ያላችሁት ፡ አሁን ፡ ስታስቡ ፡
እኔ ፡ መገኘቴ ፡ በዚህ ፡ ዐመፅ ፡ ቦታ ፡
ያስጠረጥረኛል ፡ ገፍቶ ፡ በግዴታ ፡

ዳሩ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ ልናገረውና ፡
ተረዱት ፡ ዕወቁት ፡ የኔን ፡ ንጽሕና ።

መስፍን ።

ታሪኩን ፡ እንስማ ፡ በሉ ፡ ይናገሩ ።

አባ ፡ ሎራ ።

ሐተታ ፡ አላበዛም ፡ ልናገር ፡ ባጭሩ ፤
ረዥም ፡ አይደለም ፡ ቀላል ፡ ነው ፡ ምስጢሩ ።
መልካሙ ፡ ሮሜዎ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ የሞተው ፡
ለገቦልዬት ፡ ባሏ ፡ ነው ፤ በተክሊል ፡ ተጋብተው ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሞልተዋል ፡ ቈርበው ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡
በሃይማኖት ፡ ሥራት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሲያደርጉ ፡
የተክሊሉን ፡ ሥራት ፡ ባርኮ ፡ የቀደሰው ፡
እኔው ፡ ራሴ ፡ ነኝ ፤ አይደለም ፡ ሌላ ፡ ሰው ።
በዚያው ፡ ቀን ፡ ቲባልትን ፡ ቢገድለው ፡ ተፈርዶ ፡
ከዚህ ፡ አገር ፡ ወጣ ፡ ሮሜዎ ፡ ተሰዶ ፡
ገቦልዬት ፡ ዘመዶቿ ፡ ይህንን ፡ ሳያውቁ ፡
ለፓሪስ ፡ ሊድሯት ፡ እሷን ፡ ቢያስጨንቁ ፡
በሐዘን ፡ አልቅሳ ፡ ነገረችኝ ፡ መጥታ ፤
ዘዴ ፡ ካልተገኘ ፡ በገዛ ፡ እጅዋ ፡ ሞታ ፡
ልትድን ፡ አሰበች ፡ ካገኛት ፡ ፈተና ፤
እኔም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ አዘንኩና ፡

መድኀኒት ፣ ሰጠኋት ፤ ሕይወት ፣ አጠውልጎ ፣
እንቅልፍ ፣ የሚያስተኛ ፣ እንደ ፣ ሞት ፣ አድርጎ ።
ከዚያም ፣ ለሮሜዎ ፣ ወረቀት ፣ ጽፌለት ፣
እንዲመጣ ፣ አዘዝኩት ፣ ገሥግሦ ፣ በፍጥነት ።
ከእንቅልፍ ፣ ስትነቃ ፣ የመርዙ ፣ ኀይል ፣ አልቆ ፣
እንዲወስዳት ፣ ነበረ ፣ ውጭ ፣ አገር ፣ ደብቆ ፣
የኔንም ፣ ወረቀት ፣ የወሰደልኝ ፣ ሰው ፣
የኛ ፣ ካህን ፣ ነበር ፤ እሱም ፣ ሳያደርሰው ፣
እክል ፣ ስላገኘው ፣ በሄደበት ፣ ቦታ ፣
መልሶ ፣ አመጣልኝ ፣ ትናንትና ፣ ማታ ።
የገቦልዬት ፣ መነሻ ፣ ሌሊት ፣ ስለ ፣ ነበር ፣
እኔም ፣ በጨለማ ፣ መጣሁ ፣ ስደናበር ፣
አሳቤ ፣ ነበረ ፣ ሮሜዎ ፣ እስቲመጣ ፣
ደብቄ ፣ ላቄያት ፣ ከቤት ፣ ሳላስወጣ ፣
ዳሩ ፣ ግን ፣ ገሥግሼ ፣ እኔ ፣ ከዚህ ፣ ስደርስ ፣
ወድቀው ፣ አየኋቸው ፣ ሮሜዎና ፣ ፓሪስ ።
እሷም ፣ ነቃችና ፣ ወዲያው ፣ ስትነሣ ፣
እግዜር ፣ ያመጣውን ፣ ብትቀበል ፣ ታግሣ ፣
የሚሻል ፣ መሆኑን ፣ ላስረዳት ፣ ሞክሬ ፣
ከደጅ ፣ ድምፅ ፣ ሰማሁ ፣ ሳጥናናት ፣ በምክሬ ።
ለመንኳት ፣ እንድትሄድ ፣ እኔን ፣ ተከትላ ፣
ምክሬን ፣ አልሰማችም ፣ ቀረች ፣ እንቢ ፣ ብላ ፤

እኔም ፣ የመጣውን ፣ ለማየት ፣ በኋላ ፤
ወጥቼ ፣ መጣሁኝ ፣ ይኸው ፣ እዚህ ፣ ቦታ ፣
ያስረዳ ፣ ነበረ ፣ የገቦልዬት ፣ ሁኔታ ፣
ሐዘኗ ፣ መሆኑን ፣ በጣም ፣ የበረታ ።
ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ግን ፣ የሆነውን ፣ ነገር ፣
አላየሁምና ፣ አልችልም ፣ መናገር ፣
ገቦልዬት ፣ ሮሜዎን ፣ በተክሊል ፣ ማግባቷን ፣
ታውቀዋለችና ፣ ጠይቁ ፣ ሞግዚቷን ፣
እንግዴህ ፣ ልቀጣ ፣ ቃሌ ፣ ቢገኝበት ፣
በውስጡ ፣ የገባ ፣ ሐሰትና ፣ ውሸት ።

መስፍን ።

ጻድቅ ፣ ሰው ፣ አድርገን ፣ እርስዎን ፣ ከማክበር ፣
አቋርጠን ፣ አናውቅም ፤ የሮሜዎን ፣ አሽከር ፣
በፍጥነት ፣ አቅርቡት ፣ ያየውን ፣ ይናገር ።

ቤልሻጥር ።

የገቦልዬትን ፣ መሞት ፣ ጌታዬ ፣ ብነግረው ፣
መርዶውን ፣ ሲሰማ ፣ ሐዘን ፣ አሰከረው ፣
ወዲያው ፣ ተነሣና ፣ እየገሠገሠ ፣
ሌሊት ፣ እዚህ ፣ ቦታ ፣ ከኔ ፣ ጋር ፣ ደረሰ ።
ይህንን ፣ ደብዳቤ ፣ ላባቴ ፣ ስጥ ፣ ብሎ ፣
እኔን ፣ እንዳልገባ ፣ በብርቱ ፣ ከልክሎ ፣
ትእዛዙን ፣ ባልፈጽም ፣ በሞት ፣ አስፈራርቶ ፣

አየሁት ፣ ሲገባ ፣ እኔን ፣ እዚህ ፣ ትዶ ።

መስፍን ።

ደብዳቤውን ፣ ስጠኝ ፣ እስቲ ፣ ልመልከተው ፤
የፓሪስም ፣ አሽከር ፣ ይጠራ ፣ ወዴት ፣ ነው ?

(የፓሪስ ፣ አሽከር ፣ ቀረበ) ።

ሌሊት ፣ በጨለማ ፣ ደግሞ ፣ ያንተ ፣ ጌታ ፣
እዚህ ፣ ለምን ፣ መጣ ፣ እመቃብር ፣ ቦታ ?

የፓሪስ ፣ አሽከር ።

አበባ ፣ ሊያስቀምጥ ፣ እመቃብሯ ፣ ላይ ፣
መጣና ፣ እኔንም ፣ እዚሁ ፣ ሁኜ ፣ እንዳይ ፣
አዞኝ ፣ እንድጠብቅ ፣ እዚህ ፣ እንድቀመጥ ፣
ሰው ፣ የመጣ ፣ እንደሆን ፣ ምልክት ፣ እንድሰጥ ፣
ስጠብቅ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ መብራት ፣ ይዞ ፣ መጣ ፤
አፍጨሁ ፣ ጌታዬም ፣ ከመቃብር ፣ ወጣ ።
ሁለቱ ፣ ሲዋጉ ፣ ይሽው ፣ እዚህ ፣ ስፍራ ፣
ቶሎ ፣ ሮጬ ፣ ወጣሁ ፣ ዘበኛ ፣ ልጠራ ።

መስፍን ።

አምነን ፣ ለመቀበል ፣ እኛ ፣ የቁሱን ፣ ቃል ፣
ተመልክቼዋለሁ ፣ ደብዳቤው ፣ ይበቃል ።
የፍቅራቸው ፣ ነገር ፣ የገዖልዬትም ፣ መሞት ፣
ይሽው ፣ ይነበባል ፣ በደብዳቤው ፣ ጽፎት ፣
ሁሉንም ፣ ገልጦታል ፤ ከገዖልዬትም ፣ ጋራ ፣

ለመሞት ፣ መምጣቱን ፣ ይሽው ፣ እዚህ ፣ ስፍራ ፣
መድኀኒት ፣ የሚሸጥ ፣ ድኻ ፣ ሰው ፣ አግኝቶ ፣
መርዝ ፣ ይዞ ፣ እንደ ፣ መጣ ፣ በገንዘቡ ፣ ገዝቶ ፣
ይሽው ፣ ተናግሮታል ፣ የሠራውን ፣ ሥራ ፤
ማስረጃው ፣ በቂ ፣ ነው ፣ ትክክል ፣ የጠራ ።
ካፑሌና ፣ ሞንታግ ፣ የት ፣ ናችሁ ? አስተውሉ ፤
የበቀልን ፣ ፍሬ ፣ ዛሬ ፣ ተቀበሉ ፣
እነሆ ፣ ይሽ ፣ ነው ፣ የቂማችሁ ፣ ዋጋ ፤
እዩት ፣ ይህን ፣ መዓት ፣ ይህንን ፣ አዩጋ ፣
እግዚአብሔር ፣ አስቦ ፣ እናንተን ፣ ሊቀጣ ፣
እንዴት ፣ ያለ ፣ መቅሠፍት ፣ በኛ ፣ ላይ ፣ አመጣ ።
በኛ ፣ ላይ ፣ እላለሁ ፤ ምክንያቱም ፣ ዛሬ ፣
ይሽው ፣ ሁለተኛ ፣ ዘመዴን ፣ ቆብሬ ፣
እኔም ፣ ከናንተ ፣ ጋር ፣ ተቀጣሁ ፣ አብሬ ።
ዘላለም ፣ ቂመኞች ፣ የማትመከሩ ፣
ደም ፣ ለማፍሰስ ፣ ብቻ ፣ የምትጣጣሩ ፣
ፍቅርን ፣ የጠላችሁ ፣ ሆናችሁ ፣ ስትኖሩ ፣
ትልቅ ፣ ትምህርት ፣ ነው ፣ ብትመለከቱ ፣
ዛሬ ፣ ልጆቻችሁ ፣ ለፍቅር ፣ ሲሞቱ ።
ሌላ ፣ ልጅ ፣ የላችሁ ፣ አለኑሱ ፣ በቀር ፤
ከዚህ ፣ በላይ ፣ ቅጣት ፣ መቼም ፣ አይፈጠር ።

ካፑሌ ።

ይህ ፣ የወደቀብኝ ፣ የዛሬው ፣ ቅጣቴ ፣
ከሥጋዬ ፣ ዘልቆ ፣ ተሰማኝ ፣ ሳጥንቴ ፣
ለኔ ፣ ሆኖ ፣ ሳለ ፣ የሚገባኝ ፣ ሞቱ ፣
ንጹኅ ፣ የኔ ፣ ልጅ ፣እንደዚህ ፣ በከንቱ ፣
ደሟን ፣ በኔ ፣ ክፋት ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ አፍስሳ ፣
መሥዋዕት ፣ ሆና ፣ ሞተች ፣ ለክፋቴ ፣ ካሳ ።
ሞንታግ ፣ ወንድሜ ፣ ሆይ ፣ በል ፣ እጅህን ፣ ስጠኝ
ይብቃን ፣ እንታረቅ ፣ በፍቅር ፣ ጨብጠኝ ።
(እጅ ፣ ለጅ ፣ ይጨባበጣሉ) ።
ደኅና ፣ አድርገን ፣ ከፈልን ፣ የጎጢአትን ፣ ዋጋ ፤
እየው ፣ ሲያንገበግብ ፣ የእግዚአብሔር ፣ አለንጋ ፣
ክፉዎች ፣ ብንሆንበት ፣ እሱም ፣ ክፉ ፣ ሆኖ ፣
ድብን ፣ አደረገን ፣ ሳይራራ ፣ ጨክኖ ፣
በውነት ፣ ሆንኩ ፣ ዛሬ ፣ ዕርቅን ፣ የምሻ ፣ ሰው ፣
በልጁ ፣ ንጹሕ ፣ ደም ፣ መሬት ፣ በፈሰሰው ።

ሞንታግ ።

እኔም ፣ ለገዖልዬት ፣ ይኸው ፣ በዚህ ፣ ስፍራ ፣
ሐውልት ፣ አቆማለሁ ፣ በወርቅ ፣ የተሠራ ፣
ዜናዋ ፣ እንደ ፣ ወርቅ ፣ ያማረ ፣ ነውና ፤
ዘለዓለም ፣ እንዲኖር ፣ ስሟ ፣ በቬሮና ፣

ከልብ ፣ ለሆነ ፣ ለእውነተኛ ፣ ፍቅር ፣
ምሳሌ ፣ ይሆናል ፣ አብነት ፣ ምስክር ።

መስፍኑ ።

ተመልከቱት ፣ ፊቷን ፣ የዛሬ ፣ ጧት ፣ ፀሓይ ፣
ደመና ፣ ለብሳለች ፣ ውበቷ ፣ እንዳይታይ ፤
ሆናለች ፣ ከሰው ፣ ጋር ፣ ሐዘኑን ፣ ተካፋይ ።
በሉ ፣ ሁላችሁም ፣ ሥራችሁን ፣ ሥሩ ፤
ሐዘን ፣ ያለው ፣ ያልቅስ ፣ ሙታን ፣ ይቀብሩ ፣
እንደ ፣ ሙታን ፣ ሁሉ ፣ እኛን ፣ በመቅጣቱ ፣
ነፍሳቸውን ፣ ያድን ፣ እግዜር ፣ በምሕረቱ ፣
መቼም ፣ መቼም ፣ ቢሆን ፣ ታይቶ ፣ አያውቅና ፣
እንደ ፣ እነዚህ ፣ ልጆች ፣ የሚያሳዝን ፣ ዜና ።

